ኅዳር 28 ቀን 2009
የረቡዕ እትም

Rescue Press freedom from the hangman!!
የፕሬስ ነፃነትን ከስቅላት ያድኑ!

ቅፅ 22 ቁጥር 1733 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ | ጳጉሜን 6 ቀን 1987 ተመሠረተ |ዋጋ ብር 10.00

የዓለም ባንክ ኢትዮጵያ የብር ምንዛሪ ማስተካከያ እንድታደርግ አሳሰበ

ብሔራዊ ባንክ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል አለ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስትሩ ዶ/ር አብርሃም ተከስተና የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ካሮላይን ተርክ አምስተኛው የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ ሪፖርት ይፋ በተደረገበት ወቅት ተገኝተው ነበር

በአሥራት ስዩም

በከፍተኛ ደረጃ ማሽቆልቆል እያሳየ ያለውን የወጪ ንግድ ገቢን ለማረቅና የወጪ ንግድ ምርቶች አቅርቦት እንዲጨምር ለማበረታታት፣ ኢትዮጵያ የብር የምንዛሪ ምጣኔን እውነተኛውን የኢኮኖሚ አቅሟን በሚያመላክት ደረጃ ማስተካከል ይገባታል ሲል የዓለም ባንክ ምክር ሰጠ::

ባንኩ ማክሰኞ ኅዳር 27 ቀን 2009 ዓ.ም. በሸራተን አዲስ ይፋ ያደረገው አምስተኛው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሪፖርት ካነጣጠረባቸው ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው፣ ሚዛኑን የሳተው የብር የምንዛሪ ምጣኔ ጉዳይ ነበር:: ከሪፖርቱ አዘጋጆች አንዱ የሆኑት ማይክል ጋይገር እንደሚሉት ከሆነ፣ የኢትዮጵያ የምንዛሪ ምጣኔ በተለይ እ.ኤ.አ. በ2010 ከተደረገው የምንዛሪ ማስተካከያ (Devaluation) በኋላ በዝግታ እየቀነሰ መሆኑ የታየ ቢሆንም፣ አገሪቱ በምትከተለው ቅይጥ ምንዛሪ ፖሊሲ ምክንያት (Managed Floating) አሁንም እውነተኛው የብር የምንዛሪ ምጣኔና በሥራ ላይ ያለው ምጣኔ በእጅጉ የተዛነፈ ነው::

በዚህ መሠረት እውነተኛውን የምንዛሪ ምጣኔ የሚለካው (ሪል ኢፌክቲቭ ኤክስቼንጅ ሬት) (Real Effective Exchange Rate) የምጣኔውን መዛነፍ በግልጽ እንደሚያሳይ የገለጹት ሚስተር ማይክል፣ የምንዛሪ ማሻሻያው ከተደረገ በኋላ (2010) እንኳን የብር የምንዛሪ ምጣኔ ቢያንስ በ84 በመቶ ጨምሮ እንደሚታይ አስረድተዋል:: በመሆኑም ብር የምንዛሪ ምጣኔውን ስቶ ከሚገባው በላይ መቆለሉን (Overvalue) ጠቅሰው ተከራክረዋል::

እንደ ኢኮኖሚስቱ ጥናት ምጣኔውን በእጅጉ የሳተው ብር ይበልጥ አሳሳቢ የሚሆነው፣ ከወቅቱ የወጪ ንግድ ገቢ ማሽቆልቆል ጋር በጥምረት ሲታይ ነው:: ‹‹ምናልባትም የአገሪቱን የወጪ ንግድ እየጎዱ ካሉ ነገሮች መካከል አንደኛው የዚህ የእውነተኛው የብር የምንዛሪ ያለአግባብ ማበጥ ነው፡፡›› ያሉት ሚስተር ማይክል፣ የምንዛሪ ማሻሻያ ማድረጉ ብልኃት የተሞላበት አካሄድ መሆኑን ጠቁመዋል::

የተመጠነ የምንዛሪ ማሻሻያ የአገሪቱን የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነት እንደሚጨምር በጥብቅ የሚመክሩት የባንኩ ባለሙያዎች፣ በስብሰባ አዳራሹ የተገኙ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ልብ ማሸነፍ ተስኗቸው ታይተዋል:: በተለይ የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥና ዋና ኢኮኖሚስት አቶ ዮሐንስ አያሌው የምንዛሪ ማሻሻያውን ምክር ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርገውታል:: እንደ አቶ ዮሐንስ ገለጻ ከሆነ፣ የምንዛሪ ማሻሻያ ዓይነት መዘዝ ያላቸው የፖሊሲ ውሳኔዎችን ከመወሰን በፊት ማጤኑ ጠቃሚ ይሆናል:: በመሆኑም የምንዛሪ ማሻሻያው የሚያስከትለው ጉዳትና ያመጣል ተብሎ የሚጠበቀው ጥቅም መወዳደር አለባቸው ብለዋል::

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሐ ግብር አፈጻጸምን ገለልተኛ አካል እንዲከታተል ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠየቁ

በዮሐንስ አንበርብር

እስከ 2012 ዓ.ም. ድረስ ተግባራዊ እንዲሆን ታስቦ ለውይይት የቀረበው የሰብዓዊ ድርጊት መርሐ ግብር አፈጻጸምን የሚከታተልና መንግሥት የሚወከልበት ገለልተኛ አካል እንዲቋቋም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠየቁ::

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር 26 እና 27 ቀን 2009 ዓ.ም. ከተቃዋሚ ፓርቲዎች በድርጊት ጋር በመርሐ ግብሩ ላይ ውይይት አካሂዷል::

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

የንግድ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ያዕቆብ ያላ የሎጅስቲክስ ኢንተርፕራይዝ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኑ

አቶ ያዕቆብ ያላ

በውድነህ ዘነበ

የንግድ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ያዕቆብ ያላ የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ኢንተርፕራይዝ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

በሚዲያና ኮምዩኒኬሽንስ ሴንተር (ኤም.ሲ.ሲ)
ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር
እየታተመ የሚወጣ ጋዜጣ

ረቡዕ ኅዳር 28 ቀን 2009

አድራሻ፡- ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 2347 ፖ.ስታ 7023 አ.አ ኢትዮጵያ
ማስታወቂያ ሽያጭና ስርጭት
0910 885206/ 011 6 61 61 79/ 85
ፋክስ: 011-661 61 89
mcc@ethionet.et
E-mail: mccreporter@yahoo.com
Website: www.ethiopianreporter.com

ዋና ሥራ አስኪያጅ: አማረ አረጋዊ
ማኔጂንግ ኤዲተር: መላኩ ደምሴ
ዋና አዘጋጅ: ዘካሪያስ ስንታየሁ
የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 የቤት ቁ. 217
ከፍተኛ አዘጋጆች: ዳዊት ታዬ, ሔኖክ ያሬድ, ሰለሞን ጎሹ, ብርሃኑ ፈቃደ
አዘጋጆች: ምሕረት ሞገስ
ረዳት አዘጋጆች: ታደሰ ገ/ማርያም, ምሕረት አስቻለው, ታምሩ ጽጌ, የማነ ናግሽ, ዮሐንስ አንበርብር
ውድነህ ዘነበ

ከፍተኛ ሪፖርተር: ደረጀ ጠገናው
ሪፖርተሮች: ምሕረተሥላሴ መኮንን, ሻሂዳ ሁሴን
ማርኬቲንግ ማናጀር: እንዳልካቸው ይማም
ሴልስ: ሃና ግርማ፣ ብሩክ ቸርነት፣ እስከዳር ደጀኔ፣ ኤፍሬም ገ/መስቀል, ሔኖክ መርሐጽድቅ፣ መዋዕል ነጋሽ
ማስታወቂያ ፕሩፍሪደር: መሳይ ሰይፉ፣ ፣ መላኩ ገድፍ ፣ ዘመኑ ተናኘ
ኮምፒውተር ጽሑፍ: ብርቱካን አባተ፣ ሄለን ይታየው፣ ቤተልሔም ታደሰ፣ ቤዛዊት መኮንን፣ መስከረም ሽብሩ፣
ማስታወቂያ ፅሁፍ: ቤተልሔም ዘለቀ፣ መሠረት ወንድሙ፣ ራሔል ሻወል፣ የሺሀረግ ሀይሉ
ሕትመት ክትትል: የየሱስወርቅ ማሞ፣ ገዛኸኝ ማንደፍሮ
ዌብ ሳይት: ቤዛዊት ተስፋዬ፣ ቢኒያም ሐይሉ

ዋና ግራፊክ ዲዛይነር: ደበቃል ጌታሁን
ከፍተኛ ግራፊክ ዲዛይነር: ሳሙኤል ስገሰ
ግራፊክ ዲዛይነሮች: ፀሐይ ታደሰ, ፋሲካ ባልቻ, ስሜነህ ሲሳይ, ነፃነት ያዕቆብ, ቤዛዬ ቴዎድሮስ
ዋና ፎቶግራፈር: ናሆም ተሰፋዬ
ፎቶግራፈሮች: ታምራት ጌታቸው, መስፍን ሰሎሞን, ዳንኤል ጌታቸው
ካርቱኒስት: ኤልያስ አረዳ

በጳጉሜን 6 1987 ተጀመረ በሳምንት ሁለት ጊዜ የሚታተም
አድራሻ:- ከቦሌ መድኃኒዓለም ወደ ብራስ ሆስፒታል በሚወስደው መንገድ ከቦሌ ኢንተርናሽናል ሆቴል አጠገብ
ስልክ 0910-885206/ 011-661 61 79/85/87 ፋክስ: 011-661 61 89

ርእሰ አንቀጽ

መንግሥት የሚወስዳቸው ዕርምጃዎች ከሕዝብ ፍላጎትና ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ይጣጣሙ!

የአገሪቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመርያዎች ተግባራዊ የሚደረጉት በአስፈጻሚው አካል ወይም መንግሥት ነው፡፡ መንግሥት ሕዝብን ሲያስተዳድር ከአገር ዘላቂ ጥቅምና ሉዓላዊነት ጋር ትልቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ ከሕግ አውጭውና ከሕግ ተርጓሚው ጋር በመናበብ ግዴታውን መወጣት ይኖርበታል፡፡ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች፣ ሕግ በማስከበር፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በግብርና፣ በንግድ፣ በዲፕሎማሲ፣ በመሠረተ ልማት ግንባታዎች፣ በመሬት አስተዳደርና ልማት፣ ወዘተ የሚወሰዱ ዕርምጃዎች የሕዝቡን ፍላጎት ያገናዘቡና ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር መጣጣም አለባቸው፡፡ ሕዝብ በአገሩ ደስተኛ የሚሆነውና የሥራ ሞራሉ የሚነሳሳው በዚህ መንገድ ነው፡፡

መንግሥት ከሕዝብ የተሰጠውን አደራ በብቃት ለመወጣት ሕዝብ የሚያምንባቸውና የሚተማመንባቸው ሹማምንት ሊኖሩት ይገባል፡፡ እነዚህ በትምህርታቸው፣ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ሹማምንት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሕዝቡን ፍላጎት አውቀው ሥራቸውን በአግባቡ ሲወጡ ሁከትና ብጥብጥ ሥፍራ አይኖራቸውም፡፡ ይልቁንም የሕዝብ ፍላጎት ሲከበር የሕግ የበላይነት ይረጋገጣል፡፡ ፍትሐዊ የሥልጣንና የሀብት ክፍፍል ይኖራል፡፡ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች በሚገባ ይከበራሉ፡፡ ምርጫ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ይሆናል፡፡ የሲቪክ ማኅበራት ያብባሉ፡፡ የዜጎች ተሳትፎ ይዳብራል፡፡ ግልጽነትና ተጠያቂነት መርህ ይሆናሉ፡፡ በዚህ መሠረት የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እየተገነባ ለሁሉም ወገን የሚበጅ የፖለቲካ ምኅዳር ይፈጠራል፡፡ ድንጋይ ወርዋሪ ሳይሆን ጠያቂና ሞጋች ትውልድ ለማፍራት ይጠቅማል፡፡

አገራችንን ጨምሮ በበርካታ አገሮች በሕዝብና በመንግሥት መካከል መቃቃር የሚፈጠረው፣ ሕዝብ በመንግሥት ላይ ያለው አመኔታ ሲነጥፍና የመንግሥት የአገልጋይነት ሚና ሲኮላሽ ነው፡፡ መንግሥት የልማት ዕቅዶችን ዘርግቶ የፈለገውን ያህል ቢማስን የሕዝብ ተሳትፎ ካልታከለበት ፋይዳ አይኖረውም፡፡ መንግሥት በሕዝብ የተመረጠ አካል መሆኑን ማረጋገጫው የሥልጣኑ ባለቤት ለሆነው ሕዝብ በሚኖረው ታዛዥነት መጠን ነው፡፡ የመንግሥት የተለያዩ ተቋማት በየዘርፎቻቸው ከግብር ከፋዩ ሕዝብ ጋርም ሆነ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያላቸው ግንኙነት በመተማመን ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ይህ መተማመን የሚፈጠረው ደግሞ የመንግሥት ተቋማቱ በአገልጋይነት መንፈስ ሥራቸውን ሲያከናውኑና ግልጽነትና ተጠያቂነት ሲኖርባቸው ነው፡፡ ዘመኑ ከደረሰበት የዕድገት ግስጋሴ ጋር በመጣጣም ለተገልጋዩ ሕዝብ ከበሬታ ሰጥተው ማገልገል ሲችሉ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በልማዳዊ አሠራር ተተብትበው የትም መድረስ አይችሉም፡፡ ለአገሪቱም አይጠቅሙም፡፡

ከዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር አመራር መስጠት የሚችሉ ብቁ ሹማምንት በየቦታው መመደብ አለባቸው፡፡ እነዚህ ሹማምንት የግድ ከገዥው ፓርቲ ብቻ መምጣት የለባቸውም፡፡ አገራቸውን በከፍተኛ ፍቅር ለማገልገል የሚፈልጉ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የሠለጠኑና ልምድ ያካበቱ ዜጎች በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ በብዛት አሉ፡፡ ይህ ዘመን በቴክኖሎጂ የተመነደገና በዳበሩ አስተሳሰቦች የሚመራ እንደመሆኑ መጠን፣ ከጊዜው ጋር እኩል የሚራመድ አሠራር ማስፈን ተገቢ ነው፡፡ ሥልጣን ሕዝብን ማገልገያ እንጂ በሕዝብ ላይ መገልገያ እንዳልሆነ በአንክሮ መጤን አለበት፡፡ እንኳን ተሿሚ ግለሰቦች ይቅሩና ፓርቲዎች በሕዝብ ድምፅ ብቻ ነው ሥልጣን መያዝ ያለባቸው፡፡ እኔ ብቻ ነኝ የምችለው ከማለት ይልቅ፣ ለአገር በተሻለ የሚጠቅሙ አሉ ወይ? ብሎ ማፈላለግ ለዘላቂው የአገርና የሕዝብ ጥቅም ጥሩ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ያስከብራልም፡፡

የመልካም አስተዳደር ዕጦት አለ ሲባል፣ ፍትሕ ችግር ውስጥ ገብቷል ሲባል፣ ሙስና አገርን እንደ ሰደድ እሳት እየበላ ነው ሲባል፣ ሕዝብ በመንግሥት ላይ አቂሟል ሲባልና የመሳሰሉት ችግሮች በስፋት ሲስተጋቡ ግራና ቀኙን ማየት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ችግሮች ክትራቸውን ጥሰው ለአገር ህልውና ሥጋት ሲደቅኑ ዘለቄታዊ መፍትሔያቸው ሊታሰብበት ይገባል፡፡ የተጫረውን እሳት በጊዜያዊ ዕርምጃ አጥፍቶ መቀመጥ ሳይሆን፣ ከሕዝብ መሠረታዊ ጥቅምና ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የሚጣጣም ዘላቂ መፍትሔ ማፈላለግ ብልህነት ነው፡፡ በመንግሥት ውሳኔ አሰጣጥ ወቅት ግራና ቀኙን በሚገባ በመመርመር ከአገርና ከሕዝብ ዘላቂ ጥቅም አንፃር ድምዳሜ ላይ መድረስ ተገቢ ነው፡፡ በግዴለሽነትና በማናለብኝነት የሚወሰዱ ግብታዊ ዕርምጃዎች አገርን ለጥፋት፣ ሕዝብን ደግሞ ለእንግልት ሲዳርጉ በተደጋጋሚ ታይተዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ አካሄድ በፍፁም መታረም አለበት፡፡

የአገር ሰላምና ደኅንነት በሕዝብ እርካታ ላይ ይወሰናል፡፡ ጥቂቶች እንደፈለጉ እንሁን ሲሉ ብዙኃኑ ለምን ብለው ይነሳሉ፡፡ የሕግ የበላይነት ሲረጋገጥና የሕዝብ ፍላጎት ሲከበር ግን ብዙኃን ይደሰታሉ፡፡ ጥቂቶቹም ቢሆኑ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ በተለይ በአገር አጠቃላይ ጉዳይ የሕዝብ ፍላጎት ገዥ መሆን አለበት፡፡ ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የተቃናና የሕዝብና የአገርን ዘለቄታዊ ጥቅም የሚያስከብር ውሳኔ ቅራኔን ለማስወገድና ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር ይጠቅማል፡፡ መንግሥት በተለያዩ ጉዳዮች ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሕዝቡን ፍላጎት በሚገባ መረዳት አለበት፡፡ የሕዝብ ፍላጎት ሲባል ከጊዜያዊ እርካታ ጋር የተያያዘ ስሜት ሳይሆን፣ ከአገር ዘለቄታዊ ጥቅም ጋር የተቆራኘ ውሳኔ ማለት ነው፡፡ ስለዚህም መንግሥት የሚወስዳቸው ዕርምጃዎች ከሕዝብ ፍላጎትና ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ሊጣጣሙ ይገባል!

ሰሞኑን የኤሌክትሪክ ኃይል የሚቆራረጠው ከ30 በላይ መስመር ተሸካሚ ምሰሶዎች በመውደቃቸው ነው

በታምሩ ጽጌ

ባለፉት ሁለት ሳምንታት በተከታታይ ቀናት የኤሌክትሪክ ኃይል ሲቆራረጥ የነበረው፣ በአዲስ አበባ ከተማ ከተተከሉ 126 ዋና መስመር ተሸካሚ ምሰሶዎች ውስጥ ከ30 በላይ የሚሆኑት ምሰሶዎች በንፋስ ኃይል በመውደቃቸው መሆኑን፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

በተለይ ኅዳር 24 እና 25 ቀን 2009 ዓ.ም. በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ሊባል በሚችል ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ ንፋስ በመከሰቱ ከተተከሉ ረዥም ዓመታት ያስቆጠሩ ዋና መስመር ተሸካሚ የእንጨት ምሰሶዎች ሊቋቋሙት ባለመቻላቸው፣ ተገርስሰው መውደቃቸውን የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ለሪፖርተር ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዲስትሪቢዩሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ብርሃኔ እንደተናገሩት፣ በመላው አገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ተሸካሚ የኮንክሪት ምሰሶዎች እየተገነቡ ነው፡፡ ኤስጂዲሲሲ የተባለው የቻይና መንግሥት ኩባንያ በ80 ሚሊዮን ዶላር መቐለ፣ ደሴ፣ ባህር ዳር፣ ድሬዳዋን ጨምሮ በስምንት የክልል ከተሞች የኮንክሪት ማሠራጫ ግንባታ ላይ ነው፡፡ መስመር ከመለወጡ ጎን ለጎንም የትራንስፎርመር ዕድሳትም ይከናወናል ብለዋል፡፡

ዘፉ (ZHEFU) የሚባለው ሌላው የቻይና ኩባንያ በ20 ሚሊዮን ዶላር፣ ፓወር ቻይና የሚባለው ኩባንያ ደግሞ በ160 ሚሊዮን ዶላር የአዲስ አበባን የኤሌክትሪክ ኃይል ማሠራጫ መስመር የመቀየርና አቅም የማሳደግ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

አቶ ሰለሞን ኃይሌ

የአዲስ አበባ መሬት ልማት ቢሮ ኃላፊ ወደ ፌዴራል መንግሥት ተዛወሩ

በውድነህ ዘነበ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሰለሞን ኃይሌ፣ የኮንስትራክሽን ሚኒስትር ዴኤታ ሆነው ተሾሙ፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ፊርማ ኅዳር 15 ቀን 2009 ዓ.ም. በወጣ ደብዳቤ የኮንስትራክሽን ሚኒስትር ዴኤታ ሆነው የተሾሙት አቶ ሰለሞን፣ ባለፈው ዓርብ ኅዳር 23 ቀን 2009 ዓ.ም. አዲሱን የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀላቅለዋል፡፡

አቶ ሰለሞን ወደ አዲስ አበባ ከመምጣታቸው በፊት በትግራይ ክልል የመቐለ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሆነው ሠርተዋል፡፡ በኋላም የትግራይ ክልል የከተማ፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ ሆነው ሠርተዋል፡፡

በኅዳር 2004 ዓ.ም. የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የሚደነግገው አዋጅ ከወጣ ከአሥር ወራት በኋላ አቶ ሰለሞን ወደ አዲስ አበባ በመምጣት፣ በአቶ ኩማ ደመቅሳ ከንቲባነት ወቅት የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

በአገር አቋራጭ አውቶቡሶች ዘመናዊ የቲኬት አሠራር ተግባራዊ ሊሆን ነው

ቲኬት ቆራጮች ሥጋት ገብቷቸዋል

በብርሃኑ ፈቃደ

በ1,500 የአገር አቋራጭ አውቶቡሶች በመላው የአገሪቱ ትራንስፖርት መስመሮች እንደሚጀመር ይፋ የተደረገው ዘመናዊ የቲኬት ሽያጭ አገልግሎት፣ ተሳፋሪዎች ከዚህ ቀደም ይገጥማቸው የነበረውን እንግልትና አላስፈላጊ ወጪ እንደሚያስቀር ተገለጸ፡፡

ክፍያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ ኩባንያ ከአውቶቡስ ባለንብረቶች ማኅበራት ጋር በመሆን አገልግሎቱን ለማቅረብ ለሁለት ወራት ሲያዘጋጅ የቆየውን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት የሚሠራ የቲኬት አገልግሎት፣ ከመጪው ታኅሳስ 1 ቀን 2009 ዓ.ም. ጀምሮ በ170 የጉዞ መስመሮች ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጀመር ይፋ ተደርጓል፡፡ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከትራንስፖርት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ቴክኖሎጂው ሥራ ላይ እንዲውል አደርጓል፡፡

ከአዲስ አበባ በመነሳት በሁሉም የአገሪቱ መዳረሻ መስመሮች በ1,500 የአገር አቋራጭ አውቶቡሶች የሚጀመረው ይህ የኤሌክትሮኒክ ቲኬት ሽያጭ፣ በመናኸሪዎች ሲታዩ የነበሩ ወከባዎችን ከማስቀረት ጀምሮ ቲኬት ለማግኘት በተጓዦች ላይ ይደርሱ የነበሩ እንግልቶችን ያስቀራል ሲሉ፣ የትራንስፖርት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ካሳሁን ኃይለ ማርያም ገለጸዋል፡፡

ለአገር አቋራጭ አውቶቡሶች የተዘጋጀው ዘመናዊ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ይፋ ሲደረግ

አቶ ካሳሁን ማክሰኞ ኅዳር 27 ቀን 2009 ዓ.ም. በተካሄደው ጋዜጣዊ መግለጫ ወቅት እንደተናገሩት፣ ዘመናዊው አሠራር በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙት አምስቱም መናኸሪያዎች ማለትም በአውቶቡስ ተራ፣ በአየር ጤና፣ በአስኮ፣ በላምበረትና በቃሊቲ መናኸሪያዎች ተግባራዊ መደረግ ይጀምራል፡፡

የኤሌክትሮኒክ ቲኬትና ክፍያ ሥርዓቱ በ21 የአውቶቡስ ባለንብረቶች ማኅበራት አማካይነት እንዲጀመር ስምምነት ተደርሶ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሥራው እንደሚጀመር የገለጹት ደግሞ፣ የአገር አቋራጭ አውቶቡስ ባለንብረቶች ማኅበር የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ብርሃነ አምባዬ ናቸው፡፡ አቶ ብርሃነ እንዳሉት፣ ከመናኸሪያ ውጪ የሚታየውን ‹‹የሕገወጥ›› ትራንስፖርት እንቅስቃሴን ጨምሮ በመናኸሪያዎች አካባቢ የሚታየውን ግርግር ብሎም በበርካቶች ተሳፈሪዎች ዘንድ ለአገር አቋራጭ አውቶቡሶች የነበረው አመኔታ እንደሚመለስ እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡

በደርሶ መልስ ለተሳፋሪዎች አገልግሎት የሚሰጠው ይህ ቴክኖሎጂ፣ ተሳፋሪዎች ለጉዞ አስቀድመው ዕቅድ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ማስታወቂያ

The Fred Hollows Foundation
ACN 070 556 642

Invitation FHFE BID No. FHFE/011/2016

The Fred Hollows Foundation Ethiopia (FHFE), invites potential suppliers for Bid # FHFE/011/2016 as per the bellow detail:

1. Bid Requirement:

   A. Interested suppliers should quote as per the following table:

#	Item description	Unit	Qty.
1	Amplifier with Mixer - 250W capacity, with Flash + SD card slot, with double speaker, compatible with solar power, with XLR & Banana mic output, manufactured in the year 2015 -2016	set	139
2	Vocal Microphone – Wired, Sensitivity 1 Khz, frequency response of 15Khz, with banana output, manufactured in the year 2015 -2016	set	139
3	Speaker – 300W capacity, with cable jack (XLR & Banana input), manufactured in the year 2015 -2016	set	139

   B. The price must be in ETB and bidders should mention bid validity date, quantity available, delivery time and term of payment,

2. Terms and Conditions:

   A. Bids should be submitted in a sealed envelope and hand delivered. FHFE will not consider bids submitted through fax or post office,

   B. Bidders should furnish their VAT & TIN certificate, valid trade license, valid trade registration certificate and other supporting documents. Bidders should submit their bids in English,

   C. Bidders who meet the above criteria can submit their bid, at the following address, until the closing date and time, December 14th, 2016 at 9:00 AM,

   D. Bid will be opened on December 14th, 2016 10:00AM, in the presence of interested bidders who wishes to attend,

Procurement & Logistics Coordinator, Fred Hollows Foundation Ethiopia,
22 Mazoria, Haile G/Selassie Ave., Rebecca Building, 4th Floor, Addis Ababa
Tel. 011 618 1042/43.
FHFE reserves the right to accept or reject any bid.

የኢትዮጵያ ቅመማ ቅመም ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር
Ethiopian Spice Extraction Factory PLC

ክፍት የሥራ ማስታወቂያ

የኢትዩጵያ ቅመማ ቅመም ፋብሪካ ኃላ/የተ/የግል/ማህበር ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ባለሙያዎችን አወዳድሮ በቋሚነት ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

ተቁ	የሥራመደቡ መጠሪያ	ተፈላጊ የት/ደረጃ	የሥራ ልምድ	ብዛት	ደመወዝ
1	የሽያጭ ክለርክ	በሴልሰማን ሺፕ ወይም በማርኬቲንግ ማኔጀመንት ዲኘሎማ	በፋብሪካ ሽያጭ ሠራተኛነት ቢያንስ 3 ዓመት የስራ ልምድ ያለው	1	በስምምነት
	የቴክኒክ ዋና ክፍል ኃላፊ	በቢ.ኤስ.ሲ. ዲግሪ /አድቫንስድ ዲፕሎማ በሜካኒካል ምህንድስና፣ በኤሌክትሪካል ምህንድስና ወይም በሜታል ቴክሎጂ የተመረቀ	በማምረቻ ድርጅት ውስጥ 6/8 ዓመት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለውና ቢያንስ 3 ዓመት በኃላፊነት የሰራ	1	በስምምነት

አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ከCV ጋር በማያያዝ ቃሊቲ ጉምሩክ ፊት ለፊት በአዋሽ ባንክ ገባ ብሎ በሚገኘው ፋብሪካችን አስተዳደር ቢሮ ድረስ በግንባር በመቅረብ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡
ለበለጠ መረጃ፡ 0118495373 ደውለው ይጠይቁ

ድርጅቱ

ILRI INTERNATIONAL LIVESTOCK RESEARCH INSTITUTE
International Livestock Research Institute
Consultative Group on International Agricultural Research
People and Organizational Development

POSITION ANNOUNCEMENT

International Center of Insect Physiology & Ecology (ICIPE)

Accountant

Ref. No.: A/46/16

The position: The International Centre of Insect Physiology & Ecology (*icipe*) seeks to hire an Accountant position who will be based in Addis Ababa, Ethiopia.

General: International Centre of Insect Physiology & Ecology (*icipe*)—African Insect Science for Food and Health is a world-class research centre with a mission to alleviate poverty by ensuring food security, improving health, protecting the environment and building the capacity of researchers and communities across the developing world, through the application of insect sciences. Employing more than 500 national and international staff, *icipe* is headquartered in Nairobi, Kenya with outposts in Ethiopia and on the shores of Lake Victoria in western Kenya. *icipe* has a proud reputation and history of delivering world-quality science that has made crucial contributions to African food and health policy, delivered development outcomes to rural communities, and has been at the forefront of building Africa's biological research capacity. The Centre's research activities span the African continent with partnerships linking research organizations, not only across Africa, but also the globe. In addition, more than 100 graduate students and a number of postdoctoral fellows contribute to *icipe*'s research portfolio annually. For more information visit: www.icipe.org

Main Responsibilities:
- Prepare payments by verifying documentation and ensure that payments have proper authorization and supporting documents;
- Process advance liquidation or expense recording after the receipt of the original invoices and relevant documents by verifying the supporting documents presented are appropriate, sufficient and in line with the policy;
- Control bank account balances and report when the balance is low so as to take the necessary action before checks are written;
- Verify cheque payments, handle cheque books and vouchers with due care and in safe places;
- Prepare financial reports, bank reconciliation and cash book records, and organize the supporting documents in the manner required;
- Prepare weekly cash position report including forecasted project expenditure;
- Ensure the availability of sufficient cash at the bank and liaise with *icipe* HQ for transfer of operating cash to the *icipe* Ethiopia office;
- Ensure that payment commitments are honored on time;
- Check the accuracy and compliance of petty cash expenditure and its timely replenishment;
- Review monthly charges from ILRI, assign proper budget codes and ensure monthly financial reports are submitted to HQ on time with sufficient and appropriate supporting documentation;
- Liaise with *icipe* HQ and ILRI regarding financial and accounting related matters;
- Assist with the facilitation to annual and external audits;
- Assist with the preparation of operational budgets;
- Perform other duties as requested.

Education:
- BA degree in Accounting
- Accounting certification is an added advantage

Experience:
- At least five years of relevant experience in an international organization or NGO.

Skills:
- High computer knowledge (Microsoft Word, Excel, Access and Accounting software)
- Good written and oral communication in English language
- Integrity and capacity to keep confidential information
- Ability to organize work and archives efficiently
- Ability to work under pressure
- Ability to work in a multi-cultural organization
- Knowledge of ABW-OCS is an added advantage

Duty Station: Addis Ababa, Ethiopia.

Position level: 2C.

Minimum Base salary:
- **Birr 16,619 per month** (Negotiable depending on experience, skill and salary history of the candidate)

Terms of appointment: Initial appointment is for **three years** renewable appointment based on performance and funding availability. ICIPE offers a multicultural, collegial research environment with competitive salary and excellent benefits in line with ILRI salary scale applicable for its Nationally Recruited Staff. ICIPE is an international and equal opportunity organization and believes that diversity of its staff contributes to excellence.

Applications: Applicants should provide a cover letter and curriculum vitae; names and addresses (including telephone and email) of three referees who are knowledgeable about the candidate's professional qualifications and work experience to be included in the curriculum vitae. The position and reference numbers should be clearly indicated in the subject line of the cover letters. All applications to be submitted online on our recruitment portal: http://ilri.simplicant.com/ on or before **19 December 2016.**

To find more about *icipe* , visit our Website at http://www.icipe.cgiar.org
More ILRI jobs
Subscribe by email to ILRI jobs alert

Oxfam GB

Invitation to Open Tender

PROVISION OF GENERATOR and SUMERSABLE PUMPS.

Tender No. OXGB/ETADD/2016/0016

Oxfam GB is a UK based International Humanitarian and Development Organization working in Ethiopia since the 1960s. Oxfam GB is looking for capable and reliable suppliers for the supply of the attached list of item to support its humanitarian response and development activities in Ethiopia. Thus, Oxfam GB is issuing this Invitation to Tender to invite all legitimate suppliers with relevant experience to take part in this tender.

No. Of Lots	Items description	Quantity
LOT 1	**Generator, Diesel, 33kVA, Canopy silencer, 3 phase**	2
LOT 2	**Pump, Submersible, 15kW, Phase 3,with complete accessory**	1
LOT 3	**Pump, Submersible, 2”, Dewatering , Electric without Generator**	1
LOT 4	**Pump kit, Submersible, 6”, 3 phase, 15kw, with complete accessories**	1

The chosen supplier(s) will be required to sign a contract agreement with Oxfam Addis Office to fulfil all Oxfam GB’s requirements for the above mentioned Items.

Interested suppliers are invited to collect the tender documents from Oxfam GB, Ethiopia Programme Addis Office, which is located in the address below. Suppliers are required to carefully read through the tender documents, make a note of the planned time table below, and return their responses by the close of business Wednesday, 28th December 2016 (3.00PM after noon) , Late bid offers will not be considered. We request contractors to sign the confirmation in Appendix A upon collection of the tender documents.

Oxfam GB Addis Ababa Office:

Oxfam GB
P. O. Box 2333, Kifle Ketema Bole, Kebele 08/09, House No. 1419
In front of Imperial Hotel/Adjacent to Hill Belt Restaurant
Addis Ababa, Ethiopia
Tel: +251-(0)-116-174155

Planned Timetable	
Issue ITT	7th December 2016
Deadline for reply	28th December 2016 (3.00PM after noon)
Bid Opening	29th December 2016
Evaluation of ITT	30th December 2016
Award of Contracts	05th January 2016

This invitation to tender has been issued for the sole purpose of obtaining offers for the supply of goods and/or services against the specification contained within the tender document. Oxfam GB reserves the right not to enter into or award a contract as a result of this invitation to tender. Oxfam GB also reserves the right to terminate any contract issued as a result of this ITT as set out in the contract terms and conditions. Successful tenders will be expected to enter into a formal contract with Oxfam GB, which will be supported by a Service Level Agreement.

- Oxfam GB reserves the right to alter the dates of the timetable.
- Oxfam GB does not bind itself to accept the lowest or any tender.
- Oxfam GB is in no way responsible for the cost of preparation of the tender response.

Please note that external packaging or envelopes must be WAX SEALED; and MUST NOT bear the name, or any markings, which may identify the bidding company or organisation.

The onus is on the supplier to ensure that their offer is complete and meets Oxfam GB’s requirements. Failure to comply may lead to the offer being rejected without any reason being given. Please therefore ensure that you read the tender document carefully and answer fully all questions asked.

Once this Invitation to Tender is announced on the local /National media, Oxfam GB will not be obliged to make any further announcements or communications using the same channel. Oxfam GB will only contact those bidders who have officially collected the tender documents from Oxfam GB’s Office. Hence, the onus is on the bidder to ensure that they have provided a legitimate and valid contact person and address of their organisation at the time of collecting the tender documents.

Habesha Cement Share Company

Immediate Vacancy Announcement

Habesha Cement S. Co. would like to invite qualified and competent applicants for the following vacant position:

1.Position: **Blaster**

Qualification: Technical Certificate(10+1)

Experience: 4 Years experience as Blasting Technician (Blasting Special License is required)

Term of Employment: Permanent
Duty Station: Goro Site

Work experience in Industry is advantageous

Salary: Negotiable and Attractive

Interested applicants who fulfill the above requirements can submit their application, CV and non- returnable photo copies of their testimonials in person to HRM, Office located at WelloSefer, Ethio-China Friendship Street, KASMA building 8th floor, in front of wengelawit building within 7 days after this vacancy announcement.

For further information use telephone No.011-833-41-94

Position: Apprenticeship Trainee - Industrial Electrician

Registration Date: from December 12, 2016 to December 16, 2016

Registration place: Ethiopian Airlines, Recruitment & placement Office.

Qualification Required

Minimum of Level III Certificate in *Power Generation and System Installation and Maintenance- Electrical Electronics /*Building Electrical Installation or related field from a recognized TVET/ College /Institute.

N.B:

- 2nd Grade or Automotive Driving License is Advantageous.
- Age limit up to 35 years.

Interested applicants must bring/attach all original and copy of their supporting documents, including 6th /8th Grade Ministry Card with copy & one passport size picture when they come/apply for registration/ online on Ethiopian Airlines Recruitment system on the appropriate dates stated above.

በኢዴፓ መግለጫ ላይ የተሠራው ዘገባ ይስተካከል

ኅዳር 18 ቀን 2009 ዓ.ም. በወጣው የጋዜጣችሁ ዕትም ‹‹መንግሥት ሕዝቡ ላቀረበው ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እንዳይነሳ ኢዴፓ አሳሰበ›› ተብሎ ተዘግቧል፡፡ በወቅቱ በእኛ በኩል የተገለጸው ‹‹መንግሥት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሊነሳ ነው እያለ ነው፡፡ ነገር ግን የሕዝቡ ጥያቄ ምላሽ እስካላገኘ ድረስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ቢነሳም ችግሩ ተመልሶ ሊፈጠር ይችላል እንጂ መፍትሔ ሊሆን አይችልም፤›› የሚል ነው፡፡

በወቅቱ ለዚህ አባባል ጋዜጠኞች የተዛባ ትርጉም እንዳይሰጡት በመሥጋት ‹‹የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አይነሳ እያልን እንደሆነ አድርጋችሁ እንዳትተረጉሙ፡፡ እኛ እያልን ያለነው ለችግሩ መፍትሔ የሚገኘው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ስለተነሳ ሳይሆን የሕዝቡን ጥያቄ በአግባቡ በመመለስ ነው፤›› በማለት ግልጽ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

ሌሎች በቦታው የነበሩ መገናኛ ብዙኃን ይህንን መልዕክት በትክክል የዘገቡት ሲሆን፣ በእናንተ በኩል ግን መልዕክቱ በተዛባ ሁኔታ ተገልጿል፡፡ በተለይ ደግሞ በተዛባ ሁኔታ እንዳይዘገብ ማሳሰቢያ የሰጡት አቶ ልደቱ አያሌው ሆነው እያለ፣ እሳቸው እንዲህ ዓይነት ማሳሰቢያ እንደሰጡ ሆኖ መዘገቡ ለምን እንደሆነ አልገባንም፡፡

ስለሆነም በተዛባ ሁኔታ ለሕዝቡ የተገለጸው ዜና ተስተካክሎ እንደገና እንዲዘገብ እንጠይቃለን፡፡

ግዛቸው አንማው፣ የኢዴፓ 7ኛ ጠቅላላ ጉባዔ
አዘጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ

የሰብዓዊ መብት…

ከገጽ 1 የዞረ

በዚህ ውይይት ላይ በርካታ ቁጥር ያላቸው አገር አቀፍና ክልላዊ ፓርቲዎች የተሳተፉ ሲሆን፣ በርካቶቹ የቀረበውን የድርጊት መርሐ ግብር ተግባራዊነት በመጠራጠር ጥያቄዎቻቸውን አቅርበዋል፡፡

ከጌዲዮ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት የተወከሉት አሌሳ መንገሻ፣ ‹‹ዛሬ ጥያቄው የተግባር ነው፤›› ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የመንግሥት የፖለቲካ ቁርጠኝነት በቃል እስከ ዛሬ ከተነገረው በላይ በተግባር እንዲሆን ይፈለጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ትዕግሥቱ አወሉ በበኩላቸው የድርጊት መርሐ ግብሩ የዘገየ ቢሆንም መዘጋጀቱን ተቀብለው አፈጻጸሙን በተመለከተ ግን፣ ‹‹የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሐ ግብር አፈጻጸም ምክር ቤት›› እንዲቋቋም ጠይቀዋል፡፡

የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሐ ግብሩ አጥጋቢ ሆኖ እንዳላገኙት የጠቀሱት ደግሞ ከሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ የተወከሉት አቶ ሉምባ ደምሴ ናቸው፡፡

የሰብዓዊ መብት ጥሰቱ በአጠቃላይ የሚመነጨው አገሪቱ ከምትከተላቸው ፖሊሲዎች መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ የኢኮኖሚ መብቶች ጥሰት የሚመነጨው አገሪቱ በምትከተለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ለማሳያነትም በድርጊት መርሐ ግብሩ ላይ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብትን በተመለከተ ቢታቀድም፣ ይህ ግን በኢትዮጵያ ሁኔታ ሊሳካ የሚችለው የመሬት ፖሊሲው መከለስ ሲችል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ዝግ የሆነ የመሬት ፖሊሲ ተይዞ የዜጎችን የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብት ለመመለስ መጣር የሚጋጭ ነው ብለዋል፡፡

‹‹ከሊዝ ነፃ ዜጎች መሬት የማግኘት መብት ሲያገኙ ነው የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብት የሚከበረው እንጂ ስለኮንዶሚኒየም በማቀድ አይደለም፤›› ብለዋል፡፡

የኦሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት ተወካይ የሆኑት አቶ ግርማ በቀለ በበኩላቸው፣ የድርጊት መርሐ ግብር ሰነዱን ሙሉ ለሙሉ እንዳነበቡት ጠቁመው፣ ‹‹የማነበው ግን ስለሌላ አገር ነው የመሰለኝ፤›› ብለዋል፡፡

አክለውም፣ ‹‹የምናወራው ስለሌላ አገር ካልሆነ በስተቀር በ150 ገጾች ተዘርዝሮ የቀረበውን የድርጊት መርሐ ግብር ሊያስፈጽም የሚችል ተቋም አለ ወይ?›› ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ‹‹የሲቪክ ማኅበራት በተዘጉበትና የዴሞክራሲ ተቋማት በተዳከሙበት፣ ነፃ ፕሬስ በሌለበት ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል ወይ?›› ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

ሌላ የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ በበኩላቸው፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል መሆን በራሱ ለሰብዓዊ መብት ረገጣ የሚዳርግ በመሆኑ በተጋላጭነት ከሚጠቀሱት ሴቶችና ሕፃናት ቀጥሎ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት የሚል እንዲካተትላቸው ጠይቀዋል፡፡

በውይይቱ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት የድርጊት መርሐ ግብሩ አፈጻጸም ክትትል ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ይበቃል ግዛው፣ ጠቃሚ የሚባሉትን ነጥቦች በሰነዱ ለማካተት እንደሚጥሩ አስረድተዋል፡፡

በፓርላማ የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ አስመላሽ ወልደ ሥላሴ በተመሳሳይ በርካታ ጠቃሚ ግብዓቶች ከውይይቱ እንደተገኙ ገልጸው፣ መታረም አለበት ያሉትንም ጠቁመዋል፡፡ ይኸውም በዋናው የውይይቱ አጀንዳ ላይ ሐሳብ ከመሰንዘር ይልቅ የፖለቲካ ክርክር ውስጥ መግባት የመፈለግ አዝማሚያ መቅረት እንዳለበት፣ ምክንያቱም ለፖለቲካ ክርክር ራሱን የቻለ መድረክ ያስፈልገዋል ብለዋል፡፡

የንግድ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ያዕቆብ…

ከገጽ 1 የዞረ

ሆነው ተሾሙ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ አቶ ያዕቆብን በአዲሱ ካቢኔያቸው ውስጥ ባያካትቷቸውም፣ ግዙፉን የሎጅስቲክስ ኢንተርፕራይዝ እንዲመሩ ሾመዋቸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አቶ ያዕቆብን ብቻ ሳይሆን፣ የትራንስፖርት ሚኒስትሩን አቶ አህመድ ሺዴ የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ኢንተርፕራይዝ ሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ አድርገው ሾመዋል፡፡

አቶ አህመድ ቀደም ሲል የትራንስፖርት ሚኒስትርና የቦርድ ሰብሳቢ የነበሩትን፣ በአሁኑ ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙትን ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁን ተክተዋል፡፡

አቶ ያዕቆብ ደግሞ ለአምስት ዓመታት የኢንተርፕራይዙ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የነበሩትን አቶ አህመድ ቱሳን ተክተዋል፡፡ አቶ አህመድ የኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ሆነው መሾማቸውን መዘገባችን ይታወሳል፡፡

የቀድሞው ዋና ዳይሬክተርና አዲሱ የቦርድ ሰብሳቢ ማክሰኞ ኅዳር 27 ቀን 2008 ዓ.ም. ከኢንተርፕራይዙ ሥራ አመራር ቦርድና ከማኔጅመንት አባላት ጋር ትውውቅና ምክክር ማድረጋቸውን ምንጮች ገልጸዋል፡፡ አቶ ያዕቆብ ግን ከአዲስ አበባ ውጪ ስለነበሩ አልተገኙም፡፡

አቶ ያዕቆብ ለበርካታ ዓመታት በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር ሠርተዋል፡፡ አቶ ያዕቆብ በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ምርቶች ግብይት ሚኒስትር ዴኤታ በመሆን ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ መንግሥት በዘርፉ ለውጥ ለማድረግ የግብርና ግብይቶች በንግድ ሚኒስቴር ሥር እንዲካሄድ ሲያደርግ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ ሆነው ሠርተዋል፡፡ በኋላም በንግድ ሚኒስትርነት ቆይተው፣ መንግሥት እንደ አዲስ ካቢኔውን ሲያዋቅር ቦታቸውን ለዶ/ር በቀለ ቡላን ለቀዋል፡፡

አቶ ያዕቆብ የሦስት ድርጅቶች ውህድ የሆነውን የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ኢንተርፕራይዝ ይመራሉ፡፡

የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ኢንተርፕራይዝ ዕቃ የማጓጓዝ አቅሙ በየጊዜው እያደገ ሲሆን፣ በ2008 ዓ.ም. 175 ሺሕ ኮንቴይነሮችን አጓጉዟል፡፡ በገቢ ደረጃም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 16.6 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡ ታውቋል፡፡

የአዲስ አበባ መሬት …

ከገጽ 3 የዞረ

ኃላፊ ሆነው ተሹመዋል፡፡

በአቶ ሰለሞን የአምስት ዓመታት የሥልጣን ቆይታ በአዲስ አበባ መሬት ዘርፍ በርካታ ሕጎች ወጥተዋል፡፡ በርካታ አመራሮችና ሠራተኞች ከሥራ ተሰናብተዋል፡፡

የተቀላቀለ ስሜት እየተንፀባረቀበት የሚገኘው የአዲስ አበባ ከተማ መሬት ዘርፍ አሁንም ከቅሬታ ነፃ መሆን አልቻለም፡፡ በአዲስ አበባ መሬት ሕገወጥ አሠራር ብቻ ሳይሆን ሙስና የተንሰራፋበት በመሆኑ፣ የከተማው ነዋሪዎች ባገኙት አጋጣሚ ቅሬታቸውን ሲያቀርቡ ቆይተዋል፡፡

መንግሥት ይህንን ችግር ለመቅረፍ በርካታ የመዋቅር ለውጥ ከማድረጉ በተጨማሪ፣ በርካታ ሕጎችን ሲያወጣ ቆይቷል፡፡ ዕርምጃን በሚመለከትም ከ600 በላይ አመራሮችና ሠራተኞች ላይ ዕርምጃ የወሰደ ሲሆን፣ የተወሰኑት በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

አቶ ሰለሞን በመሬት ዘርፍ ችግር እንዳለ ያምናሉ፡፡ አቶ ሰለሞን ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ የአዲስ አበባ ከተማ በመሬት ዘርፍ ያለውን ችግር ለመፍታት ዘመናዊ አሠራር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

‹‹በመሬት ዘርፍ ያለውን ችግር ለመፍታት በርካታ ደንቦችንና መመርያዎችን አሻሽለን ወደ ሥራ አስገብተናል፡፡ ችግር ባለባቸው አመራሮችና ሠራተኞች ላይ ዕርምጃ ወስደናል፤›› ሲሉ አቶ ሰለሞን በሥልጣን ዘመናቸው ካከናወኗቸው ሥራዎች አንዱና ግንባር ቀደሙ የአሠራር ማሻሻያ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

ከዚህ ሥራ በተጨማሪ በተለይ በሊዝ አዋጁ በዋናነት መሬት የሚቀርበው በሊዝ ጨረታ በመሆኑ፣ በየወሩ በርካታ መሬቶች በጨረታ መቅረባቸውን በመልካም ጎን ይመለከቱታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በመልሶ ማልማት ሥራዎች በርካታ ቦታዎችን ነፃ በማድረግ ለግንባታ ያዘጋጁ መሆኑን አቶ ሰለሞን ገልጸው፣ ነገር ግን በመልሶ ማልማት ፕሮግራም የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ፈታኝ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

‹‹ከ600 ሔክታር በላይ መሬት በመልሶ ማልማት ፕሮግራም ነፃ አድርገናል፡፡ በማድረግ ላይም ነን፡፡ አሁን የሚታዩት ልማቶችም የዚህ ፕሮግራም ውጤቶች ናቸው፤›› ሲሉ አቶ ሰለሞን ገልጸዋል፡፡

አቶ ሰለሞን እንደሚሉት፣ በአጠቃላይ በዘርፉ ኪራይ ሰብሳቢነት (ሙስና) አለ፡፡ ችግሩ በአመራሮች ላይም ያለ ስለሆነ ከባድ ትግል ይጠይቃል ይላሉ፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ሲሉ ጉዳዩ ያለበትን ደረጃ አስረድተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ካቢኔያቸውን እንደ አዲስ ከመሠረቱ በኋላ ሚኒስትር ዴኤታዎችን በመሾም ላይ ይገኛሉ፡፡

ነገር ግን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ እስካሁን ሳይነካ ቀጥሏል፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ለውጥ ለማድረግ እየሠራ ነው፡፡ በቅርቡ በሚጠራው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አዳዲስ ሹመቶች ይፋ እንደሚደረጉ ምንጮች ጠቁመዋል፡፡

በአገር አቋራጭ…

ከገጽ 3 የዞረ

እንዲይዙና ወደሚፈልጉት ቦታ ለመጓዝ ሲያስቡም ከሳምንት በፊት ቲኬት እንዲቆርጡ የሚያስችላቸው እንደሆነ፣ የክፍያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሙኒር ዱሪ ተናግረዋል፡፡ ተሳፋሪዎች ክፍያ ለሁሉ በሚባሉ ወኪሎች አማካይነት ቲኬት እንዲያገኙ እንደሚደረግ፣ በሚሳፈሩበት ዕለትም የቀረጡትን ቲኬት ይዘው በመገኘት መሳፈር የሚችሉበት አሠራር መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ለተቆረጠው ቲኬት ትክክለኛነት የሞባይል አጭር የጽሑፍ መልዕክት በመላክ ጭምር ማረጋጫ በመላክ የሚሠራው ቴክኖሎጂ ከወዲሁ ሥጋት የፈጠረባቸው የቀድሞ ቲኬት ቆራጮች ሥጋት እንደገባቸውና ሥራቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ መግለጻቸው ታውቋል፡፡ ለሸገር ሬዲዮ ሥጋታቸውን የገለጹ ቲኬት ቆራጮች ስለቴክሎጂው ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ቢናገሩም፣ አቶ ካሳሁን ግን ማንም ከሥራው እንደማይፈናቀልና ቴክኖሎጂውን ለመተግበር ሥልጠና መውሰድ የሚችሉ ሁሉ እንደሚካተቱበት አስታውቀዋል፡፡

አቶ ሙኒር በበኩላቸው እስካሁን 102 ቲኬት ቆራጮች የኤሌክትሮኒክ ቲኬትን የተመለከቱ ሥልጠናዎችን ለሁለት ሳምንት እንዲከታተሉ መደረጉን ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ…

ከገጽ 7 የዞረ

ኢኪዩፕመንት ኤንድ ቴክኖሎጂ ኩባንያ የለገሱት ቆጣሪ በናይጄሪያ ተሞክሮ የኃይል ማሠራጫ ብክነት ከነበረበት 46 በመቶ ወደ 11 ከመቶ እንዲቀንስ ማስቻሉ ተነግሮለታል፡፡ በተመሳሳይ የኃይል ፍጆታን ለመለካት ከሚደረገው ቆጠራ አኳያም በአማካይ ከ53 በመቶ ያላነሰ ብክነት ይታይ እንደነበርና ይህም ወደ 9.2 ከመቶ እንዲቀንስ ማስቻሉ ተነግሮለታል፡፡

በኢትዮጵያ በጠቅላላው የሚታየው የኃይል ብክነት መጠን 20 በመቶ እንደሚገመት የገለጹት አቶ ጋሻውበዛ፣ በአሜሪካው ማኬንዚ ኩባንያ አማካይነት እየተካሄደ ያለው ጥናት የብክነት መጠኑ ምን ያህል እንደሚሆን በተጨባጭ ሊያረጋግጠው እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በአሁኑ ወቅት 2.5 ሚሊዮን ደንበኞች እንዳሉት የገለጹት የአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጎሳዬ መንግሥቴ፣ ይህ ቁጥር ከአምስት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሰባት ሚሊዮን ሊደርስ እንደሚችል አስረድተዋል፡፡ ይሁንና በኃይል ሥርጭት፣ በአቅርቦት መጓደልና በተደጋጋሚ መቆራረጥ ምክንያት ከፍተኛ ቅሬታ የሚቀርብበት በመሆኑም የደንበኞችን ዕርካታ ለማምጣት ዘመናዊ የቆጣሪ ቴክኖሎጂዎችን ጨምሮ ሌሎችም ማሻሻያዎችን ተግባራዊ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል፡፡

ከቻይና ኩባንያዎች በተጨማሪ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን፣ እንዲሁም አገር በቀሉ ዲቨንተስ ኩባንያ ዘመናዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ቆጣሪዎችን ገበያ ላይ ለማዋል ሙከራ በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡

የዓለም ባንክ…

ከገጽ 1 የዞረ

አቶ ዮሐንስ የምንዛሪ ማሻሻያው በሁሉም መንገድ ቢታይ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ያምናሉ፡፡ ‹‹ከዚህ በፊት የተወሰደውን የምንዛሪ ማሻሻያ ተከትሎ የተቀሰቀሰውን የዋጋ ግሽበት ማስታወስ ያስፈልጋል፤›› ያሉት አቶ ዮሐንስ፣ ‹‹የረጅም ጊዜ ጉዳቱ በግልጽ ከአጭር ጊዜ ጥቅሙ የማይበልጥ ፖሊሲን አንተገብርም፤›› ብለዋል››፡፡

የኧርነስት ኤንድ ያንግ ማኔጂንግ ፓርትነር አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ በበኩላቸው፣ የምንዛሪ ማስተካከያ ማሳሰቢያው ተገቢ አይደለም ባይ ናቸው፡፡ በስብሰባው ላይ አቶ ዘመዴነህ በሰጡት አስተያየት ባንኩ ይህንን ዓይነት ምክር ሲያቀርብ ይህ ‹‹ለሁለተኛ ወይም ለሦስተኛ›› ጊዜው መሆኑን፣ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የግብርና ምርቶች ወደ ውጭ በመላክና የካፒታል ዕቃዎች በማስመጣት ላይ የተመሠረተ የወጪ ንግድ ሥርዓት ላላቸው አገሮች የምንዛሪ ማሻሻያ ተገቢ ፖሊሲ አይመስለኝም ብለዋል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2010 መስከረም ወር ላይ የተደረገው አጠቃላይ የምንዛሪ ለውጥ የብር ምንዛሪን በአንድ ጊዜ በ20 በመቶ ገደማ እንዲቀንስ ያደረገ መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡ በወቅቱ ብር ከዶላር ጋር የነበረው የምንዛሪ ምጣኔ ከ13.80 ወደ 16.35 ከፍ እንዲል የተደረገ ሲሆን፣ ይህንን ውሳኔ ተከትሎ አገሪቱ ለተከታታይ ሁለት ዓመታት ያህል በሁለት አኃዝ የዋጋ ግሽበት ስትታመስ እንደከረመች የሚታወስ ነው፡፡

እንደ ሚስተር ማይክል ገለጻ ከሆነ ግን፣ እ.ኤ.አ. በ2010 የምንዛሪ ማስተካከያ ማግሥት ግሽበት ተከስቶ ስለነበር ብቻ የምንዛሪ ማስተካከያን እንደ አማራጭ ፖሊሲ ውድቅ ማድረግ ብልህነት አይደለም፡፡ ‹‹የምንዛሪ ማስተካከያው በምን ዓይነት ከባቢያዊ ሁኔታ ነው የሚከናወነው የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት፤›› ያሉት ሚስተር ማይክል፣ የ2010 የምንዛሪ ማስተካከያ በተካሄደበት ጊዜ የዓለም አቀፍ የሸቀጦች ዋጋ ጣራ የነካበት ወቅት ነበር፡፡ የባንኩ ኢኮኖሚስት፣ ‹‹ነገር ግን አሁን ያለንበት ነባራዊ ሁኔታ የተለየ ነው፤›› ብለዋል፡፡

‹‹የዓለም አቀፍ የሸቀጦች ዋጋ በእጅጉ ያሽቆለቆለበት ጊዜ እንደመሆኑ መጠን፣ የምንዛሪ ማስተካከያው የተፈራውን ያህል የዋጋ ግሽበት መቀስቀስ እንደማይችል ግልጽ ነው፤›› ብለዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የባንኩ ሪፖርት የምንዛሪ ማስተካከያ ማድረግ፣ በተለይ እንደ ቻይና ያሉ አገሮች አሁን ኢትዮጵያ ባለችበት አቋም ላይ ሆነው የተጠቀሙበት የወጪ ንግድ ማበረታቻ መሣሪያ መሆኑን ያትታል፡፡ በዚህ መሠረት በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ብር ከዶላር ጋር ያለው የምንዛሪ ምጣኔ ከእውነተኛው የኢኮኖሚ አቅም አንፃር ሲታይ ከ70 በመቶ ያላነሰ የተቆለለ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል በአሁኑ ወቅት የአንድ በመቶ የምንዛሪ ማስተካከያ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ቢያንስ የ1.06 በመቶ ወጪ ንግድ መሻሻልን፣ በአገልግሎት ዘርፍ እንዲሁ የ0.5 በመቶ መሻሻልንና በግብርና ምርቶች ዘርፍ ደግሞ የ0.3 በመቶ የወጪ ንግድ ዕመርታ ሊያመጣ እንደሚችል ሪፖርቱ በጥልቀት ዳሷል፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ የባንኩ ዓመታዊ ጥናት ባለፈው ዓመት የስምንት በመቶ ዕድገት ያሳየው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በተለይ ከነበረው የድርቅ ሁኔታ አንፃር በእጅጉ አበረታች መሆኑን ያትታል፡፡ ‹‹በከፋ ድርቅ ወቅት ይህንን ያህል ዕድገት ማስመዝገብ በእጅጉ አበረታች ነው፤›› ያለው ሪፖርቱ፣ ከዕድገቱ ባሻገር ሌሎች የማክሮ ኢኮኖሚ መለኪያዎችም የኢኮኖሚውን ተፅዕኖ የመቋቋም ጥንካሬ ያሳዩ ናቸው ብሏል፡፡

በነጠላ አኃዝ የተገደበ የግሽበት ምጣኔ ከድርቅ ጋር ተያይዞ የሚከሰት የእህል ዋጋን መጨመር ሥጋት የተቋቋመ ነበር ያለው ሪፖርቱ፣ የድርቅ ተጠቂዎችን ከመርዳት ጋር ተያይዞ በእጅጉ የጨመረው የመንግሥት ወጪ አጠቃላይ የበጀት ጉድለቱን ያለማባባሱም ሌላው የሚደነቅ ክስተት ነው በማለት አወድሷል፡፡

ሰሞኑን…

ከገጽ 3 የዞረ

ሥራ እያከናወኑ መሆኑን አቶ መስፍን አስረድተዋል፡፡

ኩባንያዎቹ ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ የገቡ በመሆናቸው መንግሥት መስመር የመቀየርና አቅም የማሳደጉን ሥራ በተያዘው የበጀት ዓመት እንዲያጠናቅቁ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ይጠናቀቃል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ አንዱ ኩባንያ (ፓወር ቻይና) ዘግይቶ በመጀመሩ ወደ 2010 ዓ.ም. ሊተላለፍ ይችላል የሚል ግምት ቢኖራቸውም፣ ዋና ዋና ሥራዎቹን ግን በዚህ ዓመት ሊያጠናቅቅ እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

የመስመር ዝርጋታውና አቅም የማሳደጉ ሥራ ሲጠናቀቅ፣ የኃይል መቆራረጥም ሆነ ሌሎች ችግሮች ሊቀረፉ እንደሚችሉ አቶ መስፍን አስረድተዋል፡፡

ሰሞኑን የደረሰው መቆራረጥ ከኃይል አቅርቦት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለው የገለጹት ሥራ አስፈጻሚው፣ የተፈጥሮ አደጋ መሆኑን ደንበኞች ተረድተው አስፈላጊው ጥገና እስከሚደረግ እንዲታገሱ ጠይቀዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ 25 የማሠራጫ ጣቢያዎች መኖራቸውን የገለጹት አቶ መስፍን፣ በ126 ዋና መስመር ተሸካሚ ምሰሶዎች ከማሠራጫ ጣቢያዎቹ የሚወጣው ኃይል በሁሉም የከተማው አካባቢዎች ተሠራጭቶ ተደራሽ እየሆነ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም ከ30 በላይ የሚሆኑ መስመር ተሸካሚ ምሰሶዎች በመገርሰሳቸው፣ በበርካታ አካባቢዎች የኃይል መቆራረጥና መጥፋት መከሰቱን አረጋግጠዋል፡፡ ይህንን ችግር ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት በከፍተኛ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን አክለዋል፡፡

የቻይና ኩባንያዎች ከዓለም ባንክ፣ ከነዳጅ አቅራቢ አገሮች (OPEC) እና ከቻይና ኤግዚም ባንክ በተገኘው ከ260 ሚሊዮን ዶላር በላይ ብድር ግንባታዎቹን እያፋጠኑ መሆናቸው ታውቋል፡፡

የቀድሞ የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ ፕሬዚዳንት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኑ

አቶ ኃይለ እየሱስ በቀለ

በዳዊት ታዬ

የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር ከመዋሃዳቸው በፊት የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ ፕሬዚዳንት በመሆን ሲያገለግሉ የነበሩት አቶ ኃይለ ኢየሱስ በቀለ፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው መሰየማቸው ተገለጸ::

ምንጮች እንደገለጹት የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲዋሀዱ አቶ ኃይለ ኢየሱስ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የፋይናንስ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ለወራት ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ፣ ኃላፊነታቸውን ለቀው በሥራ ገበታ ላይ እንዳልነበሩ ምንጮች ገልጸዋል::

ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ምክትል ፕሬዚንዳትና አማካሪ ሆነው እንዲያገለግሉ መሰየማቸውን ለማወቅ ተችሏል:: አቶ ኃይለ ኢየሱስ ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ልማት ባንክን ለስምንት ዓመታት በፕሬዚዳንትነት የመሩ ናቸው::

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ መዋቅር ሁለት ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሲኖሩት፣ የአቶ ኃይለ ኢየሱስ ሹመት ባንኩ ሦስት ምክትል ፕሬዚዳንቶች እንዲኖሩት አድርጓል:: የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በቅርቡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ የነበሩት አቶ ጌታሁን ናና በፕሬዚዳንትነት እንደሰየሙለት ይታወሳል::

የትግራይ ክልል በርከት ያለ ምሁራን የተካተቱበት አዲስ ካቢኔ አዋቀረ

በዮናስ ዓብይ

የትግራይ ክልል ምክር ቤት በአብዛኛው የዶክተርነት ማዕረግ ባላቸው ምሁራን አዲስ ካቢኔ ለማዋቀር የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር ያቀረቧቸውን ዕጩዎች አፀደቀ::

ምክር ቤቱ እሑድ ኅዳር 25 ቀን 2009 ዓ.ም. በጠራው አስቸኳይ ጉባዔ ስድስት አዳዲስ የቢሮ ኃላፊዎችን ጨምሮ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል፣ እንዲሁም የክልሉን ዋና ኦዲተር ኮሚሽነር ሹመት ማፅደቁን ከክልሉ የኮሙዩኒኬሽን ቢሮ የተገኘው መረጃ አመልክቷል::

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ዓባይ ወልዱ ተሿሚዎችን ለምክር ቤቱ ሲያቀርቡ አራት ዋና ዋና መሥፈርቶችን በዝርዝር አስረድተዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ሕገ መንግሥቱን በማመን በቁርጠኝነት ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ዓላማ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂን በተመለከተ ሥልጠና የወሰዱ፣ በቂ ትምህርትና የሙያ ሥልጠና ዝግጅት ለተፈለገው ዘርፍ የሚስማማና የሚመች ልምድ ያላቸው፣ እንዲሁም ታማኝነትና ከሙስና የፀዱ መሆናቸው የመምረጫ መሥፈርቶች እንደሆኑ አስረድተዋል::

ለቢሮ ኃላፊነት የተመረጡት ስድስቱም ተሿሚዎች በዶክትሬት ማዕረግ የሚጠሩ ሲሆን፣ ለሌሎች ተቋማት የተመረጡ ተጨማሪ ሦስት ተሿሚዎች በተመሳሳይ ማዕረግ ላይ የሚገኙ መሆናቸው ታውቋል::

በአጠቃላይ 12 ተሿሚዎች ሹመታቸው ሲፀድቅ ሦስቱ በካቢኔው ውስጥ ቀድመው የነበሩ ሲሆኑ፣ በአዲሱ አወቃቀር የቢሮ ለውጥ ያደረጉ ናቸው ተብሏል:: ለቢሮ ኃላፊነት የተመረጡት ዶ/ር ኢንጂነር ገብረ መስቀል ካህሳይ (የትምህርት ቢሮ ኃላፊ)፣ ዶ/ር አትንኩት መዝገበ (የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ አንድ ዘርፍ ኃላፊ)፣ ዶ/ር ተስፉ ሚካኤል ገብረ ዮሐንስ (የውኃ ሀብት ቢሮ ኃላፊ)፣ ዶ/ር አብርሃ ኪሮስ (የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቢሮ ኃላፊ)፣ ዶ/ር የትምወርቅ ገብረ መስቀል (የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ) እና ዶ/ር

ወደ ገጽ 42 ዞሯል

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዘመናዊ የኤሌክትሪክ ቆጣሪዎችን ከቻይና ኩባንያዎች ተረከበ

95 ስማርት ሜትር ቆጣሪዎች በአዳማ ሙከራ ሊደረግባቸው ነው

በብርሃኑ ፈቃደ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የደንበኞችን የኃይል ፍጆታ መጠን ከመለካት ባለፈ የኃይል ሥርጭት ብክነትን፣ ብልሽትና ሌሎችም ሆን ተብለው በኃይል ማሠራጫዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን የሚያጋልጡ ዘመናዊ የኤሌክትሪክ ቆጣሪዎችን ከሁለት የቻይና ኩባንያዎች በዕርዳታ ተረከበ::

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በአገሪቱ ከሚያከናውናቸው የኤሌክትሪክ ኃይል ማሠራጫ መስመሮች ማሻሻያ ሥራ ጋር በተገናኘ በተለይ በአዳማ ከተማ ተገጥመው ሙከራ እንደሚደረግባቸው የሚጠበቁና ለቤት ውስጥ፣ ለንግድና ለኢንዱስትሪዎች መገልገያነት የሚወሉ 95 ዘመናዊ ሜትር ቆጣሪዎችን ከሁዋዌና ከቻይና ኤሌክትሪክ ፓወር ኢኪዩፕመንት ኤንድ ቴክኖሎጂ ከተባለው ኩባንያ ተበርክተውለታል::

የቻይና ስቴት ግሪድና የሁዋዌ ቴሌኮም ኩባንያ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዘመናዊ የቆጣሪ ሜትሮችን በገለሱበት ወቅት

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኢነርጂ ማኔጅመንት ኃላፊ አቶ ጋሻውበዛ አበራ ለጋዜጠኞች እንዳብራሩት፣ ከሁለቱ የቻይና ኩባንያዎች የተበረከቱት ዘመናዊ ቆጣሪዎች ከዚህ ቀደም ቤት ለቤት እየተዞረ ይደረግ የነበረውን የቆጣሪ ንባብ ሥራን ጨምሮ፣ ደንበኞች ለተገለገሉበት የኃይል መጠን ትክክለኛውን ሒሳብ እንዲከፍሉ፣ የተጠቀሙት ትክክለኛ የኃይል መጠን ምን ያህል እንደሆነ በተጨባጭ መረጃ አስደግፈው እንደሚሰጡ ይጠበቃል ብለዋል:: ከዚህም በተጨማሪ በኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና በአገልግሎት ሒሳብ አሰባሰብ ላይ የሚታዩ ብክነቶችን ጨምሮ ሌሎችም ጠቀሜታዎችን እንደሚያስገኙ የሚታሰቡት ዘመናዊ ቆጣሪዎቹ፣ በሁለት ወራት ውስጥ ሙከራ ተደርጎባቸው ውጤታቸው እንደሚታይ አቶ ጋሻውበዛ አስረድተዋል::

ሁዋዌ ኩባንያና ቻይና ኤሌክትሪክ ፓወር

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ማስታወቂያ


ABYSSINIA
INTEGRATED STEEL PLC
አቢሲኒያ ሪኢንፎርስመንት ባርስ
ለማንኛውም የግንባታ ሥራ የመጀመሪያ ምርጫ
Certified for
Grade: B500WR, B500DWR, B420WR, B400DWR, B350DWR
6ሚ.ሜ | 8ሚ.ሜ | 10ሚ.ሜ | 12ሚ.ሜ | 14ሚ.ሜ
16ሚ.ሜ | 20ሚ.ሜ | 24ሚ.ሜ | 30ሚ.ሜ | 32ሚ.ሜ
ምርቶቻችን
በተፈቀደላቸው
በሁሉም አከፋፋዮቻችን
ጋር ይገኛሉ
አድራሻችን
ቦሌ መንገድ ዳቢ ኮምፕሌክስ ሕንፃ 4ኛ ፎቅ አዲስ አበባ
ስልክ: 251 116 639 755, 251 116 635 122/25
ፋክስ: 251 116 639 756
ኢሜል: abysteel@ethionet.et
Design: Fractals Promotions & Communication +251 911 247 737

HEINEKEN

INVITATION OF BID

Heineken Breweries S.C would like to sell 3rd grade barley of 613 quintal found at different locations. The detail is found on the TOR.

Bid Opening Date:December 07, 2016

Bid Closing Date:December 15, 2016, at 5:00 PM

- Bidders shall submit their bid in a sealed envelope;
- Bidders shall submit Tax Identification Number(TIN) during submittal of bid documents;
- The bidders shall submit a bid bond to the value of **50,000 ETB** to the name of Heineken Breweries SC;
- The bid bond to the unsuccessful bidders shall be released within 10 working days after closing of the bid;
- The bid bond shall be released to successful bidder after signing of the contract and making full payment to the contract value;
- The successful bidders shall sign the contract within 10 working days after award notification, and failure to comply with this shall result in forfeiting of the bid bond;
- Bidders shall collect the document by paying **100.00 ETB non-refundable** up on receivingthe documents from the below address:

Reception desks at Head Office of Heineken Breweries SC,

Yezellalem Building (2nd floor),

In front of Africa Union

- Heineken Breweries SC reserves the right to accept or reject any or all bids at any time.
- It is possible to obtain further information from procurement unit of Heineken Breweries SC by telephone numbers:

T +251 (0) 11 4 70 30 20

M +251 (0) 926 75 54 79; M +251 (0) 911 892170;M +251 (0) 911 300888;

ባለአክሲዮን ለሆኑ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጎች የወጣ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ (Guideline) ቁጥር FIS/01/2016 መሰረት በባንኮች ወይም በመድን ድርጅቶች ውስጥ ባለአክሲዮን የሆናችሁ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጎች ያላችሁን የአክሲዮን ድርሻ ባላችሁ የአክሲዮን መጠን ልክ የሚደርሳችሁን ገንዘብ እንደዚሁም እ.ኤ.አ. እስከ ጁን 30 ቀን 2016 ድረስ ያለው የትርፍ ድርሻ እንድትሰበስቡ መመሪያ አስተላልፏል፡፡

በመሆኑም በወጋገን ባንክ አ.ማ. ውስጥ አክሲዮን ያላችሁ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆናችሁ የውጭ ዜጎች ይህ ማስታወቂያ በወጣ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ የአክሲዮን ሰርተፍኬታችሁን ለባንኩ በማስረከብ በአክሲዮናችሁ መጠን ልክ የሚደርሳችሁን ገንዘብ እንደዚሁም እ.ኤ.አ. እስከ ጁን 30 ቀን 2016 ድረስ ያለው የትርፍ ድርሻ መሰብሰብ እንደሚገባችሁ ከወዲሁ ያስታውቃል፡፡

ወጋገን ባንክ
የብልጽግናዎ አጋር

Wegagen Bank®
Your Partner in Development

[ክቡር ሚኒስትሩን ሾፌራቸው ከቤታቸው እየወሰዳቸው ነው]

- ምነው ክቡር ሚኒስትር?
- ምን ሆንክ?
- እንዴ ክቡር ሚኒስትር?
- ምንድን ነው የምትለው?
- ራስዎትን ተመልክተውታል?
- ሁሉም ራሴን እንደተመለከትኩ ነው፡፡
- ታዲያ እንዴት እንዲህ ያደርጋሉ?
- እኔ ምንም አላደረኩም፡፡
- ሸሚዝዎትን አይተውታል?
- ምን ሆነ ሸሚዜ?
- ታኝኮ የተተፋ ነው እኮ የሚመስለው፡፡
- ምን አልክ አንተ?
- ለጨዋታ ብዬ ነው፡፡
- ከእኔ ጋር የምን ጨዋታ ነው?
- ይቅርታ አልተተኮሰም ለማለት ነው፡፡
- እና በምኔ ልተኩሰው?
- ኧረ ክቡር ሚኒስትር ሠራተኛዋ ምን ሠርታ ትበላለች? እሷ ትተኩሰው እንጂ፡፡
- እኮ እሷስ በምኗ ትተኩሰው?
- እንዴ በካውያ ነዋ?
- መብራት ከጠፋ እኮ ሰነባበተ፡፡
- ምን?
- ይኸው ሦስት ቀን ሞላን፡፡
- እየቀለዱ ነው ክቡር ሚኒስትር?
- የምን ቀልድ ነው?
- ሚኒስትር እኮ ነዎት፡፡
- ብሆንስ ታዲያ?
- ብዙ የገባዎት አልመሰለኝም፡፡
- ምኑ ነው ያልገባኝ?
- ሚኒስትርነት፡፡
- ምን ማለትህ ነው?
- ክቡር ሚኒስትር አንድ ነገር ልንገርዎት?
- ምንድን ነው የምትነግረኝ?
- የቀድሞው አለቃዬን ያውቋቸዋል?
- የተነሱት ሚኒስትር?
- የተሾሙት በሉኝ እንጂ፣ ኢሕአዴግ መቼ ማንሳት ያውቃል?
- እ…
- ሲጀመር የእሳቸው ቤት መብራት ጠፍቶ አያውቅም፡፡
- እሺ፡፡
- ቢጠፋም ፋብሪካ የሚያንቀሳቅስ ጀነሬተር ቤታቸው አለ፡፡
- ምን?
- ምን ይኼ ብቻ?
- ሌላ ምን አለ?
- ከጥበቃቸው ጋር ሁሌ እንደተጣላን ነበር፡፡
- ለምን?
- እሱ ራሱ ዴኤስቲቪ ክፍሉ ተገጥሞለታል፡፡
- እ…
- በቃ ሁሌ ኳስ እያየ በር እንኳን አይከፍትልኝም፡፡
- ለምን እንደተባረሩ ገባኝ፡፡
- ክቡር ሚኒስትር ለምን እንደተሾሙ ገባኝ ማለትዎ ነው?
- እ…
- እሳቸው ቤት ቁርስ የበላሁ ዕለት ቀኑን ሙሉ ምግብ አልበላም ነበር፡፡
- ለምን?
- ቁርሱ ራሱ ድግስ በሉት፡፡
- አስገራሚ ነው፡፡
- እርስዎም ራሱ አስገራሚ ነዎት፡፡
- እንዴት?
- መብራት ጠፍቷል ሲሉኝ ነዋ፡፡
- ምን ላድርግ?
- እኔ ግን አንድ ምክር ልምከርዎት፡፡
- ምንድን ነው?
- በአግባቡ ይጠቀሙበት፡፡
- ምኑን?
- ሹመትዎን!

[ክቡር ሚኒስትሩ የቦርድ ሲቀመንበር ከሆኑበት አንድ የልማት ድርጅት ኃላፊ ጋር እየተወያዩ ነው]

- ክቡር ሚኒስትር ስለተገናኘን ደስ ብሎኛል፡፡
- ሥራ አይደለ እንዴ ምን ችግር አለው?
- የቀድሞውን ሚኒስትር ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡
- ለምን?
- በቃ ራሳቸውን የሚጠቅማቸው ነገር ከሌለ ወደዚህ ዝር ማለት አይፈልጉም፡፡
- ምን ታደርገዋለህ?
- ለነገሩ ምን ያድርጉ?
- እንዴት?
- እስር ቤት የሚገባቸው ሰውዬ ሹመት ነው የጠበቃቸው፡፡
- እ…
- ለማንኛውም ስለጨረታው እናውራ ብዬ ነው፡፡
- እሺ ምን ዓይነት ጨረታ ነው የሚወጣው?
- ሁለት ዓይነት ጨረታ ማውጣት እንችላለን፡፡
- ምንና ምን ዓይነት?
- ግልጽ ወይም ዝግ ጨረታ፡፡
- አሁን የተኛውን ዓይነት ጨረታ እናውጣ ታዲያ?
- እኔ ግልጽ ጨረታ ቢወጣ ባይ ነኝ፡፡
- ለምን?
- ዝግ ጨረታው ለሙስና በጣም ተጋላጭ ነው፡፡
- እንዴት?
- ያው ለዝግ ጨረታው የሚመረጡት ሰዎች አደገኛ ሙሰኞች ናቸው፡፡
- ስለዚህ ግልጽ ጨረታ ይደረጋ?
- አዎን ክቡር ሚኒስትር፡፡
- ዓለም አቀፍ ተቋማት ብቻ ይሳተፉ ወይስ የአገር ውስጦቹም ይኑሩበት?
- የአገር አቀፎቹም ቢኖሩ መልካም ነው፡፡
- አቅም አላቸው ግን?
- እሱን በውድድሩ ያሳዩ፡፡
- በቃ እንደዛው ይደረግ፡፡

[ክቡር ሚኒስትሩ ቢሮ ሲገቡ አማካሪያቸውን አገኙት]

- ሪፖርቱን እየሠራህ ነው?
- አዎን ክቡር ሚኒስትር፡፡
- ምን ያህል ገጽ ሠራህ?
- ገና ሁለተኛ ገጽ ላይ ነኝ፡፡
- ምን?
- ሥራ ስለሚበዛብኝ ነው እኮ፡፡
- የ50 ገጽ ሪፖርት እንደምፈልግ ታውቃለህ አይደል?
- ምን ችግር አለው? ከቀድሞው ሪፖርት ኮፒ ፔስት ማድረግ ነው፡፡
- እ…
- ከፈለጉም ከኢንተርኔት ኮፒ ማድረግ እችላለሁ፡፡
- ስማ ለሚኒስትሮች የሚቀርብ ሪፖርት እኮ ነው፡፡
- ምን ችግር አለው?
- አንተ በዚህ አቅምህ እንዴት ነው ከእኔ ጋር የምትሠራው?
- እኔ የምልዎት ጠዋት የት ሄደው ነበር ግን?
- የቦርድ ሲቀመንበር የሆንኩበት የልማት ድርጅት ስለሚያወጣው ጨረታ ለመነጋገር እዛ ነበርኩ፡፡
- አልሰሙም እንዴ?
- ምኑን?
- ጨረታው መሰረዙን?
- እ…
- ጨረታው እኮ የበርካታ ባለሥልጣናትን ቀልብ ስቧል፡፡
- እና?
- ተሰረዘ፡፡
- እንዴት?
- በአንድ የስልክ ጥሪ!

[አንድ ነባር ሚኒስትር ለክቡር ሚኒስትሩ ስልክ ደወሉላቸው]

- ተመስገን ነው ክቡር ሚኒስትር፡፡
- ምን ተገኘ?
- ስልክዎት ሠራ ብዬ ነዋ፡፡
- እምቢ ብሎ ነበር አይደል?
- በተደጋጋሚ ነበር የሞከርኩልዎት፡፡
- ውጭ ነበርኩ፡፡
- እሱማ ሰምቻለሁ ግን…
- ምነው?
- ማለት ገና ከመሾምዎት…
- ምን?
- ጉዞ አበዙ፡፡
- ለሥራ እኮ ነው የምሄደው፡፡
- ቢሆንም በየሳምንቱ የውጭ ጉዞ እንዴት ነው?
- በሪስፖርተርነቴ አይደለም እኮ እየሄድኩ ያለሁት፡፡
- እሱማ ይገባኛል፡፡
- አገር ወክዬ እኮ ነው የምሄደው፡፡
- ያው ዓይን ውስጥ እንዳይገቡ ብዬ ነው፡፡
- ማለት?
- የሚባለው እኮ ሌላ ነው፡፡
- ምንድን ነው የሚባለው?
- ከአየር ላይ ነው እየመሩት ያለው እየተባለ ነው፡፡
- ምኑን?
- መሥሪያ ቤቱን፡፡
- ወሬኞች በላቸው፡፡
- ሌላም ነገር ተብለዋል፡፡
- ሌላ ምን?
- ክቡር ካፒቴን!

[ክቡር ሚኒስትር ቢሮ አንድ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኛ ገባ]

- ሰላም ክቡር ሚኒስትር፡፡
- ሰላም እንዴት ነህ?
- ጥሩ ሰው መሆንዎትን ሰምቻለሁ፡፡
- አመሰግናለሁ፡፡
- በርካታ ለውጦች ያመጣሉ ብዬ አስባለሁ፡፡
- ምንድን ነው የምትሠራው?
- ጠቅላላ አገልግሎት ላይ ነው የምሠራው፡፡
- ብዙ ዓመት ሠራህ?
- ጡረታ ለመውጣት አምስት ዓመት ነው የቀረኝ፡፡
- ቆይተሃላ?
- መሥሪያ ቤቱን በሚገባ አውቀዋለሁ፡፡
- እስቲ ንገረኝ?
- ሕይወቴን የነጠቀኝ መሥሪያ ቤት ነው፡፡
- እንዴት?
- የቀድሞው ሚኒስትር ግፈኛ ነበሩ፡፡
- ማለት?
- ሁሉም ባዶ ተስፋ ይሰጡኝ ነበር፡፡
- የምን ባዶ ተስፋ?
- ይኸው ይኼን ያህል አገልግዬ የኮንዶሚኒየም ቤት እንኳን የለኝም፡፡
- እሺ፡፡
- እሳቸው ግን ሁሉም የማያደርጉትን ነገር እንደሚያደርጉልኝ ያወሩልኝ ነበር፡፡
- ምን ታደርገዋለህ?
- ለራሳቸው ግን ቤት ሳይሆን ቤተ መንግሥት ነው የገነቡት፡፡
- ካልኖሩበት ምን ይጠቅማል ብለህ ነው?
- እኔ የመጣሁት እንደሳቸው እንዳይሆኑ ለመምከር ነው፡፡
- እንደሳቸው ምን እንዳልሆን?
- ክቡር ሙሰኛ!

[አንድ ደላላ ክቡር ሚኒስትር ቢሮ ገባ]

- ሰላም ክቡር ሚኒስትር፡፡
- ምን ፈልገህ መጣህ?
- ጉዳይ አለኝ፡፡
- የምን ጉዳይ?
- በርዎት ክፍት መስሎኝ፡፡
- ለአንተ ግን ክፍት አይደለም፡፡
- ረሱት እንዴ?
- ምኑን?
- የሰጡትን መግለጫ፡፡
- የምን መግለጫ?
- ለሁሉም ኢትዮጵያዊ በሬ ክፍት ነው ብለው ተናግረው ነበር፡፡
- እሱማ ክፍት ነው፡፡
- ታዲያ እኔ ላይ ለምን ይዘጉታል?
- ስማ ከሙሰኞች ጋር መሥራት አልፈልግም፡፡
- ክቡር ሚኒስትር ቢሰሙኝ ጥሩ ነው፡፡
- ምንድን ነው የምሰማው?
- የምሰጥዎትን ምክር፡፡
- ምን?
- አብረን እንብላ፡፡
- ውጣ ከዚህ፡፡
- ምን አጠፋሁ?
- ውጣልኝ፡፡
- በሬ ክፍት ነው ብለው?
- ለአንተ መከፈት ያለበት ሌላ በር ነው፡፡
- የምን በር?
- የእስር ቤት!

በጥልቀት መታደስ ጥልቀቱ ምን ድረስ ነው?

በየማነ ናግሽ

ቀደም ሲል ሕወሓት በኋላም በኢሕአዴግ ደረጃ ደርግን የተዋጋው ድርጅት በአገሪቱ ውስጥ አሉ ያላቸውን የዴሞክራሲና የብሔር ጥያቄዎች በጥልቀት የገመገመ ነበር፡፡ የድርጅቱ የውስጥ አወቃቀር ኮሙዩኒስታዊ ገጽታ ነበረው፡፡ ዴሞክራሲያዊነቱና ሕዝባዊነቱም የሚመነጨው ከማርክስምና ሌኒኒዝም ፍልስፍና በሚቀዳ አስተሳሰብ ነበር፡፡

ሕዝቡን ከጭቆና ነፃ ለማውጣት ታጋዩም አመራሩም የታጠቀው ዋና ስንቅም ሕዝባዊነትና መስዋዕት ለመሆን ዝግጁነትን ነበር፡፡

በ1966 ዓ.ም. አብዮቱ ከመፈንዳቱ በፊት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመንም ሆነ በደርግ ያልተመለሱ የማንነትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን ለመመለስም፣ ለዘመናት የቆየውን አሃዳዊ ሥርዓት አፍርሶ በፌዴራላዊ ሥርዓት የመለወጥ ፕሮጀክትን እንደ ዓላማ የተያያዘው ነበር፡፡

ይኼ በግራ ዘመም አተያይ የተተነተነው ችግርና መፍትሔ አስፈላጊነትን ጥያቄ ውስጥ የሚከት ዓለም አቀፋዊ የርዕዮተ ዓለም ትግል መብቃት አጋጠመ፡፡ በ1980ዎቹ ውስጥ ያበቃው የምሥራቁና የምዕራቡ ዓለም ርዕዮተ ዓለም ፍጥጫ ቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት እየተባለ የሚጠራው ነው፡፡

የ17 ዓመታቱ የትጥቅ ትግል የርዕዮተ ዓለም ግጭት አመላካች አልነበረም፡፡ ሥልጣኑ ያበቃው ደርግም ከአሸናፊው ከኢሕአዴግ ባልተናነሰ ማርክሲስታዊ ሥርዓት ነበር፡፡ ወደ ሥልጣን የመጣው አዲሱ ድርጅትም ራሱን ከዓለም ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማጣጣም ነበረበትና በከፊል የምዕራቡ ዓለም መመርያ የሆኑትን ነፃ ገበያ፣ ነፃ አስተሳሰብና የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት በመርህ ደረጃ ለመቀበል ተገዷል፡፡ የምዕራቡ ዓለም ድጋፍም ተችሮታል፡፡ ኢሕአዴግ ያልተቀበላቸው የዓለም ባንክና የአይኤምኤፍ የልማት መርሆች እንዳሉ ሆነው፡፡ ለብዙዎች የመጀመሪያው የድርጅቱ ህዳሴ መባል ያለበት ይኼው የርዕዮተ ዓለም ክለሳ ነበር፡፡ ዛሬም ከ25 ዓመታት በኋላ እነዚህ ጥያቄዎች በኢሕአዴግ ጠረጴዛ ላይ ናቸው፡፡

በፌዴራላዊ አስተሳሰብ የተዘጋጀው አዲሱ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ ስምምነት የተደረሰባቸው የሰብዓዊ መብትና የዴሞክራሲ ቃል ኪዳኖች ያካተተ፣ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ሕገ መንግሥት ፀድቆ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ተግባራዊነት ላይ ግን ጥያቄ ይነሳበታል፡፡

ከሕገ መንግሥቱ መረቀቅ በፊት ሥራ ላይ በዋለው የሽግግር መንግሥት ቻርተር ወቅት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ተሳትፎ ይገኝበታል፡፡ የራሱን አሻራም አሳርፏል፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ በቀደሙት ሥርዓቶች የማንነት ጭቆና ከደረሰባቸው መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡ ዛሬ ግን ሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ የቅቡልነት ጥያቄ ከተነሳባቸው ክልሎች ግንባር ቀደሙ ሲሆን፣ ባለፈው ዓመት ኅዳር ወር የተቀሰቀሰው አመፅ ለአንድ ዓመት መዝለቁ ይታወሳል፡፡ ቀጥሎም ሁለተኛው ትልቁ ክልል በሆነው ከአማራ ክልል ተመሳሳይ ሁከት ተቀስቅሶ ነበር፡፡

1993 እና 1997

በ1990 ዓ.ም. ከኤርትራ ወረራ በኋላ በተለይ ሕወሓት ውስጥ የተከሰተው ቀውስ ትልቁና ኢሕአዴግንም የነካ፣ በአጠቃላይ ለአዲሱ ሥርዓትም መነቃነቅ የፈጠረ ነበር፡፡ የትግራይ ክልል ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ ገብሩ አሥራትንና የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩትን አቶ ስዬ አብርሃን ጨምሮ፣ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር የነበሩ ከአሥር በላይ ሰዎች ከድርጅቱ እንዲወገዱ ምክንያት የሆነ መሰነጣጠቅ ነበር የተፈጠረው፡፡

በአሸናፊው (በቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ የሚመራ) አካልና ‹‹አንጃ›› ተብለው በተገለሉ ሰዎች መካከል ዛሬም ድረስ የመሰነጣጠቁ አጀንዳ ላይ ስምምነት የሌለ ቢሆንም፣ የኤርትራ ጉዳይና ሙስና ተደጋግመው የሚነሱ ነጥቦች ናቸው፡፡

በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው ቡድን ድርጅቱ የመበስበስ አደጋ እንደገጠመው ቦናፓርቲዝም በሚል ርዕስ ያቀረበው አጀንዳ ነበር፡፡ በአንጃነት የሚታወቁ ሰዎች ከድርጅቱ መውጣታቸውን ተከትሎ የታወጀው ህዳሴ አገሪቱ በልማት ወደፊት እንድትራመድ አስችሏል ተብሎ ይታመናል፡፡

የኢሕአዴግ ተቃዋሚዎች አብዮታዊ ዴሞክራሲ በመባል የሚታወቀው ሥርዓት ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር እንደሆነና ነፃ አስተሳሰብን አይፈቅድም በማለት በተደጋጋሚ ሲወቅሱ ነበር፡፡ በተለይ በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ዋዜማ የታወጀው የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሥርዓት በአገሪቱ ለተከታታይ ዓመታት ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያመጣ ቢሆንም፣ እሱን የሚመጣጠን የዴሞክራሲ ለውጥ አልመጣም ተብሎም ይተቻል፡፡

ኢሕአዴግን ከትጥቅ ትግል ጀምሮ የሚከታተሉ የምሥራቅ አፍሪካ የፖለቲካ ተንታኝ ፕሮፌሰር አሌክስ ዲዋል፣ ሥርዓቱ እምብዛም ውይይት ያልተደረገበትና በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ መሬት የወረደ ለድርጅቱ ባዕድ አካሄድ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ እሱም ብቻ ሳይሆን ልማታዊ መንግሥት በኢትዮጵያ እንደማይሠራ፣ እንዲያውም እስከዛሬ ድርጅቱ ያስመዘገበውን የኢኮኖሚ ዕድገት ይዞ እንዳይሄድ በማለት አሌክስ ዲዋል ከሪፖርተር ጋር በነበራቸው ቆይታ አስገንዝበዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በተደጋጋሚ ባደረጉት ንግግርና በተለይ ደግሞ የድርጅቱ ንድፈ ሐሳብ መተንተኛ በሆነው በአዲስ ራዕይ መጽሔት ተደጋግሞ እንደተተነተነው፣ ተቃዋሚዎች የሚያራምዱት የጥፋትና የከሰረ ፖለቲካ መሆኑን፣ ኢሕአዴግ ውስጥ ያለውን የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ በማሸነፍ ‹‹ልማታዊነት›› የበላይነት እንዲኖረው የተቀረፀ እንደሆነ ይከራከራሉ፡፡

ከሥርዓቱ መታወጅ ይያያዝ አይያያዝ በቂ ማረጋገጫ ባይገኝም በአገሪቱ በ1997 ዓ.ም. ምርጫ የታየው የዴሞክራሲ ፍንጭ ለሁለተኛ ጊዜ አልተደገመም፡፡ የምርጫውን ቀውስ ተከትሎ በተከታታይ የታወጁ የሚዲያ፣ የሲቪክ ማኅበረሰብና የፀረ ሽብር አዋጆች የአገሪቱን ፖለቲካ የማያፈናፍን አድርገውታል ተብሎ ይተቻል፡፡ በእርግጥ በሁለቱ ተከታታይ ምርጫዎች በተለይ ደግሞ ባለፈው ዓመት በተካሄደው አምስተኛ ዙር ምርጫ ኢሕአዴግና አጋሮቹ የፓርላማ መቀመጫዎችን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥረውታል፡፡

የታወጀው የልማታዊ መንግሥት ሥርዓት ስዊድን፣ ደቡብ ኮሪያና ቻይናን የመሳሰሉ አገሮችን በሞዴልነት የሚያስቀምጥ ሲሆን፣ በእነዚህ አገሮች አንድ ፓርቲ ከ30 እስከ 60 ዓመታት በአውራነት የቆየበትና ከፍተኛ የኢኮኖሚ ሽግግር መምጣቱ ይታወቃል፡፡ ተቃዋሚዎች ‹‹የአንድ ፓርቲ ሥርዓት›› በማለት የሚተቹት ቢሆንም፣ ኢሕአዴግ ‹‹ጤነኛና ምክንያታዊ›› ተቃዋሚዎች እስኪፈጠሩ ድረስ በ‹‹አውራ ፓርቲ›› ሥርዓት አገር የመገንባት ዓላማ እንዳለው ደጋግሞ ተናግሯል፡፡

ዴሞክራሲን የመገንባት ሒደት በተቃዋሚዎች ፓርላማ መግባትና አለመግባት እንደማይወሰን አቶ መለስ ይሞግቱ ነበር፡፡ ኢሕአዴግ በውስጡ የመከራከርና ሕዝብን የማሳተፍ ባህልና ስትራቴጂ እንዳለው በመናገር፡፡ በዋናነት ግን በተለይ አዲስ ራዕይ በሐምሌ - ነሐሴ 2001 ዓ.ም. ዕትሙ ‹‹የአመራር መተካካት በኢሕአዴግ›› በሚለው ዋና የትንተና ጽሑፉ፣ በመንግሥትና በድርጅት የአመራር መተካካት በትውልዶች የዱላ ቅብብል እንደሚሳካ ያትታል፡፡ ወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ‹‹ሥልጣን እለቃለሁ›› በማለት ለፋይናንሻል ታይምስ የተናገሩበት ጊዜ ሲሆን፣ የአመራር መተካካት የግለሰብ የፍላጎት ሳይሆን በተለይ በትጥቅ ትግል የነበረውን አመራር በአዲስ አመራር የመተካት መርህ የተቀመጠበት ጊዜ ነበር፡፡ በሌላ ዕትም እንደተተነተነው ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ብቻውን በራሱ አላስፈላጊ ማኅበራዊ ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችልና በዴሞክራሲያዊ ምርጫ አሸንፎ ሥልጣን ላይ የወጣውን የጀርመን የናዚ ሥርዓት በምሳሌነት ያስቀምጣል፡፡ በመሆኑም እንደ 1997 ዓ.ም. ሕዝቡ ቀይ ካርድ ከማሳየቱ በፊት የመበስበስ አደጋ ሳይመጣ በመተካካት መርህ ዴሞክራሲያዊ የአመራር ለውጥ መፍጠር፣ በልማታዊ መንግሥት እንደ አማራጭ መንገድ የተወሰደ ይመስል ነበር፡፡

ፕሮፌሰር ሬኔ ሊፎርት ይህንን የልማታዊ መንግሥትነት ሒደት በተነተኑበትና ‹‹Ethiopia's Crisis›› በሚል ርዕስ የኢትዮጵያን ያለፈው ዓመት ቀውስ በገመገሙበት ጥናታዊ ጽሑፍ አንድ ከፍተኛ የኢሕአዴግ አመራር አነጋግረው ያገኙት ምላሽ፣ ‹‹ኢትዮጵያ ወደ ካፒታሊዝም ሥርዓት ከመሸጋገሯ በፊት የብዙኃን አስተሳሰብ [የመድብለ ፓርቲ] ሥርዓት አንጫንም፡፡ የተለያዩ መደቦች ሲፈጠሩ ብቻ ራሳቸውን የሚወክል ፓርቲ ያቋቁማሉ፤›› ይላል፡፡ ‹‹ኢሕአዴግ እየተመኘ ያለው ልማትና ዴሞክራሲ በአንድ ጊዜ እንዲመጣ ሳይሆን፣ መጀመርያ ልማት ከዚያ ቀጥሎ ዴሞክራሲ ነው፤›› የሚል ድምዳሜ ያስቀምጣሉ ፕሮፌሰሩ፡፡

የቀውሱ አተያይ

ባለፈው ዓመት ኅዳር ወር ለአዲስ አበባና ለኦሮሚያ ልዩ ዞን ከተሞች የተዘጋጀውን የጋራ ማስተር ፕላን በመቃወም የተጀመረው አመፅ ለዘጠኝ ወራት ዘልቋል፡፡ ከኦሮሚያ ወደ አማራ ክልልም ተቀጣጥሎ ነበር፡፡ በአብዛኛው እኔ ነኝ ያለ መሪ ያልነበረው ይኼው ድንገተኛ ሁከት በማኅበራዊ ሚዲያ የሚመራና ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ አክራሪ የፖለቲካ ኃይሎችም እጃቸውን አስገብተውበታል ተብሎ በተደጋጋሚ ተነግሯል፡፡ የኋላ ኋላም ግብፅንና ኤርትራን የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ቁጥር አንድ ጠላት የተባሉ አገሮች እንደነበሩበትም በቂ መረጃዎች መገኘታቸው በስፋት ተገልጿል፡፡

ያም ሆነ ይህ መንግሥት ከመነሻው ጀምሮ የሁከቱን ምክንያት ወደ ውጭ ለመግፋት አለመሞከሩንና ከውስጥ የመነጨ ነው ብሎ እንደሚያምን ገልጿል፡፡ ከመነሻው ግን መንግሥት የተነሳውን ጥያቄ የቢሮክራሲ ማሻሻያ አድርጎ አይቶታል፡፡ ምናልባትም ቀደም ሲል በተለይ በመቐለው አሥረኛው የኢሕአዴግ ጉባዔ የመልካም አስተዳደር ዕጦት የሥርዓቱ አደጋ እየሆነ ነው ብሎ ከመቀበሉ፣ ከአስተዳደርና ከፍትሕ ዕጦት የመነጨ መሆኑን ከማመኑ በላይ ይዘላል ብሎ አላመነም ነበር፡፡ የሕወሓት ነባር ታጋዮችና ወታደራዊ አዛዦች ሌተና ጄኔራል ፃድቃን ገብረ ትንሳዔ (የቀድሞ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታ ማዦር ሹም)፣ እንዲሁም ሜጀር ጄኔራል አበበ ተክለ ሃይማኖት (የቀድሞ አየር ኃይል ዋና አዛዥ) ለረዥም ጊዜ ድምፃቸውን አጥፍተው ከቆዩ በኋላ፣ በተከሰተው ቀውስ ላይ የራሳቸውን አተያይ አስቀምጠው ነበር፡፡ ጉዳዩ የቢሮክራሲ ሳይሆን የሥርዓት ቀውስ መሆኑንና ይህንን የሚመጥን የሥርዓት ማሻሻያ እንዲደረግ መዋቅራዊ የመፍትሔ ሐሳቦች ሰንዝረዋል፡፡

ከመነሻው ከኢሕአዴግ የሐሳብ አመንጪ ሰዎች እምብዛም አወንታዊ ምላሽ ባያገኙም፣ ሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችም ተመሳሳይ ሐሳብ አቅርበዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የኢዴፓ መሥራችና የቀድሞ ሊቀመንበር (በአሁኑ ወቅት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል) አቶ ልደቱ አያሌው ችግሩ የሥርዓት ቀውስ ምልክት እንደሆነ፣ ድርጅቱ እሱን የሚመጥን የሥርዓት ማሻሻያ እንዲያደርግ ጠይቀው ነበር፡፡ በእርግጥ ጫፍ ድረስ ሄደው የሽግግር መንግሥት እንዲመሠረት የጠየቁ ሌሎችም ነበሩ፡፡

መታደስ እስከ ምን? ከማን ጋር?

ሁከቱ ከመነሳቱ በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የሚመሩት አዲሱ መንግሥት በተቋቋመ በመጀመሪያዎቹ ወራት፣ የመንግሥት የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል ያደረገው ጥናት ይፋ መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡ የሥርዓቱ ችግር በድርጅቱ ጉባዔ ከተገመገመው በላይ መሆኑንም ያመለክታል፡፡ እምብዛም ሳይቆይ ሁከቱ መነሳቱ ኢሕአዴግ ዕርምጃ ከመውሰዱ በፊት እንደተቀደመም በአንዳንዶች ተተንትኗል፡፡

ያም ሆነ ይህ በ2008 ዓ.ም. የተከሰተው ሁከት ኢሕአዴግ ሥልጣን በያዘ በ25 ዓመቱ ውስጥ ከፍተኛው ሆኗል፡፡ ሁከቱን በመደበኛ ሕግና ሥርዓት ከማስከበር በላይ በመሆኑም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እስከ ማወጅ ተደርሷል፡፡ አዋጁ ተፈጥሮ የነበረውን ቀውስ ማስቆም የቻለ ሲሆን፣ በአገሪቱ አንዣብቦ የነበረው በሰላም ወጥቶ በሰላም የመግባት ፍራቻን በማስተካከል የአገሪቱ ሰላም ቀድሞ ወደነበረበት መመለስ ችሏል፡፡ በዚህ መሀል አንድ ነገር እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ በመንግሥትና በገዥው ፓርቲ ውስጥ የአመራር ለውጥና ማሻሻያ ማድረግ፡፡

አዋጁ ከመታወጁ ቀደም ብሎ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ ለሁለቱም ምክር ቤቶች ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር፣ በመንግሥትና በድርጅቱ ውስጥ መሠረታዊ የአወቃቀር ለውጥ እንደሚደረግ ቃል ገብተዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ በገቡት ቃል መሠረት ኢሕአዴግ ለበርካታ ሳምንታት በዝግ ከፍተኛ ግምገማ አድርጓል፡፡ በተናጠልም አባል ▶

በ2007 ዓ.ም. መጨረሻ በትግራይ ክልል ዋና ከተማ መቐለ በተካሄደው አሥረኛው የኢሕአዴግ ጠቅላላ ጉባዔ ወቅት የአራቱ አባል ድርጅቶች ሊቀመናብርት ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ደመቀ መኮንን፣ አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ፣ አቶ ሙክታር ከድር (አሁን ከፓርቲ አመራር ተሰናብተዋል) እና አቶ ዓባይ ወልዱ

ድርጅቶቹ በየፊናቸው ከከፍተኛ አመራር ጀምሮ እስከ ታችኛው የአመራር እርከን ድረስ እየተገማገሙ ይገኛሉ:: ከአራቱ አባል ድርጅቶች መካከል ኦሕዴድ ነባር ሊቀመናብርቱን በማሰናበት አዳዲስ አመራሮች ከማምጣቱም በላይ፣ ምሁራንና የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ያልሆኑ ወደ ኃላፊነት በማምጣት ግንባር ቀደም ዕርምጃ መውሰዱ ይታወሳል:: ብአዴንም በብዙዎች እንደተጠበቀው ሊቀመናብርቱን ባያሰናብትም አዳዲስ ምሁራን ወደ ካቢኔ በማምጣት ማሻሻያ ማድረጉን አስታውቋል:: የፌዴራል መንግሥትም ካቢኔውን እንደ አዲስ በማዋቀር ከሚኒስትሮች መካከል ዘጠኙ ባሉበት እንዲቀጥሉ በማድረግ ለ21 አዳዲስ ሚኒስትሮች ሹመት ሰጥቷል:: የብዙዎችን ቀልብ የሳበው በርካታ የዩኒቨርሲቲ ምሁራን ወደ ከፍተኛ ሥልጣን መምጣታቸው ሲሆን፣ በብዙዎች ዘንድ ምሁራንን አያቀርብም ተብሎ በሚታማው በኢሕአዴግ ታሪክ እንደ አዲስ ምዕራፍ ታይቷል:: ተቃዋሚዎች ግን አሁንም ከአዲሱ ካቢኔ አዲስ ነገር እንደማይጠብቁ ይናገራሉ::

የኢሕአዴግ ዋናው መሥራች ሕወሓት ቀደም ሲል የአመራር መተካካት ማድረጉ ይታወሳል:: አሁንም በከፍተኛ አመራር ደረጃ ግምገማ ተካሂዷል:: በድርጅቱ ውስጥ ፀረ ዴሞክራሲያዊ አሠራር በከፍተኛ ደረጃ መስፈኑን ገምግሟል:: በመንግሥት ደረጃ በቅርቡ የተወሰነ የአመራር ለውጥ አድርጓል:: በኢሕአዴግ ደረጃ በቀረበው በጥልቀት የመታደስ ሰነድ መሠረት እየተገማገመም ነው:: የድርጅቱ መሥራችና አንጋፋ ታጋይ አምባሳደር ሥዩም መስፍን በቅርቡ ‹‹ውራይና›› ለተባለው የትግርኛ መጽሔት በሰጡት ቃለ መጠይቅ፣ ሕወሓት ከሙስናና ከፀረ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ጋር በተያያዘ ውስጡን መፈተሹን ተናግረዋል:: እስከ ዛሬ በተለይ ምሁሩን ያገለለ አካሄድና ነፃ አስተሳሰብን የማይፈቅድ መንገድ እንደነበር መተማመን ላይ መደረሱንም አስረድተዋል::

ካቢኔውን እንደ አዲስ ያዋቀረው ብአዴንም የኢሕአዴግን ሰነድ መሠረት አድርጎ ያለፉትን 15 ዓመታት የክልሉን ጉዞ መገምገሙን የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አለምነው መኮንን ለሪፖርተር ተናግረዋል:: በሰፋፊ መድረኮች ከማዕከላዊ ኮሚቴ ጀምሮ እስከ ወረዳና ዞን አመራሮች ድረስ እስካሁን ድርጅቱ አለኝ የሚላቸው 7,500 የሚደርሱ አባላት ተገማግመዋል::

ድርጅቱ አምስት ዋና ዋና ችግሮች ነቅሶ የለየ መሆኑንና በተለይ ደግሞ ፀረ ዴሞክራሲያዊነት፣ የሕዝቡን አንገብጋቢ ችግሮች አለማዳመጥ፣ የአባላቱ በመርህ የለሽ አመለካከትና በትምክህት የመለከፍንና ዘረኝነትን የመሳሰሉ ጉዳዮች ለይቶ ገምግሟል ብለዋል:: በአጠቃላይ ድርጅቱ ቀና ሲሆን ሊያመጣ የሚችለውን ለውጥ ያህል ድርጅቱ ሲበላሽ ምን ያህል የጥፋት ኃይል ሊሆን እንደሚችል ይናገራሉ:: ‹‹ለሥልጣን ያለው አመለካከትና አተያይ መዛባት›› የችግሮቹ ምንጭ አድርገውም ይመለከታሉ::

ዛሬም የ‹‹አፈጻጸም›› ችግር

አቶ አለምነው እንደሚሉት ኢሕአዴግ ግምገማ የጀመረው በአፈጻጸም ችግር ላይ እንጂ የሥርዓት ለውጥ ለማድረግ አልነበረም:: እንደ እሳቸው እምነት የልማታዊ መንግሥት ፍኖተ ካርታና እሱን ለማስፈጸም የተቀረፁ ስትራቴጂዎች አማራጭ የላቸውም:: አቶ አለምነው፣ ‹‹ያቃተን መስመሩን በተሟላ ሁኔታ ጨብጦና አምኖ የመፈጸም ችግር ነው:: ይኼ መስመር የኢትዮጵያ ሕዝቦች ወደ ብሩህ ጎዳና መርቷቸዋል፤›› ይላሉ:: ‹‹ይህንን መጣል ወደ ጨለማ የሚወስድ መንገድ መከተል ነው፤›› በማለት::

አቶ ሔኖክ ሥዩም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዕጩ ሲሆኑ፣ ከኢሕአዴግ የሚጠበቀው የአመራር መሻሻል እንጂ የአስተሳሰብና የመስመር ለውጥ አይደለም ሲሉ ለሪፖርተር ገልጸዋል:: ‹‹የሕዝቡ ጥያቄ የመንግሥት ለውጥ ነው ወይ?›› በማለት ጥያቄውን ራሳቸው ውድቅ ያደርጉታል::

ህዳሴ የማድረግ ዕቅድ ቀደም ሲል ተይዞ የነበረ እንጂ ሁከቱን ተከትሎ እንዳልመጣ የአቶ አለምነውን ሐሳብ አቶ ሔኖክ ይቀበላሉ:: ኢሕአዴግም ‹‹የመስመርና የርዕዮተ ዓለም ማሻሻያ ማድረግ ሳይሆን፣ የተያዘውን መስመር ለማስፈጸም የተስተካከለ ቁመና የለኝም፤›› የሚል መነሻ እንዳለው ያምናሉ:: የፓርቲውን አሠራርና አመራር ለመፈተሽና ብቃት ያለው አመራር ለመፍጠር የተሰጠውን ትኩረት ይቀበላሉ:: ጉዳዩ በዚህ ከቀጠለ በሕዝቡ የቀረበው ጥያቄ ምላሽ ያገኛል ብለውም ያምናሉ:: ኢሕአዴግና አባል ድርጅቶቹ የያዙት ‹‹በጥልቀት›› የመታደስ ዘመቻ አዝማሚያ፣ በፓርቲው ውስጥ ፍተሻ የማድረግና የማጥራት እንጂ የመርህና የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት አይመስልም::

‹‹የሕዝቡ ጥያቄና ቁጣ በፓርቲ የውስጥ መታደስ መልስ ያገኛል ወይ?›› የሚል ጥያቄ ከቀድሞ የሕወሓት መሥራችና አመራር እንዲሁም የዓረና ትግራይ ፓርቲ መሥራች አቶ ገብሩ አሥራት ይነሳል:: አቶ ገብሩ ህዳሴው የታለመለትን ዓላማ የማሳካት ሁኔታ እንዳለው ይቀበላሉ:: ሆኖም ‹‹ጊዜው የሚጠይቀው መታደስ ከሆነ›› የሚል ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣሉ::

በአንድ ወቅት በምሥራቅ አውሮፓ ከሶሻሊስት አስተሳሰብ ለመውጣት የተደረገው ‹‹ዙሪያ ምላሽ›› የአስተሳሰብ ለውጥ ፍሬያማ መሆኑ ይናገራሉ:: ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተው ቀውስ ኢሕአዴግ ከሚከተለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የመነጨ እንደሆነ ያስረዳሉ:: ‹‹ነፃ አስተሳሰብ አይቀበልም:: ተቃዋሚዎችን በጠላትነት የሚፈርጅ ነው:: ለመታደስ ከሆነ ከዚህ ዓይነት ርዕዮተ ዓለም መውጣት ያስፈልጋል፤›› ይላሉ:: በኢሕአዴግ ዘመን የመታደስ ፍንጭ የታየው በ1997 ዓ.ም. እንደሆነ የራሳቸውን ምልከታ ይገልጻሉ:: አሁንም አንድ ፍንጭ ብቻ ተመልክተዋል:: የምርጫ ሕጉን ለማሻሻል የተገባውን ቃል:: ሆኖም እንደ አቶ ገብሩ እምነት፣ መታደስ ሌሎች በርካታ ፓኬጆችን መያዝ ነበረበት:: ሙስናና ፀረ ዴሞክራሲ አስተዳደር ምንጩ የፖለቲካ ቀውስ ውጤት እንደሆኑ ያምናሉ:: ግምገማውንና የካቢኔ ለውጡንም በአወንታዊ ጎኑ ይመለከቱታል:: ‹‹አሁን ሕዝቡ እየጠየቀ ያለው ግን ከዚህ በላይ ነው:: ጥያቄዎቹ ከድሮ የተለዩ ናቸው፤›› ይላሉ:: በተለይ በተለያዩ አካባቢዎች ‹‹ኦሮሚያ ፈርስት፣ አማራ ፈረስትና ትግራይ ፈረስት›› የሚባሉ አዝማሚያዎች አደገኛ መሆናቸው በመግለጽ፣ ኢሕአዴግ ልብ ገዝቶ ሁሉንም ያካተተና የተፈጠረውን የመበታተን አዝማሚያ ተሻግሮ የሚሄድ መንገድ እንዲቀይስ ይጠይቃሉ::

ንቅናቄውን የአክራሪ ዳያስፖራ እጅ እንደተቀላቀለበት ቢያምኑም፣ በአጠቃላይ የሕዝብ ቁጣ መገለጫ መሆኑን አቶ ገብሩ ያስረዳሉ:: የአንድ ፓርቲ አገዛዝና (ሌጋሲ) የሚሉ አስተሳሰቦች እንዲቀሩ በመጠየቅ::

የኢዴፓ የቀድሞ ሊቀመንበር አቶ ሙሼ ሰሙ፣ ‹‹ጥያቄው ባህሪውን ቀይሯል›› በማለት ከአቶ ገብሩ ጋር ተመሳሳይ ምልከታ አላቸው:: በ1993 ዓ.ም. በተወሰነ ደረጃ ህዳሴ መካሄዱን ግን ያምናሉ:: ላለፉት አሥራ አምስት ዓመታት እየተንከባለሉ እዚህ የደረሱት የኑሮ ውድነትና የፍትሕ ዕጦት ጥያቄዎች በተለመደው አካሄድ አይፈቱም ይላሉ:: ‹‹ህዳሴው የፓርቲ የውስጥ ጉዳይ እንጂ የሕዝብ አይደለም:: ጥያቄው ግን የመነጨው ከሕዝብ ነው፤›› በማለት ጥልቅ ውይይት የሚያስፈልገው ከሕዝብ ጋር ነው ይላሉ:: ቀጥተኛ ውይይት በማድረግና የሕዝቡን ጥያቄ በማዳመጥ ብቻ መፍትሔ ይኖራልም ይላሉ:: ‹‹ተሃድሶ ዕድሜ ማራዘሚያ እንዳይሆን›› በማለት እንኳን ራስን በራስ በማደስ፣ የተነሳውን ጥያቄ ከተቃዋሚዎች በመነጋገር ብቻም አይፈታም ይላሉ:: ‹‹ጉዳዩ ከውክልና ወጥቷል፤›› በማለት::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በካሪኩለም የዶክትሬት ዕጩ የሆኑት አቶ አብረሃ ኃይለዝጊ በበኩላቸው፣ የተሃድሶው እንቅስቃሴ የተለየ ስሜት እንዳልፈጠረባቸው ይናገራሉ:: ‹‹በኢሕአዴግ ዘንድ እንደ ፋሽን አዳዲስ ቃላት መፍጠር የተለመደ ነው፤›› በማለት:: ‹‹አሁን የተለየ ችግር ተፈጥሯል›› የሚሉት አቶ አብረሃ፣ የድርጅቱ አዝማሚያ ግን ጥያቄውን ለመመለስ የሚያስችል የተለየ መንገድ እየፈለገ እዳልሆነ ይናገራሉ::

‹‹አንደኛ ነገር መታደስ በዘመቻና በድንገት አይመጣም:: ሁለተኛ ከልብ መታደስም ቢፈልግ (ማን ይቀበላል) የሚል ጥያቄ ይነሳል:: በተደጋጋሚ ብዙ ንቅናቄ ለመፍጠር ቃል ተገብቷል:: ግን አላደረገም:: ጭብጡ ለውጥ የማይመጣ ከሆነ ማንም አያምንህም፤›› ይላሉ:: አቶ አብርሃ፣ ‹‹በ1993 ዓ.ም. የተደረገው ተሃድሶ ለዚህ ቀውስ ካደረሰን ሌላ ማራዘሚያ ተሃድሶ ለምን እናደርጋለን?›› ሲሉ ይጠይቃሉ::

አቶ አብረሃ በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች የተደረጉ የአመራር ለውጦችን በአወንታዊ መልክ ያዩዋቸዋል:: የተሃድሶ ምንጭ አድርገው ግን አይመለከቱዋቸውም:: ‹‹ለእኔ ተሃድሶ መሠረታዊ የሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ነው፤›› በማለት ከአቶ ገብሩና ከአቶ ሙሼ ጋር ይስማማሉ:: መደረግ ነበረባቸው የሚሉዋቸው ሕገ መንግሥቱን ማክበር፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን፣ እንዲሁም ሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱ የሰብዓዊ መብት ቃል ኪዳኖችን ማረጋገጥ ነበር:: ‹‹አሁን ጊዜ አልፎበታል›› የሚሉት መፍትሔ ሲሆን፣ ‹‹ዛሬ ኢሕአዴግ እጅግ ከሚያምነው ሕዝብ ሳይቀር እምነት አጥቷል:: ይኼ ቢደረግ የምለው መፍትሔ የለኝም፤›› በማለት በተስፋ መቁረጥ ሐሳባቸውን ይቋጫሉ::

ፕሮፌሰር ሬኔ ሊፎርት በኢትዮጵያ ታሪክ የመንግሥት ለውጥ የሚመጣው በገዥው አካል ውስጥ ያፈነገጠ አካል ሲኖር እንደሆነ በመግለጽ፣ የታሰቡ የተሃድሶ እንቅስቃሴዎች ዋናውን የችግሩን ምንጭ የሚነቅሱ ባይሆኑም፣ የቅቡልነት ጥያቄ ውስጥ እየገባ ቢሆንም የኢሕአዴግ ሥርዓት እንዲህ በቀላሉ አይፈርስም በማለት ይደመድማሉ:: ፕሮፌሰሩ በሁከቱ ወቅት በኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች ውስጥ በመዘዋወር የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማነጋገር ካገኙት መረጃ ድምዳሜ ላይ መድረሳቸውንም ገልጸዋል::

ንግድ ሚኒስቴር የንግድ ምክር ቤቶች የምርጫ ሕጋዊነት እንዲረጋገጥ አሳሰበ

በዳዊት ታዬ

ንግድ ሚኒስቴር የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ያካሄዷቸው ምርጫዎች ሕጉን ተከትለው የተካሄዱ መሆናቸው እንዲረጋገጥና የዘገየውም የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባዔና ምርጫም በዚሁ መሠረት እንዲካሄድ አሳሰበ፡፡

በሚኒስቴሩ የንግድና የአክሲዮኖች ዘርፍ ማኅበራት ጉዳዮች ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በአቶ ኑረዲን መሐመድ ተጽፎ የወጣው ደብዳቤ፣ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትና በተዋረድ የሚገኙ ምክር ቤቶች ሕጉን ተከትለው ምርጫ ማከናወናቸውን በቅድሚያ የማረጋገጥ ሥራ ከተሠራ በኋላ የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ምርጫና ጉባዔ እንዲካሄድ ጠይቋል፡፡

‹‹የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በተለያዩ ምክንያቶች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በማካሄድ ፕሬዚዳንትና የቦርድ አመራር አባላት ምርጫ ያላካሄደ መሆኑ ይታወቃል፤›› በማለት የሚጀምረው ይኸው ደብዳቤ፣ የምርጫ አሠራርና ደንብን ያልተከተሉ የአሳታፊነት ጉድለት የሚስተዋልባቸው ምርጫዎች በየደረጃው ተከናውነዋል ሲል ከዚህ ቀደም የቀረቡ አቤቱታዎችን ዋቢ አድርጓል፡፡

‹‹በተለይም ክልሎችና የከተማ አስተዳድሮች እንዲሁም ሌሎች አባል ምክር ቤቶች ምርጫ ሳያካሂዱ ወደ ቀጣዩ እርከን ነባር አመራር ይዘው የሚቀርቡባቸው ምርጫዎች እየተከናወኑ ነው በማለት የተለያዩ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች እየቀረቡ ይገኛሉ፤›› በማለት የሚጠቅሰው የሚኒስቴሩ ደብዳቤ፣ ለቅሬታዎቹ አስፈላጊው መፍትሔ እንዲሰጣቸው በማለት ምክር ቤቶችን ጠይቋል፡፡

በንግድ ምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 እንዲሁም ከምክር ቤቱ መተዳደሪያ ውጭ ከሁለት ጊዜ በላይ የተመረጡ የቦርድ አመራር አባላት አሉ ተብሎ የቀረበው ቅሬታና አቤቱታም አስፈላጊ መፍትሔ ሊሰጠው እንደሚገባ በማሰባሰብ ጉዳዩ እንዲጣራ ንግድ ሚኒስቴር ጽፏል፡፡

ሁሉም አባል ንግድና ምክር ቤቶች በአዋጁና በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት በየደረጃቸው በሕጋዊ መንገድ ምርጫ ያላከናወኑ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ሌሎች አባል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ሕጉን ተከትለው ግልጽ፣ ፍትሐዊና አሳታፊ ምርጫ ስለማከናወናቸው የማረጋገጥ ሥራ እንዲሠራም አሳስቧል፡፡

የማጣራቱ ሥራ በየክልሉ ንግድ ቢሮዎች ድጋፍ ከተሠራ በኋላ የአገራዊ ንግድ ምክር ቤቱን መደበኛ ጉባዔና ምርጫ ማካሄድ እንደሚገባ የዳይሬክተሩ ደብዳቤ ጠቅሷል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት መስከረም መጨረሻ ላይ ጠቅላላ ጉባዔውን ለማካሄድ ይዞት የነበረውን መርሐ ግብር፣ የቦርድ አመራር አባላት ያጋጠሙኝ ችግሮች አሉ በማለት ምርጫና ጠቅላላ ጉባዔውን ማራዘሙ ይታወሳል፡፡

ተፈጠሩ ከተባሉ ችግሮች ውስጥ ሕግን መሠረት በማድረግ ከሥር ጀምሮ መደረግ የነበረባቸው ምርጫዎች ከሕግ ውጭ መከናወናቸው፣ በተደጋጋሚ በንግድ ምክር ቤቱ አመራር ቦታ ላይ ለመውጣት ሕግን ያልተከሉ ምርጫዎች ተደርገዋል የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባዔውን ለማካሄድ እንቅፋት ሆኑብኝ ያላቸውን እንዲህ ያሉ ችግሮች እንዲፈቱ ለማድረግ አጣሪ ኮሚቴ አቋቁሟል፡፡ ሰባት አባላት ያሉት ይህ ኮሚቴ ከሕግ ውጭ ተከናወኑ ያላቸውን ጉዳዮች ለማጣራት የሁለት ወራት ጊዜ ተሰጥቶታል፡፡ ኮሚቴው በሕወጥ መንገድ ተመረጡ የተባሉ የምክር ቤቶች አመራሮችን ጉዳይ የሚያይ ሲሆን፣ የደረሰበትን ውጤት ሪፖርት በማድረግ ጠቅላላ ጉባዔው እንዲካሄድ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ኮሚቴው በማጣራቱ ሥራ ወቅት አቤቱታ የቀረበባቸው ጉዳዮች እርግጥ ተፈጽመው ከተገኙ ዕርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ ሕገወጥ ምርጫ ተከናውኗል በማለት ንግድ ሚኒስቴር ድረስ አቤቱታ ከቀረበባቸው መካከል የኢትዮጵያ ዘርፍ ምክር ቤት፣ የአማራ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትና የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ይገኙባቸዋል፡፡

ከአቤቱታዎቹ መካከል በሚመሯቸው ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ከተቀመጠው መመርያ ውጭ ከስምንት ዓመታት በላይ በብቸኝነት ፕሬዚዳንት ሆነው የዘለቁ ግለሰቦች መኖራቸው አግባብ አይደለም የሚለው ሚዛን ደፍቷል፡፡

ከተሽከርካሪ የሚመነጭ በካይ ጋዝን ለመቀነስ የሚረዳ አዲስ ቴክኖሎጂ ቀረበ

በሻሂዳ ሁሴን

ከተሽከርካሪዎች የሚወጣውን የበካይ ጋዝ ልቀት በ80 በመቶ መቀነስ ይችላል የተባለና ጣልያን ሠራሽ ‹‹ሱፐርቴክ›› የተባለ ቴክኖሎጂ ሥራ ላይ ሊውል ነው፡፡ ቴክኖሎጂው የበካይ ጋዝ ልቀትን በመቀነስ፣ ብክለትን ከመቆጣጠር ባሻገር እስከ 12 በመቶ የነዳጅ ፍጆታን እንደሚቀንስ ተነግሮታል፡፡ ለአውቶሞቢሎች፣ ለሚሳብ ተሽከርካሪዎች፣ ለጭነት፣ ለአውቶብሶችና ለረዣዥም ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በነዳጅ ለሚሠሩ ጀነሬተሮች የሚያገለግል ሲሆን፣ የገበያ ዋጋውም ከ25 እስከ 100 ዩሮ እንደሆነ ታውቋል፡፡ በ30 አገሮች ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት ሱፐርቴክ ቴክኖሎጂን የሚያስመጣው ኢዙኬም ትሬዲንግ የተባለ አገር በቀል ኩባንያ ነው፡፡

አቶ አበዱላዚዝ ከማል የኢዙኬም ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ማኔጂንግ ዳይሬክተር

በመኪና የነዳጅ መያዣ ቋት (ሳልቫቲዮ) ውስጥ የሚገጠመው ይህ ቴክኖሎጂ፣ ጭስ ማውጫን የማፅዳት ባህሪይ እንዳለው፣ የካርቦን ዝቃጭን እንደሚቀነስ፣ ለሞተር የበለጠ ዕድሜን በመስጠት በየጊዜው የሚደረግን ጥገና እንደሚቀንስ ስለቴክኖሎጂው ገለጻ የሰጡት አቶ ዮሐንስ ወልደገብርኤል አስረድተዋል፡፡

የኩባንው ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ አብዱላዚዝ ከማል፣ ቴክኖሎጂው በተለያዩ የዓለም ክፍሎችና በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች ጥቅም ላይ መዋሉን ተናግረዋል፡፡ ቴክኖሎጂውን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ጣልያን አገር ከሚገኘው የምርቱ ባለቤት ኩባንያ ጋር በተናጠል መፈራረማቸውን፣ የገበያ ሽፋኑንም በምሥራቅ አፍሪካ በሚገኙ አገሮች ሁሉ ተደራሽ የማድረግ ዕቅድ መነደፉን ለሪፖርተር ገልጸዋል፡፡ በነዳጅ ለሚሠሩ ጀነሬተሮች ቴክኖሎጂው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሥራ ላይ እንደሚውል ገልጸው፣ ‹‹ቴክኖሎጂውን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ከባንኮች የውጭ ምንዛሪ ጠይቀናል፡፡ ገንዘቡ እጃችን ሲገባ ወደ አገር ውስጥ የማስገባቱን ሥራ እንጀምራለን፡፡ ከቀረጥ ነፃ እንድናስገባ ለመንግሥት ጥያቄ አቅርበናል፤›› ብለዋል፡፡ አቶ አብዱላዚዝ ይህንን የተናገሩት፣ እሑድ ኅዳር 25 ቀን 2009 ዓ.ም. በመንገድና ትራንስፖርት ባለሥልጣን ጽሕፈት ቤት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ወቅት ነበር፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲህ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ብቅ እያሉ ሲሆን ከዚህ ቀደም የጃፓን ሥሪት ቴክኖሎጂ በአሁኑ ወቅት በዓለም ትልቅ መነጋገሪያ የሆነውን የበካይ ጋዞች ልቀትን ለመቆጣጠር ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከፍተኛ የሆነው የበካይ ጋዝ ልቀት በኢንዱስትሪ ከበለፀጉት አገሮች የሚለቀቅ ሲሆን፣ እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ታዳጊ አገሮች የሚለቀቀው የበካይ ጋዝ መጠን ከሌሎቹ አንፃር ሲታይ እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ የበካይ ጋዝ ምንጭ ከሆኑት መካከል ትራንስፖርት አንዱ ነው፡፡ በአገሪቱ 30 በመቶ የሚሆነው የበካይ ጋዝ ልቀት ከተሽከርካሪዎች የሚወጣ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እ.ኤ.አ. በ2012 የወጣ ሪፖርት እንደሚያሳየው አዲስ አበባ ከተማ 4.8 ሚሊዮን ቶን ካርቦንዳይኦክሳድ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር ትለቃለች፡፡ ከዚህ ውስጥ 47 ከመቶ ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቅ ነው፡፡ ካለው የሕዝብ ብዛት አኳያ በአገሪቱ ያለው የተሽከርካሪ ቁጥር በእጅጉ አናሳ ነው፡፡

ከ90 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ በሚኖርበት አገር ውስጥ የተሽርካሪዎች ብዛት 708,000 ብቻ ነው፡፡ ይህንን ያህል ተሽከርካሪ ባለበት ሁኔታ ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቀው የበካይ ጋዝ መጠን ከሚጠበቀው በላይ መሆኑ በአብዛኛው በዕድሜ የገፉና ያረጁ ተሽከርካሪዎች በብዛት መኖራቸው አንዱ መንስዔ ሲሆን፣ የሚነጨው በካይ ጋዝ መጠንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ አሳሳቢ ሆኗል፡፡

ይህም ሆኖ በአገሪቱ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ የጥናት ሰነድ መሠረት ከፍተኛውን የበካይ ጋዝ የሚያመነጩት የግብርናና የደን ምንጣሮ ተግባራት ናቸው፡፡

አዲስ ባንክ 112 ሚሊዮን ብር ማትረፉን አስታወቀ

በዳዊት ታዬ

ከሌሎች የግል ባንኮች በተለየ አደረጃጀት የተለያዩ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን፣ የብድርና ቁጠባ ተቋማትን፣ ከ170 በላይ ዕድሮችንና የመሳሰሉትን ተቋማት በአክሲዮን ባለቤትነት ያቀፈው አዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ፣ በ2008 በጀት ዓመት ከታክስ በፊት 112.8 ሚሊዮን ብር ማትረፉን ገለጸ፡፡

ባንኩ ቅዳሜ፣ ኅዳር 24 ቀን 2009 ዓ.ም. ባካሄደው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ከታክስ በኋላ 85.4 ሚሊዮን ብር ማግኘቱንና ለመጠባበቂያ የሚያዘው ተቀናሽ ተሰልቶ የተጣራ ትርፉ 64 ሚሊዮን ብር መድረሱን አስታውቋል፡፡ የተጣራ ትርፉ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በ45.5 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡

የተመዘገበው ትርፍ በአክሲዮን የትርፍ ድርሻ መጠን ሲሰላ በአንድ አክሲዮን የሚደርሰው የትርፍ መጠን ጭማሪ ካሳዩ ጥቂት ባንኮች መካከል አንዱ አድርጎታል፡፡ ከዚህ አኳያ እያንዳንዱ አክሲዮን ያስገኘው ትርፍ 193 ብር ወይም 19.3 በመቶ ሆኗል፡፡ በቀደመው ዓመት የአንድ አክሲዮን የትርፍ ድርሻ 187 ብር ወይም 18.7 በመቶ ነበር፡፡ በሌሎች የባንክ አገልግሎቶች የተገኘውን ውጤት የሚያሳየው የባንኩ ዓመታዊ ሪፖርት፣ የባንኩ ተቀማጭ ገንዘብ በ2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ 1.7 ቢሊዮን ብር መድረሱን ነው፡፡ የባንኩ አስቀማጮች ቁጥርም በ45.6 በመቶ ዕድገት አሳይቶ 39,945 እንደደረሰ ጠቅሷል፡፡

አስቀማጮችን ለመሳብ በባንኮች መካከል ያለው ውድድር ከፍተኛ ከመሆኑ አንፃር ባንኩ ሊጠቀስ የሚችል ሥራ ቢሠራም፣ ካለው የብድር ፍላጎት አኳያ ሲታይ ግን ተጨማሪ ተቀማጭ ገንዘብ የማሰባሰብ ሥራ መሥራት እንደሚገባው የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ኃይለመለኮት ተክለጊዮርጊስ ባቀረቡት ሪፖርት ጠቅሰዋል፡፡

ባንኩ ለደንበኞች ያቀረበው የብድር መጠን በ37.5 በመቶ እንዳደገ የባንኩ ሪፖርት ጠቅሶ፣ በ2008 መጨረሻ ላይ የሰጠው የብድር መጠን 1.1 ቢሊዮን ብር ማስመዝገቡን አመላክቷል፡፡

ባለፈው በጀት ዓመት ባንኩ በዓለም አቀፍ የባንክ አገልግሎት ዘርፍ በጠቅላላው 69.3 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት ችሏል፡፡ የተገኘው ገቢ ከአጠቃላይ የባንኩ ገቢ ውስጥ 23.5 በመቶ ድርሻ ይዟል፡፡ የተገኘው ገቢ አበረታች ቢሆንም በአጠቃላይ በኢንዱስትሪው የተከሰተው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ተፅዕኖ እንዳሳደረበት የባንኩ ሪፖርት ሳይጠቅስ አላለፈም፡፡

የባንኩ ጠቅላላ ሀብት 2.5 ቢሊዮን ብር የደረሰ ሲሆን፣ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ46.6 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ የባንኩ አጠቃላይ ካፒታል (የተከፈለ ካፒታል፣ መጠባበቂያና ያልተከፋፈለ ትርፍ ታክሎበት) 636.5 ሚሊዮን ብር ማስመዝገቡን የሚያሳየው ሪፖርት፣ ይህም ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከነበረው 445.1 ሚሊዮን ብር ጋር ሲነፃፀር የ43 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡

ከባንኩ አጠቃላይ ካፒታል ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው የተከፈለ ካፒታል ነው፡፡ 516.4 ሚሊዮን ብር በማስመዝገብ ካለፈው ዓመት አኳያ የ41 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ በተጓዳኝ የባንኩ የባለአክሲዮኖች ቁጥርም በዓመቱ የ16 በመቶ ዕድገት በማሳየት 8,370 ደርሷል፡፡

በ2008 ዓ.ም. ባንኩ በጠቅላላው 294.8 ሚሊዮን ብር ገቢ አግኝቷል፡፡ ባለፈው ዓመት ከነበረው የገቢ መጠን ጋር ሲነፃፀር 42.1 በመቶ ዕድገት የታየበት እንደሆነም አዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ ይፋ አድርጓል፡፡ በበጀት ዓመቱ የሥራ አፈጻጸም ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ እንዲሁም በአገሪቱ ውስጥ የነበረው ድርቅ ያስከተለው ተፅዕኖ፣ በባንኮች መካከል የነበረው ከፍተኛ ፉክክርና የውጭ ምንዛሪ ዕጥረትም ፈታኝ ክስተቶች እንደነበሩ ባንኩ ገልጿል፡፡

ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ከወለድ አልባ አገልግሎት 1.25 ቢሊዮን ብር ተቀማጭ ሰበሰበ

በዳዊት ታዬ

ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ በወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ዘርፍ ዕድገት ማሳየቱንና ከዚህ ዘርፍ ተጠቃሚዎች ያሰባሰበው የተቀማጭ ገንዘብ መጠን 1.25 ቢሊዮን ብር መድረሱን ይፋ አደረገ፡፡

ባንኩ የ2008 በጀት ዓመት የሒሳብ ሪፖርቱን ቅዳሜ፣ ኅዳር 24 ቀን 2009 ዓ.ም. ይፋ ሲያደርግ እንደገለጸው፣ የወለድ አልባ የባንክ አገልግሎቱ ከወትሮው በተሻለ እያደገ መምጣቱንና በ2008 መጨረሻ ላይ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ቁጥርም 97,530 መድረሱን ገልጿል፡፡ በ2007 ዓ.ም. 55,960 የወለድ አልባ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እንደነበሩም አስታውሷል፡፡ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት እንዲተገበር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን መመርያ መሠረት በማድረግ ከሌሎች ባንኮች ቀድሞ አገልግሎቱን በመጀመር የሚጠቀሰው ኦሮሚያ ባንክ፣ በ2008 በጀት ዓመት ከወለድ አልባ የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብቻ ያሰባሰበው ተቀማጭ ገንዘብ በ43 በመቶ እንዳደገ ጠቅሷል፡፡ በ2007 በጀት ዓመት 873.7 ሚሊዮን ብር ከወለድ አልባ አስቀማጮች የተሰባሰበው ተቀማጭ ገንዘብ በ2008 መጨረሻ ላይ 1.25 ቢሊዮን ብር በመድረሱ በዚህ ዘርፍ ከፍተኛ የሚባል ዕድገት መመዝገቡን ያሳያል ተብሏል፡፡

ይህም ከጠቅላላው የባንኩ ተቀማጭ ገንዘብ ውስጥ ከወለድ አልባ ብቻ የተሰባሰበው መጠን 13 በመቶውን እንደሚይዝ ባንኩ አስታውቋል፡፡

ወለድ ከማይታሰብበት ተቀማጭ ገንዘብ ውስጥ 716 ሚሊዮን ብር ዋዲህ፣ 378 ሚሊዮን ብር ደግሞ አማና ተብለው በሚታወቁት የአገልግሎት ዘርፎች አማካይነት በባንኩ የተቀመጠ ገንዘብ ነው፡፡

ከወለድ ነፃ ተቀማጭ ገንዘብ ውስጥ ሥራ ላይ ለማዋል በተደረገው እንቅስቃሴም በወለድ አልባ የባንክ አገልግሎት አሠራር መሠረት 509 ሚሊዮን ብር ለተለያዩ ቢዝነሶች በብድር ተለቋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ሙረሃባ በተባለው የወለድ አልባ አሠራር መሠረት ፋይናንስ የተደረገበት ብልጫውን የያዘ ሲሆን፣ በሙረሃባ ለአገር ውስጥ ንግድ ፋይናንስ የተደረገው የገንዘብ መጠንም 123 ሚሊዮን ብር እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከዚህም ሌላ በወለድ አልባ አገልግሎት በኩል 23.9 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱንና በዚሁ የአገልግሎት ዘርፍ 57 ሚሊዮን ብር ገቢ እንደተሰበሰበም የባንኩ ሪፖርት ያመለክታል፡፡ ይህ አገልግሎት አዲስ ቢሆንም ከጅምሩ ተስፋ ሰጪ እንደሆነ ባንኩ ገልጿል፡፡ ከመደበኛው የባንክ አገልግሎት በተለየ ራሱን ችሎ የሚሠራበት ይህ ዘርፍ ፋይናንስ የሚደረግበት መንገድም እንደመደበኛው አገልግሎት ወለድ የሚጠይቅበት ሳይሆን፣ አዋጭ የሆኑ የንግድ መስኮች እየተመረጡ ለአገልግሎቱ በተፈቀዱ አሠራሮች መሠረት ያለ ወለድ ገንዘብ በብድር የሚሰጥባቸውን መንገዶች ይከተላል፡፡

የባንኩን የ2008 በጀት ዓመት አጠቃላይ እንቅስቃሴ በተመለከተ በቀረበው ሪፖርትም ከአጠቃላይ የባንኩ አገልግሎት ከታክስ በፊት 325 ሚሊዮን ብር ትርፍ ተመዝግቧል፡፡ በቀደመው ዓመት ከታክስ በፊት 293.9 ሚሊዮን ብር እንዳተረፈ ይታወሳል፡፡ የ2008 የተመዘገበው የተጣራ ትርፉም 248.3 ሚሊዮን ብር እንደሆነ የሚያመለክተው የባንኩ ሪፖርት፣ ከቀዳሚው ዓመት በ12 በመቶ ብልጫ ማሳየቱን ነው፡፡

የባንኩ አጠቃላይ ሀብትም በቀደመው በጀት ዓመት ከነበረበት 9.53 ቢሊዮን ብር በ18 በመቶ ጨምሮ 11.9 ቢሊዮን ብር መድረሱን፣ የተቀማጭ ገንዘብ መጠኑም (በወለድ አልባ አገልግሎት የተሰበሰበውን ጨምሮ) 17 በመቶ በማደግ 9.3 ቢሊዮን ብር ደርሷል፡፡ በ2008 ዓ.ም. የሰጠው የብድር መጠን በ2007 በጀት ዓመት ከነበረው አምስት ቢሊዮን ብር ጭማሪ አሳይቶ በ2008 መጨረሻ ላይ 5.7 ቢሊዮን ብር እንደደረሰ ባንኩ አስታውቋል፡፡ ይህ የብድር መጠንም በወለድ አልባ የባንክ አገልግሎቱ ፋይናንስ የተደረገውንም ያጠቃልላል፡፡

በ2008 በጀት ዓመት የተመዘገበው የገቢ መጠን ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ቢሊዮን ብር መድረሱን የባንኩ ሪፖርት ያሳያል፡፡ በቀደመው ዓመት 849.5 ሚሊዮን ብር እንደነበር የሚያስታውሰው የባንኩ ሪፖርት፣ በ2008 በጀት ዓመት ግን በ37 በመቶ አድጎ 1.2 ቢሊዮን ብር ደርሷል፡፡ ይሁን እንጂ የባንኩ ዓመታዊ ወጪ በ51 በመቶ ጨምሯል፡፡ በበጀት ዓመቱ ባንኩ በጠቅላላው 838.5 ሚሊዮን ብር ወጪ አድጓል፡፡ ይህ ወጪ ከቀደመው በጀት ዓመት አኳያ በንፅፅር ሲቀመጥም ከ283 ሚሊዮን ብር በላይ ጨምሯል፡፡

በውጭ ምንዛሪ ግኝት በኩል ባንኩ ከካቻምናው ያነሰ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ ባንኩ በ2007 በጀት ዓመት 225 ሚሊዮን ዶላር ገቢ አግኝቶ የነበረ ሲሆን፣ በ2008 በጀት ዓመት ያገኘው የውጭ ምንዛሪ ግን 223 ሚሊዮን ዶላር ሆኗል፡፡ ይህ ክፍተት በተለይ ከወጪ ንግድ ገቢ መቀዛቀዝ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡

ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ በአሁኑ ወቅት 200 ቅርንጫፎች ያሉት ሲሆን፣ 1.4 ቢሊዮን ብር ካፒታል አስመዝግቧል፡፡

ከሁለት እጥፍ በላይ የትርፍ ዕድገት ያስመዘገበው ደቡብ ግሎባል ባንክ ካፒታል የማሳደግ ፈተና ይጠብቀዋል

ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ኑረዲን አወል እና አቶ አዲሱ ሐባ

በዳዊት ታዬ

ከ16ቱ የአገሪቱ የግል ባንኮች ኢንዱስትሪውን በመቀላቀል ከመጨረሻዎቹ የግል ባንኮች ሁለተኛው በመሆን ወደ ሥራ የገባው ደቡብ ግሎባል ባንክ አምስተኛ ዓመቱን ይዟል፡፡ ቅዳሜ ኅዳር 24 ቀን 2009 ዓ.ም. የላቀ አስተዋጽኦ አደረጉ ላላቸው የባንኩ ደንበኞች ዕውቅና ለመስጠት ባዘጋጀው ‹‹የደንበኞች ቀን›› ፕሮግራም ወቅት የባንኩ ኃላፊዎች እንደገለጹት፣ ባንኩ በአራት ዓመታት ቆይታው ዕድገት እያሳየ መምጣቱን ነው፡፡

ደቡብ ግሎባል በ2008 በጀት ዓመት ያስመዘገበው ውጤት ባለፉት ሦስት ዓመታት ከተገኘው የበለጠ ስለመሆኑ የገለጹት የባንኩ ፕሬዚዳንት አቶ ሃዲሱ ሃባ፣ ባንኩ በበጀት ዓመቱ በተለይ ከታክስ በፊት ያገኘው ትርፍ የ200 በመቶ ዕድገት ያስመዘገበ እንደነበር ጠቅሰዋል፡፡ በ2008 በጀት ዓመት ከታክስ በፊት 68 ሚሊዮን ብር ማትረፍ መቻሉ በቀደመው በጀት ዓመት አስመዝግቦት ከነበረው 22.6 ሚሊዮን ብር አኳያ የዘንድሮ ትርፉ ከሁለት እጥፍ በላይ ዕድገት የታየበት ነው፡፡ ይህ የትርፍ ዕድገት በኢንዱስትሪው ውስጥ ከተመዘገበው አንፃር ከፍተኛው ዕድገት ቢሆንም የባንኩ ዓመታዊ ትርፍ ከብዛት አኳያ ከሌሎች ባንኮች አንፃር ሲታይ ግን አነስተኛ መጠን ያለው ነው፡፡ የባንኩ ኃላፊዎች ግን የትርፍ መጠኑ ቢያንስም ከፍተኛ ዕድገት አሳይተናል ይላሉ፡፡ ከባንክ አገልግሎቶች አኳያ ደቡብ ግሎባል ባንክ ካለፉት ዓመት የተሻለ ዕድገት ማሳየቱን የሚያመለክተው የፕሬዚዳንቱ ንግግር፣ የተቀማጭ ገንዘብ መጠኑን በ6.4 በመቶ በማሳደግ በ2008 በጀት ዓመት 871.8 ሚሊዮን ብር እንደደረሰ ያትታል፡፡ በባንኩ የደንበኝነት መዝገብ ውስጥ የሰፈሩና ሒሳብ የከፈቱ ደንበኞች ቁጥርም በ44.4 በመቶ ማሳደጉ የባንኩን ተደራሽነት መጨመር ያሳያል ተብሏል፡፡ አጠቃላይ የባንኩ ሀብት በ13 በመቶ በማደግ 1.3 ቢሊዮን ብር ማድረስ መቻሉን የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ፣ በ2008 በጀት ዓመት ባንኩ የሰጠው የብድር መጠን በ76.8 በመቶ በማደግ 599.3 ማስመዝገቡ የባንኩን ጤናማ ጉዞ አመላካች እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ በበጀት ዓመቱ የባንኩ ጠቅላላ ገቢ 194.1 ሚሊዮን ብር ነበር ተብሏል፡፡

ባንኩ በኢንዱስትሪው ውስጥ ያለውን የገበያ ድርሻ ለማሳደግ የአምስት ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅድ በማውጣት እየሠራ መሆኑን የገለጹት የባንኩ የዕቅድና ቢዝነስ ዴቨሎፕመንት መምሪያ ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ብሩ፣ ባንኩ ገና ታዳጊ ቢሆንም ባለፉት አራት ዓመታት ጉዞው ውጤታማ ነበር ይላሉ፡፡ ለዚህ ማሳያ ብለው ያስቀመጡት የባንኩን የአራት ዓመታት ትርፍና ኪሳራ የሚያሳየውን አኃዛዊ መረጃ በመጥቀስ ነው፡፡

ባንኩ ወደ ሥራ በገባበት በ2005 ዓ.ም. የመጀመሪያው ዓመት አፈጻጸሙ 14.3 ሚሊዮን ብር ኪሳራ ማስመዝገቡን የሒሳብ ሪፖርቱ አሰናድቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከመጀመሪያው ዓመት በኋላ ከኪሳራ ወጥቶ በ2006 ዓ.ም. 18.5 ሚሊዮን ብር፣ በ2007 ደግሞ 22.6 ሚሊዮን ብር በማትረፍ በአሁኑ ወቅት 68 ሚሊዮን ብር ሊደርስ መቻሉ የባንኩን የዕድገት ጉዞ ያሳያል ብለዋል፡፡ በደንበኞች ቀን ፕሮግራም ላይ የባንኩ ኃላፊዎች በሁሉም የባንክ አገልግሎት ዘርፎች ዕድገት መኖሩን ተናግረው፣ በ2008 በጀት ዓመት የተከፈለ ካፒታሉ በ32.3 በመቶ ጭማሪ እንዳሳየም ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ባንኩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመርያ መሠረት የተከፈለ ካፒታሉን 500 ሚሊዮን ብር ለማድረስ 138 ሚሊዮን ብር ማስመዝገብ ይጠበቅበታል፡፡

የባንኩን ካፒታል በሚፈለገው መጠን ማሳደግ ባለመቻሉ በብሔራዊ ባንክ ሕግ መሠረት የተከፈለ ካፒታሉን ግማሽ ቢሊዮን ብር ማድረስ ያልቻለ ብቸኛው ባንክ እንዲሆን አስገድዶታል፡፡ የብሔራዊ ባንክ መመርያ በሚያዘው መሠረት፣ ለካፒታል ማሳደጊያ የተሰጠው የጊዜ ገደብ የሚጠናቀቀው በዚህ ዓመት ነሐሴ ወር ላይ በመሆኑ ባንኩ በቀሩት ወራቶች ቀዳሚ ሥራ አድርጎ የሚወስደው የተከፈለ ካፒታሉን 500 ሚሊዮን ብር ለማድረስ ነው፡፡ በባንኩ በደንበኞች ቀን ፕሮግራም ላይ የተገኙት የባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ኑረዲን አወል፣ ባንኩ እያገኘ ያለው ውጤት አበረታች ቢሆንም ካፒታሉን በማሳደጉ ረገድ የታየውን ክፍተት ለመድፈንና ቀሪውን የተከፈለ ካፒታል መጠን የሞት ሽረት ጉዳይ እንደሚሆን ተናግረዋል፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካፒታሉን ማሟላት ግዴታ በመሆኑም ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ዝግጅት መደረጉን ጠቅሰዋል፡፡ እስከ መጪው ነሐሴ ወር ይህንን ያህል ካፒታል መሙላት ፈታኝ ሊሆን ይችላል የሚል ሥጋት በባለአክሲዮኖች ዘንድ ቢኖርም፣ የባንኩ ኃላፊዎችን ግን ግማሽ ቢሊዮን ብር የተከፈለ ካፒታል እንደሚመዘገብ ያምናሉ፡፡

በዕለቱ ከባለአክሲዮኖች እንደተገለጸው ባንኩ ካፒታል በማሰባሰብ ላይ ክፍተት ያለበት በመሆኑ የተቀመጠው የጊዜ ገደቡ ከመድረሱ በፊት ይህንን ማሟላት ይቻላል ወይ የሚለው ጉዳይ አሳስቧቸዋል፡፡

ስለዚህ ባንኩ ያተረፈውን ትርፍ ለካፒታል ማሳደጊያ እንዲውል ከማድረግ ባሻገር ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ድርሻቸውን ማሳደግ እንደሚጠበቅባቸው አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ የባንኩ ዋነኛ ሥራ መሆን ያለበት ካፒታሉን ማሳደግ እንደሆነ ያሳሰቡት ባለአክሲዮኖች፣ በዕለቱ የነበራቸውን አክሲዮን በእጥፍ ለማሳደግ ቃል ሲገቡ ታይተዋል፡፡

የባንኩ የግብይት ዘርፍ ኃላፊም የተከፈለ ካፒታሉን የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት ለማሟላት የተለያዩ ስትራቴጂዎች መቀረጻቸውን አስታውሰው፣ ለዚህም የባንኩ ደንበኞች ባለአክሲዮኖች አዳዲስ አክሲዮን እንዲገዙ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

የባንኩ ባለአክሲዮኖች በባንኩ አክሲዮን ተጨማሪ አክሲዮኖችን ከመግዛት ጀምሮ አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን በማምጣት የባንኩን ዕቅድ እንደሚያሳኩ ገልጸዋል፡፡ አቶ አዲሱም የባንኩን ካፒታል 500 ሚሊዮን ብር ለማድረስና በስትራቴጂክ ዕቅዱ መሠረት በሚቀጥሉት አራት ዓመታት ውስጥም ካፒታሉን ሁለት ቢሊዮን ብር ለማድረስ ከባንኩ ደንበኞች ብዙ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

solutions work
better
when offered
together
Like us on
facebook
letter mail
door to door
parcel mail
transport service
express mail service
financial solutions
የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት
ETHIOPIAN POSTAL SERVICE ENTERPRISE
WESTERN UNION WU
moving money for better
ፖስት ባስ POST BUS
EMS
FINANCIAL SOLUTION
PARCEL MAIL
PUBLIC TRANSPORT
EXPRESS MAIL
ETHIOPIAN
POSTAL
SERVICE
ENTERPRISE
HEAD OFFICE
P.O.BOX
5555
TEL.
251115151045
www.ethiopostal.com

ለንጋት ሜካኒካል ምህንድስና ባለአክሲዮኖች የስብሰባ ጥሪ

የንጋት ሜካኒካል ምህንድስና አ.ማ. የባለአክሲዮኖች የ12ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ እና 8ኛ ድንገተኛ አስቸኳይ ጉባዔ ቅዳሜ ታኅሣሥ 15 ቀን 2009ዓ.ም. (እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 24 ቀን 2016) በግዮን ሆቴል ሰማያዊ የስብሰባ አዳራሽ ከሰዓት በኋላ ከ8፡00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል፡፡ ስለዚህ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው ከላይ በተጠቀሰው ቦታ፣ ቀንና ሰዓት በጉባዔው ላይ እንዲገኙና እንዲሳተፉ የዲሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

የዲሬክተሮች ቦርድ የመደበኛ ስብሰባው አጀንዳ

1. የጉባኤውን ረቂቅ አጀንዳዎች ማጽደቅ
2. የዲሬክተሮች ቦርድን የ2008 በጀት ዓመት ሪፖርት ማዳመጥ
3. የ2008 የውጪ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥ
4. በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ መወያየትና ማጽደቅ
5. የውጪ ኦዲተሮችን ስለመሾምና ክፍያ መወሰን
6. የዲሬክተሮችን አበልና የሥራ ዋጋ መወሰን
7. የስብሰባውን ቃለ ጉባዔ ማጽደቅ

የአቺኳይ ድንገተኛ ጉባዔ አጀንዳ

1. የአክሲዮን ማኅበሩን የካፒታል መጠን ስለማሳደግ
2. ስለ ድርጅቱ የወደፊት አቅጣጫ ተወያይቶ ስለመወሰን

በአካል በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ጉባዔው ከሚካሄድበት ሦስት የሥራ ቀናት በፊት ኮተቤ ብረታ ብረት መሣሪያዎች ፋብሪካ በሚገኘው የአክሲዮን ማኅበሩ ጽ/ቤት ቀርባችሁ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ በመሙላት ወይም ሥልጣን በተሰጠው አካል ከተረጋገጠ ሰነድ ጋር ሕጋዊ ወኪላቸውን በስብሰባው እለት መላክ የሚችሉ መሆኑን በማክበር እንገልጻለን፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በሚከተሉት አድራሻዎች ይጠቀሙ ስልክ፣0116 46 30 40 ወይም 0911 10 44 69
ኢሜይል nigatmechanical@gmail.com

AIR

AMERICAN INSTITUTES FOR RESEARCH®

RFP Announcement

The American Institutes for Research (AIR), Reading for Ethiopia's Achievement Developed Monitoring and Evaluation (READ M&E) project is hereby seeking qualified and responsive organizations/vendors to provide **Logistical services for:**

- **Formative Continuous Assessment (FCA) training in Amhara Region at Dessie, Finote Selam, Debre Tabor and Debre Berhan RFP# 2016-RFP12-004**
- **Regional Level EGRA key finding dissemination workshop in five venues at Bahir Dar, Mekelle, Bishoftu, Hawassa and Hossana; RFP# 2016-RFP12-005**
- **Formative Continuous Assessment (FCA) training in Oromia Region at Adama, Harar and Nekemte RFP# 2016-RFP12-007.**

The hard copy of the RFP document (s) can be collected directly from READ M&E Project office as of **December 8, 2016** (see address below) during office hours (8.00 am to 5.00 pm). Soft copy of the RFP can also be provided via email by submitting your request at rbernardo@air-read-me.org. If a soft copy is requested, please list the RFP number and title in the email subject line.

Interested logistical services providers are invited to submit their signed quotations via email at rbernardo@air-read-me.org . The RFP number and title must be listed in the email subject line. However if preferred, a hard copy can be delivered in a sealed envelope to Rahel Bernardo no later than the date specified in the RFP document.

For further information, contact Rahel Bernardo, Admin Assistant/Procurement, Logistics and HR Tel. 011 8 684687 or 0911 718509.

Project: Reading for Ethiopia's Achievement Developed Monitoring and Evaluation(READ M&E) Project.

Address: Bole Sub city, Mickey Leland Street Woreda 04 House No. 333, PACT Building, 4th Floor, Addis Ababa, Ethiopia

---

በከልቻ ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር
BEKELCHA TRANSPORT SHARE COMPANY

የጨረታ ማስታወቂያ

በከልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር እ.ኤ.አ. የ2016 በውጪ ገለልተኛ ኦዲተሮች ለማስመርመር ይፈልጋል፡፡

በዚሁ መሠረት ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ፣ ቲን ቁጥር ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር አጠናቀው የከፈሉና ደረጃቸው -ለ- ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የኦዲት ኩባንያዎችን ያወዳድራል፡፡

ስለሆነም መስፈርቱን የምታሟሉ ኦዲት ኩባንያዎች ከጨረታው የመክፈቻ ቀን በፊት የሥራውን ስፋት ናዝሬት ዋናው መ/ቤት ድረስ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ቀርቦ በማየት የሚሰሩበትን ዋጋ፣ ሥራውን ለመጀመርና ሪፖርት ለማቅረብ የሚችሉበትን ጊዜ ጭምር በመግለጽ የመወዳደሪያውን ሰነድ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ እ.ኤ.አ. በ16/12/2016 ናዝሬት ዋናው መ/ቤት በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ 8፡00 ሰዓት ድረስ ብቻ ማስገባት ትችላላችሁ፡፡

የጨረታ ሳጥኑም በዚሁ ዕለት ከቀኑ በ8፡00 ሰዓት ታሽጐ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎች በተገኙበት ቦታ በዚሁ ቀን ከቀኑ በ8፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡

አክሲዮን ማህበሩ የተሻለ መንገድ ካገኘ ይህንን ጨረታ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ በከፊልም ሆነ በሙሉ መሰረዝ ይችላል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ ናዝሬት ስልክ ቁጥር 0221-11 17 91 ወይም 0221-12 25 96 መጠየቅ ይችላሉ፡፡

ማሳሰቢያ፡- ተጫራቾች በሥራው ላይ ሊመደቡ የሚችሉትን ሠራተኞች ካሪኩለም ቪቴ/CV/ ማያያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

በከልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር

ታ ነ ቢ

‹እንኳን ቀዝቅዞን ወትሮም በረዶ ነን›

እነሆ መንገድ:: ከመካኒሳ ወደ ጀሞ ልንጓዝ ነው:: ቀና ሲሉት እየጎበጠ ታጠፈ ሲሉት እየረዘመ መንገድ ጠመዝማዛው ዛሬም ያሸናል:: ለአፍታ ባወጋንበት በዚህ ጎዳና ለዘመን በተወዳጀንበት በዚህ መንገድ ከስሜታችን የታለበ ማስረጊያ ዜማ ‘መለያየት ሞት ነው’ የሚለው ብቻ ነው:: አሁን አሁን እየተካው ቅድም በትዝታ ወዲያ ወደ ኋላ እየጋለበ፣ ነገ የሥጋት ጦሩን ሰብቆ እያስጨነቀ ጊዜ ሲያልፍ ጊዜ ይተካል:: መንገድ ሲያልቅ መንገድ ይጀመራል:: “አንተ እባክህ መስኮቱን ዝጋው፤” ትነጫነጫለች የወያላው መከዳ ላይ አንገቷን ያንተራሰች ተሳፋሪ:: “ዕውን መስኮቱ ነው እንዲህ የሚያስጮህሽ? ነገር ነው እንጂ፤” እያለ ወያላው መስኮቱን ይዘጋል:: “ብርድ ብመታ ታሳክመኛለህ?” ሙግት ጀመረች:: “ብርድ የሚባል ነገር የለም:: ምላስ እንጂ ንፋስ ጥሎን አያውቅም ማነሽ?” ይላል ግንባሩን ቅጭም አድርጎ ሚስጥር አዘል ሥዕል እንደሚያጠና ሆኖ አጠገቧ የተቀመጠ ጎልማሳ:: “ኧረ ሰማይ የሚባልም የለም:: ዕድሜ ለህዋ ሳይንስ. . .” ይላል መሀል መቀመጫ አጠገቤ የተቀመጠ ወጣት፣ የደወለላቸውን ደንበኛ ከአገልግሎት መስጫ ክልል የሉም ተብሎ የሚያደርገው ጠፍቶት::

“ሳይንስ አልከው? ምናለበት የምናምነውን እያስጨበጡ ያመነውን ቢያስጥሉን?” ይጠይቃል ሦስተኛው ረድፍ ላይ የተቀመጠ ወጣት:: ቆያይቶ ደግሞ፣ “ለነገሩ እነሱ ምን አደረጉ? የአምላክን ሥራ ገለጡ እንጂ ምን አደረጉ? አለን እንጂ መሬት ክብ መሆኗን የሰማን ዕለት እምነትን ያህል ትልቅ ነገር እንደ ኳስ ልንጫወትበት የሚያምረን?” ቢል፣ “እንኳን በክብነት አመንን እንጂ ግዴለም ዞረን ዞረን ከመሬት ነን፤” ትለዋለች አጠገቡ የተመቀጠች ወይዘሮ:: “ምኑን ተመለስነው ወደ ሮቦት ዘመን እየገባን?” ሲላት ክንብንቡን እያስተካከለ፣ “እህ እሱማ እንግዲህ ከአቅም በላይ ነው:: መቼም በዚህ ጉዳይ ተመልካች እንጂ ውሳኔ ሰጪ እንድንሆን አልታደልን?” ብላው ቅብጥብጥ የሚለውን ወያላ አተኩራ አየችው:: የሮቦት ወያላ ታያት ይሆን እንዴ? ምን ይታወቃል እኛም በዓይናችን እናይ ይሆናል እኮ!

“እኔ ምለው ግን?” ይላል ጎልማሳው ወደ ወይዘሮዋና ዲያቆኑ ዘወር ብሎ:: “በተበከለ አየር ልቀት አየር ንብረቱን እንዲህ መፕዋወዛቸው ሳያንስ የሮቦት ማኅበረሰብ ሰው ልጆች መሀል ማቀናጀት ሲያስቡ ዝም ብለን ልናይ ነው?” ከማለቱ አንዱ የሰሞኑ ብርድ በጥርስ ቁርጥማት አላመጠኝ ባይ፣ “አስበውማ ጨርሰዋል:: ይልቅ በጊዜ ደህና ጥሩር ለብሰን መጠበቅ ነው:: እንኳን ከሮቦት ጋር ከታክሲ ተጋፍተን እርስ በርሳችንም ወላልቀን አልቀናል፤” ብላ መጨረሻ ወንበር የተቀመጠች የዩኒቨርሲቲ ተማሪ የጨዋታው አባሪ ሆና ብቅ አለች:: “እኔ እኮ. . . ወይ ሐበሻ! . . . አሁን እስኪ የሮቦት ነው የማጣት ታሪካችን ነው የሚቀድመው? በቃ ያልበላንን ዝም ብለን መፎከት?” አለ በንዴት ከተማሪዋ አጠገብ የተቀመጠ ቸልተኛ መሳይ ወጣት:: “ይቅርታ ‘መፎከት’ ምን ማለት ነው?” ብላ ሳይሏት ተማሪዋ መጠየቅ::

ልጁም ነገር ያማረው ነገር ነው፣ “ይቅርታ በእንግሊዝኛ የማብራራት አቅም ስለሌለኝ ለቀቅ አድርጊኝ:: የዘንድሮ ምሩቃን እንደሆናችሁ የባጥ የቆጡን በጉራማይሌ እየቀየጣችሁ የምታደናብሩን ሳያንስ በገዛ ቋንቋችን ‘ሼም’ ልታሲዙን እንዲህ ያለ ጥያቄ ትጠይቃላችሁ?” ብሎ መዳፉን አማታ:: “ኧረ ተረጋጋ:: እንዲያውም እሷ እግዜር ይስጣትና አለማወቋን አውቃ ጠይቃለች:: ካልክስ አሉልህ በየሚዲያው አገር፣ ወገን፣ ዕድገትና ልማት እያሉ ሲያበቁ በመልካም ቋንቋ አጠቃቀም ችግር የመልካም አስተዳደር ችግራችንን የሚያባብሱት፤” ብሎ አጠገቤ የተቀመጠው ብሶቱን ሲናገር፣ “ኧረ እባካችሁ እንዳመጣልን አናውራ? እንዴ! አሁን እስኪ ላትጨርሱ ሳይንስን አንስታችሁ ሮቦቶችን አምታችሁ ስለቋንቋ ያነሳችሁት ምኑ ከምኑ ቢያያዝ ነው?” ብላ የንፋስ ‹ፎቢያ› ያለባት ወጣት ዘው አለች:: ይኼኔ ከጎኗ “በቃ! ግራ የገባው እኮ ከዚህም በላይ ይቃብዛል:: ለማናናርም አናናር ሲጠፋን ጨዋታስ ላይጠፋን ነው? እንዴት ነው ነገሩ?” ብሎ ገላመጣትና አረፈው:: የአየር ንብረቱ ብቻ ሳይሆን የንግግርና የወግ ሚዛናችን ጭምር ሳይዛባ አልቀረም መሰል ዘንድሮ! ኑሮ ከባድ ሚዛን ሆኖ!

ሾፌሩ ሙዚቃ ሊከፍት ቴፕ ይጎረጉራል:: ወያላው፣ “እስኪ ቅድም ያስጫንኳቸውን ዘፈኖች ክፈታቸው፤” ብሎ ‘ፍላሽ’ ያቀብለዋል:: “ካልክስ እስኪ የጥላሁንን ጋብዘንማ ሾፌር፤” ብሎ ጎልማሳው አንገቱን እየወዘወዘ ከንፈሩን መምጠጥ ያዘ:: አፍታ ሳይቆይ ደግሞ፣ “ምን ጥልቅ አድርጎኝ በሰዎች ነገር ምንስ አግብቶኝ በሰዎች ነገር’ አለ አፈር ልብላለትና . . .” እያለ ሊቀጥል ሲል “አያገባንም ብለንማ ይኼው ዓለም ስትፈርስ ይኼው ቆመን እያየን ነው፤” ብላ ወይዘሮዋ ጉድ አፈላች:: “በሕግ አምላክ! መንግሥት ባለበት አገር ዓለም ፈረሰ ብሎ ማውራት ወንጀል ነው የእኔ እመቤት፤” አላት ጎልማሳው ቆጣ ብሎ:: “እህ ታዲያ ዋሸሁ? ዓይተን እንዳላየን ሰምተን እንዳልሰማን መሆናች መሰለኝ ያለ ሙያው፣ ያለ አቅሙና ያለ ችሎታው ትንሽ ትልቁ አናታችን ላይ ቁብ እያለ የተበጠበጥነው:: አይደለም እንዴ? በሉ እንጂ አርሙኝ?” ብላ ተሳፋሪዎችን ቃኘች::

“ነው:: ግን ደግሞ ያገባኛል ይመለከተኛል ባይ ተቆርቋሪም ከመደቆስና ከመዳፈን ሌላ በለስ ሲቀናው አላየንም:: ስለዚህ አርፈን ልጆቻችን ለማሳደግ የጥላሁንን ዓይነት ዜማ ሳንወድ በግድ እንደግፋለን:: አይሞት ታዲያ? የሞተ ተጎዳ!” ብሎ መጨረሻ ወንበር አካባቢ ሰላሳን ያለፈ ወጣት ፀጉሩን እየፈተለ አስተያየት ሰጠን:: “ልክ ነው:: ዕድሜ ለልማታዊው መንግሥታችን መሀል ሰፋሪ በሁለት ጥይት ይመታል ብለን አንሥጋ:: ደግሞ. . . ህም. . . ከዝም ጭጭ በቀር ሌላ ዕድሜ ማራዘሚያ ዘዴ አለ እንዴ ጎበዝ? ስለዚህ ምን ጥልቅ አድርጎን?” ብላ ሳትጨርስ ጋቢና የተቀመጠች ጠይም ቆንጆ፣ “እኮ ሰው በሰው ላይ ሲሰለጥን፣ ሲያሴር፣ ሲገል፣ ሲሰርቅ፣ ሲያቂም፣ ሲያታልል ዝም? በቃ ይኼ ሆኖ ቀረ አትንኩኝ ባይነት?” ብለው ከጎኗ ተቀምጠው የነበሩ አዛውንት በትዝብት አዩዋት:: ኧረ አንዳንዱንስ እንኳን የትዝብት የአጥፍቶ ጠፊ ዓይንም አላስደነግጠው ብሏል:: ምን እንደሚሻል እኮ እንጃ እናንተ?

ከወደ ጋቢና ደግሞ እነሆ ሌላ ጫዋታ ይደመጣል:: ከዚህ ቀደም በደንብ የሚተዋወቁ ወዳጅ ቢጤ ናቸው:: አንደኛው መምህር ሳይሆን አይቀርም:: “ለመሆኑ አሁንም የምታስተምረው እዚያው ነው ወይስ ቀየሩህ?” ይጠይቃል የወዲያኛው:: “ተቀይሬ ሌላ ትምህርት ቤት ተመድቤያለሁ:: ምን ቦታ መቀያየር መሠረታዊ ለውጥ ያስከትል ይመስል ባለበት የሚረጋ እኮ ጠፍቷል፤” ይመልሳል መምህሩ:: “ለዚያ ይሆን ሽግሽጉና ዝውውሩ የበዛው?” ይላል ወደ ኋላ መቀመጫ አንድ ወጣት:: “በጣም! ምን እንደሚሻለን ግራ ገብቶናል?” ከጋቢና ጠያቂው ተናገረ:: “እህል ቢያላምጡት ካልዋጡት ጥቅም የለውም:: ሀቁን ተረድተው ካልሠሩበትና ሌሎች እንዲረከቡ ካልታገሉ እውነተኛ ለውጥ ማምጣት እንዴት ይቻላል?” አለ መምህሩ:: መቼም መምህር ዘንድ ምሳሌ አይጠፋምና በምሳሌ እያብራራ::

ከኋላ መቀመጫ የጋቢናው ጭውውት አንድ ሰበዝ ተመዞ ሌላ መልክ ይዟል:: “ዛሬ የማይቀየር ተጫዋች ቀይረው መስሎን ጉድ የሠሩን? እንዲያው ይኼ መቀያየርና መተካካት ምናለበት በሰዓትና በጊዜው በአግባቡ ተፈጻሚነት ቢኖረው?” ሲል አንደኛው ሌላው ተቀብሎ፣ “ሰው ሆኖ የማይሳሳት እንጨት ሆኖ የማይጨስ የለም እኮ?” ይላል:: “ሰው ሲሠራ ነው የሚሳሳተው:: አንዳንዴ ፋታ መስጠት ዕድል አለመንፈግ ቢለምድብን እንዴት ጥሩ ነበር?” ትላለች ከሴቶች ወገን:: ቅያሪውና መተካካቱ በዝቷል:: የአቅጣጫና የቦታ እንጂ የአስተሳሰብ መሆንና አለመሆኑን አጣርቶ ማን እንደሚነግረን ግን ግራ ገብቶናል:: የጠያቂው ብዛት መጥኔ ያሰኛል!

ወደ መዳረሻችን ተቃርበናል:: አንድ አዛውንቱ ስልክ እየደዋወሉ ከዘመን ጓኞቻቸው ጋር ለመገናኘት ይወተውታሉ:: የአንዱን ዘግተው ወደ አንዱ ሲሞክሩ፣ “በስተርጅና እስኪ አሁን ‘ቢዚ’ ነን ሲሉ አያፍሩም? ምን መዓት ነው የመጣብኝ ልጄ? ዕድሜያችንን በቀልድ አሳልፈን ስናበቃ በማረፊያችን ሰዓት ተሰብስበን የጥንት የጠዋቱን በማውጊያችን እንዲህ ለእንጀራ ተጠምደን እንረፈው?” እያሉ አንዴ ሾፌሩን አንዴ ወጣቷን ያያሉ:: ያ ከሾፌሩ ጀርባ ፊቱ ማይፈታው፣ “ያኔማ ምን አለ አባት? ቫት የለ ታክስ የለ፣ በየወሩ የቤት ኪራይ አይጨምር፣ የእህል ዋጋ ሰማይ አልነካ:: ሁሉ ያለውን ተካፍሎ ይኖራል፤” ብሎ ተግ ሲል፣ “አሁንስ?” አሉት:: የማያውቁትን እንደሚነግራቸው ሁሉ በምፀት እያጤኑት:: “አሁንማ እንኳን የምናካፍለው የምንጎርሰውም በቅጡ አይገኝ:: ያዩት የለም እንዴ? ትንሽ መንታፊው ይሻል እንደሆነ እንጂ ሠርቶ አዳሪውስ አልሆነለትም፤” ብሎ ያንን ፊቱ ይባስ ከሰከሰው::

“እንዴ! ግፉስ እናንተ? የድሮ ሰው እኮ ነው ይኼን ሁሉ ፍዳ ያመጣብን፤” ሲል ከጎኔ ያለው መዓት እንደመጣብኝ ተሸማቅቄ አየሁት:: “የምን ግፍ?” አለው ጎልማሳው:: “የእህል የውኃው. . .” ሳይጨርስ ጎልማሳው አቋርጦ፣ “ጡር’ አትልም ታዲያ? በተለያ ጉዳዮች ተሸናሽነን በዓይነ ቁራኛ የምንተያየው አንሶ ደግሞ በዕድሜ ልትለያየን ነው? ስንቱን እንገስጽ እናንተ?” እያለ ያዙኝ ልቀቁኝ አለ:: “ዝም አትለውም? ቋንጣ በጠጅ ተማገ፣ በፍሪዳ ደም በጮማ ስብ ታሪክ ተጻፈ ብሎ አባቶቻችንን ከሚወቅስ ፈጣኑ የኢኮኖሚ ዕድገታችን አምሮታችንን ገደበብን ብሎ አይገላገልም? ማንን ፈርቶ ነው? ዘመኑ እኮ የዴሞክራሲ ነው:: አህያውን ፈርቶ ዳውላው? ሆሆ?” ባዩዋ ወይዘሮዋ ናት:: ዕውን ከዓባይ መገደብ የአምሮታችን መገደብ የሚያብከነክነን ብዙ እንሆን እንዴ? ግን በቀኝ ሲሉት በግራ እያለ ዳኝነትን እንዲህ ያከበደው ምን ይሆን ጎበዝ? ፍርድ እንደ ራስ ነው ብለን እንውረድ? ወይስ አጥንት ድረስ ዘልቆ በሚሰማው ቅዝቃዜ እናስብ? ‹እትትት. . .›› ያለው ማን ነበር? ‹እንኳን ቀዝቅዞን ወትሮም በረዶ ነን› ተብሎ ነበር በአንድ ወቅት:: መልካም ጉዞ!

ማስታወቂያ

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE
ETHIOPIA

CAREER OPPORTUNITY
USAID/ETHIOPIA

USAID/ETHIOPIA is accepting applications from interested individuals for the position of **USAID Project Management Specialist (Democracy and Governance Cross-cutting)**

Location of Work: USAID/US Embassy Entoto Road

Final Closing Date: December 15, 2016

Salary Range: FSN-11 USD 22,457 to USD 40,421 per annum depending on the candidate's earning history, qualifications and experience.

Vacancy Announcement No.: 18/16

Basic Function of Position: The incumbent in this position serves as a Development Program Specialist (Democracy and Governance Cross-Cutting Advisor) -- to provide technical, managerial, reporting and administrative expertise to the Office of Democracy and Governance (ODG) on the full scope of its democracy and governance portfolio, but particularly, on cross-cutting programming with other USAID/Ethiopia technical offices. S/he develops, monitors, and evaluates program activities, policy development and capacity building that support the integration of improved democracy and governance as a cross-cutting objective across the Mission's portfolio.

Minimum Requirements:

Education: The multidisciplinary and multifaceted nature of the position requires a minimum of a Master's degree in Political Science, Public Policy, Public Administration, Rule of Law; or other related areas.

Experience: Five years of progressively responsible experience in the design and management of political policy programs, development and/or humanitarian programs, with specific involvement in good governance initiatives is required. Prior work experience in the design of good governance initiatives that impact upon sectors such as health, agriculture, food security or economic growth; democratic institutions or promoting the rule of law is desired. Three years' experience with USAID or other bilateral or multilateral development agencies, or International and/or Ethiopian non-governmental organizations in a project management capacity is required.

Language: Level IV (fluent) in English and Amharic. English will be tested.

Knowledge, Skills, and Abilities: A thorough understanding of the history, nature and dynamics of politics and governance in Ethiopia is required. Additionally, a thorough knowledge of the theory and practice of good governance and democratic principles and practices, including capacity building for government and civil society organizations, and analysis of political processes is required. A thorough knowledge of and ability to analyze the political environment and governance systems in Ethiopia. A complete command of the importance of gender equality and its relationship with good governance and the promotion of peaceful and stable communities. Ability to inter-relate democracy and governance issues, trends and developments USAID programming. Ability to prepare factual and interpretive reports covering good governance and political subject matter is required. Demonstrated capacity to participate in, lead and coordinate team efforts, to research and remain abreast of program management regulations, policies and procedures and to assist team members and implementing partners to apply them. Demonstrated ability to plan and conduct program evaluations, to develop outlines, solicit and incorporate inputs and edit team writing efforts. Ability to plan, organize, and execute complex projects. Excellent written and oral communication skills for analytical and factual reporting and presentations to senior GOE and USG officials. In addition, the incumbent will be expected to attend meetings, conferences, workshops, in and outside of Ethiopia at which they will be expected to represent the Mission's policies and program objectives and/or the Mission-endorsed results of their analyses.

All applicants must submit a completed form {Universal Application for Employment (DS-174)} along with the credential documents to USAID/Ethiopia, Human Resources Office via the email address addisusaidjobs@usaid.gov.

For your application to be considered, the following documents must be submitted:-

- Letter of Application/Cover Letter;
- Completed and Signed Application for Employment Official Form–DS-174 found here http://ethiopia.usembassy.gov/job_opportunities.html;
- Current Resume/CV;
- Application must be submitted ONLY via addisusaidjobs@usaid.gov and **the email subject must say–Vacancy 18/16 USAID Project Management Specialist (Democracy and Governance Cross-cutting);**
- Please submit the application only once; and
- Late and incomplete applications will not be considered; the application must be submitted before or on 5 p.m. Ethiopian time of the vacancy closing date.

The official application, form DS-174, must be signed by the applicant, in ink, not typed, and dated prior to submission. This requires the applicant to print, sign, date, scan and attach the DS-174 form to the email mentioned above. If an applicant does not sign, in ink, the applicant will not be considered by USAID/Ethiopia. Please take note of this requirement and please ensure you follow these instructions.

Internal/ External Job Re-Advertisement

About CRS: "Catholic Relief Services carries out the commitment of the Bishops of the United States to assist the poor and vulnerable overseas. Our Catholic identity is at the heart of our mission and operations. We welcome as a part of our staff and as partners people of all faiths and secular traditions who share our values and our commitment to serving those in need."

In Ethiopia, CRS has a long and rich history of providing emergency relief and development assistance to the people of Ethiopia since 1958. At present, CRS/ Ethiopia implements multiple projects through different partner organizations. CRS/Ethiopia has a highly diverse portfolio ranging from very large food-supported emergency response to cutting edge development programs. The current CRS/Ethiopia budget stands at $100 million with funding from the U.S. Government, UN agencies, private foundations, individual donors, and CRS private funds.

CRS strictly adheres to its Policy on Protection of Children and Vulnerable Adults among its staff, consultants, volunteers, and affiliates. CRS is an equal opportunity, affirmative action employer: women, minorities and people with disabilities are encouraged to apply.

As part of CRS family, you will join the more than 5000 strong and vibrant individuals working globally to accomplish the mission of CRS. CRS/Ethiopia invites you, the qualified candidate, to apply for the following positions;

Position Title: SILC/Livelihoods Officer
Duty Station: Dire Dawa
Employment term: Indefinite period contingent upon funding of the ELRP
Reports to: ELRP Economic Livelihoods Manager

Background:

CRS Ethiopia is seekingqualified candidate for the Ethiopian Livelihoods and Resilience Program (ELRP), a five-year USAID Office for Food for Peace (FFP) Title II Development Food Assistance Project (DFAP). The ELRP will focus on building resilience to shocks, enhancing livelihoods and improving food security and nutrition for rural households vulnerable to food insecurity. ELRP will operate in Oromia Region as well as Dire Dawa Administrative Area.

1. Position summary:

CRS Ethiopia is seeking a SILC/Livelihoods Officer for the Ethiopian Livelihoods and Resilience Program (ELRP), a five-year USAID Office for Food for Peace (FFP) Title II Development Food Assistance Project (DFAP). The ELRP will focus on building resilience to shocks, enhancing livelihoods and improving food security and nutrition for rural households vulnerable to food insecurity. ELRP will operate in Oromia Region as well as Dire Dawa administrative unit. The incumbent will promote and implement CRS/ET's Saving and Internal Lending Communities (SILC) model while contributing to one of the key purposes of the ELRP scope of work: ensuring households improve their sustainable economic well-being.

2. Key /Specific Duties and Responsibilities:

2.1. Provision of Support
- Works closely with ELRP livelihoods team to integrate savings and internal lending communities (SILC) into the program as part of CRS/ET Integral Human Development Framework (IHD);
- Raises awareness, promotes and market the SILC model among implementing partners, and donors;
- Builds the capacity of ELRP implementing partners to integrate SILC into their activities;
- Provides vision and leadership to effectively develop, promote, integrate and expand CRS/Ethiopia's SILC Program;
- Designs training modules for ELRP staff, partners, supervisors and filed agents and builds local capacity to deliver high quality trainings;
- Provides technical assistance and manages the development, monitoring, analysis and evaluation of the SILC portfolio in ELRP

2.2. **Program Quality**
- Works closely with partners to achieve scale and excellence in operations; designs specific trainings to address weaknesses and integrate best practices into operations;
- Monitors the quality of the SILC programs through regular community site visits;
- Gathers, analyzes and studies information captured through the SILC MIS, Guides and supports ELRP staff and partners in their efforts to collect and analyze data on a monthly basis;
- Advises on savings-led Microfinance quality standards and opportunities for enhanced programming;
- Designs, appropriate to monitoring and evaluate tools for SILC program;
- Participate in overall program reviews and evaluations;
- Supports project proposal development within the different sectoral programs, helps CRS /ET program managers and partners' budget for SILC and integrate SILC in a multitude of development activities;
- Supports successful establishment of SILC groups, identification, training and launching of Private Service Providers (PSP)
- Actively participates in meetings with program managers and unit heads to define program vision;
- Integrates SILC in design of ELRP monitoring and evaluation approaches;

2.3. **Learning Agenda**
- Documents, disseminate and publish lessons learned and best practices;
- Incorporate lessons learned and innovations from partners to improve data gathering and MIS spreadsheets;
- Stay abreast of new developments in savings-led Microfinance;
- Performs other related duties as required.

3. Minimum Qualification Requirements:
- Completion of 1st Degree (Social or Natural Science) or
- Completion of 2nd Degree in Social or Natural Sciences
- 2 years for 2nd Degree or 5 years for 1st Degree in Savings and Lending/Microfinance programs
- Good knowledge and experience in facilitation, participatory planning, conducting training of SILC programs
- Analytical and planning skills
- Good communication and interpersonal skill
- Excellent knowledge to develop, promote, integrate and expand SILC programs
- Team player with good facilitation skills and objective oriented
- A high level of computer literacy

3.3 Agency-wide Competencies

These are rooted in the mission, values, and principles of CRS and used by each staff member to fulfill his or her responsibilities and to achieve the desired results.
- Serves with Integrity
- Models Stewardship
- Cultivates Constructive Relationships
- Promotes Learning

❖ **How to apply:**

- You should send your application letter and up-to-date CV via email address: ET_Job_Applications@global.crs.orgbefore the application deadline,December 12, 2016. Please write the position title you are applying for in your subject line of your email, and in your application letter.
- This job opportunityis open to Ethiopian nationals only.Phone solicitations cannot be accepted. Only if you are selected for exam/ interview, you will be contacted.

**** Qualified women are highly encouraged to apply****

VACANCY ANNOUNCEMENT

Our Company, Brosol Engineering plc, is an importing company of Generator & other electromechanical products. The company intends to recruit a qualified candidate for its vacant position with the following requirements;

- **Qualification:** Diploma or More
- **Field of Study:** Electricity/Automotive Technology
- **Experience:** 2 years in generator maintenance, service and installation
- **Salary:** As per the Company's Scale
- Qualified individuals, who are interested to apply for the position, shall submit their Credentials/ CV in person to our office; Kera **Ayalew Building (Ground Floor)**, around Down Town Hotel & in front of Sofia Mall in **10 working** days.

For further information please call;
Telephone/ Office: 0118603034
Mobile: 0919825684/ 0935402126

SPECIAL VACANCY ANNOUNCEMENT
Open to Internal/External Candidates

IOM International Organization for Migration

Vacancy No.	:	**IOM-SVN/0074/2016**
Position Title	:	**Project Assistant**
Duty Station	:	**Semera, Ethiopia**
Classification	:	**General Service Staff, Grade G3**
Type of Appointment	:	**SVN, Six months with possibility of extension**
Estimated Start Date	:	**As soon as possible**
Closing Date	:	**December 21, 2016**

Established in 1951, IOM is the leading inter-governmental organization in the field of migration and works closely with governmental, intergovernmental and non-governmental partners. IOM is dedicated to promoting humane and orderly migration for the benefit of all. It does so by providing services and advice to governments and migrants.

IOM is committed to a diverse and inclusive environment. Internal & External candidates are eligible to apply to this vacancy.

Background:

Under the overall supervision of the Migration Management Programme Coordinator, Migration Management Unit (MMU), and the direct supervision of the Sr. Migration Management Capacity Building Project Assistant, the incumbent will be responsible for supporting the smooth operations of the Emergency Migration Response Center (EMRC) in Semera and for assisting in the implementation of MMU's capacity building programming under different projects in Afar Regional State. Specific duties shall include:

Core Functions / Responsibilities:

Logistics and Direct Assistance to Beneficiaries

1. Provide clerical support to the logistical and administrative requirements to ensure smooth EMRC operations;
2. Ensure the safety and security of migrants as well as the respect of their rights while in the center and control (un)authorized access;
3. Undertake tailored logistical arrangements for all cases of departing or arriving migrants as per the agreed upon regulations, including for cases with special needs such as medical cases and unaccompanied migrant children (UMC).
4. Draft and compile reports on EMRC activities.

Data Management

5. Regularly collect EMRC beneficiaries' bio data and update EMRC database as per IOM data protection/confidentiality standards and review the data for accuracy.
6. Ensure the organized documentation of incoming/outgoing letters, project/ operational reports, data reports, e-mails, EMRC documents, and other relevant documents.

Quality Management and Migrant Rights Promotion

7. Inform beneficiaries of their protection rights;

Awareness Raising and Behavioural Change Communication

8. Share updated information on the services provided by the EMRC and raise the awareness of transiting migrants on the risks of irregular migration through conduct outreach activities and distribute Information, Education and Communication (IEC) materials;

Coordination with Partners

9. Support the maintenance of efficient working relationships, regular coordination meetings and communication with local partners mandated with the rescue and assistance to vulnerable migrants;
10. Perform such other duties as may be assigned.

Required Qualifications and Experience

Education

- University Degree or Diploma holder in social science or related field of study.

Experience

- Minimum of one year relevant experience for Degree holders and three years' experience for Diploma holders in assisting migrants, refugees or other vulnerable groups, including children;
- Experience working in the non-profit sector (governmental, non-governmental and/or international organizations);
- Good IT skills: familiarity with data management equipment and software, working knowledge of Microsoft Office Application, especially Word, Excel and Outlook;
- Good writing, communication and negotiation skills;
- Commitment, efficiency, flexibility, strong work ethic and drive for results are important assets;
- Ability to work effectively and harmoniously with colleagues from varied cultures and professional backgrounds;
- Basic knowledge of International, Regional and local legal instruments on migrant and child protection and desire/ability to apply these standards in day-to-day work.

Languages

- Fluency in English and Amharic is required. Knowledge on Oromiffa, Tigrigna and other local language is advantageous.

Other

Any offer made to the candidate in relation to this vacancy notice is subject to funding confirmation.
Appointment will be subject to certification that the candidate is medically fit for appointment and verification of residency, visa and authorizations by the concerned Government, where applicable.
Only candidates residing in either the country of the duty station or from a location in a neighbouring country that is within commuting distance of the duty station will be considered. In all cases, a prerequisite for taking up the position is legal residency in the country of the duty station, or in the neighbouring country located within commuting distance, and work permit, as applicable.

How to apply:

Interested candidates are invited to submit their applications, CV written in English with photocopies of educational/training certificates via our e-mail address RECADDIS@iom.int, by December 21, 2016 at the latest, referring the position title and number in the subject line of your email.

Only shortlisted candidates will be contacted.
We strongly encourage qualified women to apply!

Posting period:
From 07.12.2016 to 21.12.2016

Society for International Ministries (SIM)
Has the following external Vacancy

1. **Post: Assistant Counselor**
2. **Educational backgrounds:** Masters degree in Social Work, Psychology, or Counseling degree
3. **Experience and Core competencies**
   - 2+years job experience in the non-profit sector preferred
   - Fluent written and spoken English skills
   - Completion of EMDR basic training
   - Working knowledge of child development and family systems theory
   - Well-developed skills in empathy and relationship building
   - Ability to communicate within a multi-cultural team
   - Ability to relate to families in poverty and of different cultural and religious backgrounds
   - Establishes professional boundaries within the counselor-client role
4. **Reports to:** Counselor
5. **Basic Responsibilities**
   - A compassionate and committed counselor to assist in providing counseling and mental health care for the families of Ethiopia ACT.
6. **Specific responsibilities**
   - Provide counseling for children, teenagers, adults, families
   - Lead psycho-educational groups for adults and teenagers
   - Write individualized treatment plans and goals
   - Conduct psychological assessments
   - Provide follow-up care through home visits
   - Write follow up notes and recommendations for clients
   - Cooperate within multi-cultural and interdisciplinary teams and with the
   - Refer clients for psychiatric follow-up within the Ethiopian health care system
6. **Terms of Employment:** Permanent after probation period depending on the project cycle
7. **Place of Work:** Addis Ababa, with regular visit to project sites
8. **Salary**: Per the organization's scale

N.B: Interested applicants who meet the requirements are invited to submit their letter of application with Curriculum Vitae, one photo, and relevant documents on or before 21 December 2016.

Human Resources Office
SIM-Ethiopia
P.O.Box: 127, Addis Ababa
011:5503899 or 011:5513028
Applications shall not be returned

IOM International Organization for Migration

Vacancy Announcement
Open to Internal & External Candidates

The International Organization for Migration Special Liaison Office (IOM/SLO) is hiring qualified and experienced humanitarian workers for its offices in Ethiopia for various positions indicated in the table below. The detail Terms of Reference for each positions can be accessed on IOM Ethiopia website or through this link http://ethiopia.iom.int/current-vacancies.

Type of Appointment: SVN, Six months with possibility of extension, for all positions
Estimated Start Date:As soon as possible, for all positions
Closing Date:December 21, 2016,for all positions

Established in 1951, IOM is the leading inter-governmental organization in the field of migration and works closely with governmental, intergovernmental and non-governmental partners. IOM is dedicated to promoting humane and orderly migration for the benefit of all. It does so by providing services and advice to governments and migrants.

Vacancy No	Position Title	Classification: General Service Staff	Number of vacant posts	Duty Station	Requirement
IOM-SVN/075/16	Bus Driver/ Mechanic	G3	1	Dollo Ado, Ethiopia	High school, 4 year of driving experience and valid driving licences grade 4,formal vehicle mechanical training and/or several years' experience mechanical maintenance of vehicles, excellent communications skills. Drive for results. Flexibility and ability to work within a multicultural team and hardship conditions. • **Languages:** Thorough knowledge of English& Amharic languages is required. Knowledge of Somali language is an advantageAbility to work well under pressure and with tight deadlines; • Ability to use Microsoft Excel, Outlook and Word, database, statistical software. **Experience of having worked and/or being a resident of Somali region of Ethiopian is an advantage.**
- Mechanical design & Inspection of Hospital facilities like centralized Boilers, Gas System (MGPS), and water pump system, Elevators & other related accessories.
- Maintain accurate records and files according to quality standard.
- Coordination of design, tests, and builds activities between the design team and key cross-functional teams.
- Application of standard engineering design principles and methodology for research of design options and experimentation to determine potential design feasibility or application.
- Performs other duties of a similar nature or level.

Required No. :- 1

Condition and duration of employment

One year Contract with possibility of extension

Salary: Attractive & Negotiable!

Duty Station: Federal Ministry of Health & Flexibility travel to Regions is required

Required skills

- Strong technical, analytical and planning skills
- Strong communication skills, project management skills, executed with a positive attitude
- both in speaking and writing Amharic and English
- Team work skills
- Project management skills
- Good knowledge of computer applications & Software's
- Effective time management

Special Skills:

Critical thinking with exceptional problem solving skills, able to work independently or in team environment.

- Efficiently organize and plan work tasks.
- Proactive, resourceful and highly motivated with good communication skills and ability to work in high output environment.
- Ability to balance multiple projects with proven track record.
- Travel as required to support projects.
- Contribute to office activities, initiatives, and learning programs

2. Position: ....Junior Civil Engineer

Educational Background

BSc. in Civil Engineering or Construction Technology and Management from 0 - 2 years work experience in a comparable junior position.

Duties and Responsibilities shall include, but not limited to:

- To assist in examination/ review concept plan(s) /Detailed Project Report(s) received in Ministry and make necessary suggestions/recommendations/advice.
- To assist in examination/review tender document(s) for civil or allied works and submit advice.
- To examine all technical issues related to and arising during implementation of civil and allied works in Projects and submits advice.
- To assist in evaluation of specifications and in quality assurance.
- To carry out all works as may be assigned by the Division.
- Any other work assigned by the Senior Civil Engineer.

Required No. :-

Condition and duration of employment

6 Month Contract with possibility of extension

Salary

Depending on the candidates qualification and track record

Duty Station: Federal Ministry of Health & possibly out to Regions

Required skills

- Strong technical, analytical and planning skills
- Strong communication skills, project management skills, executed with a positive attitude
- both in speaking and writing Amharic and English
- Team work skills
- Project management skills
- Good knowledge of computer applications & Software's
- Effective time management

Interested applicants are invited to submit their non-returnable applications, CVs and Copies of all documents together with original document within 7 (Seven) working days from the first announcement to **Human Resource Development & Administration Directorate**.

FEDERAL MINSTRY OF HEALTH

HUMAN RESOURCE DEVELOPMENT & ADMINISTRATION DIRECTORATE

TEL,011551-54-25

BLOCK 1 FIRST FLOOR, ADDIS ABABA

የዶናልድ ትራምፕ የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫን ማሸነፍ ከአፍሪካ ቀንድና ከኢትዮጵያ ግንኙነት አንፃር

በሉሉ ድሪባ

በቅርቡ ዶናልድ ትራምፕ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው በመመረጣቸው ለበርካታ አገሮችና መሪዎች ጥያቄ ፈጥሯል፡፡ በብዙዎች ዘንድ የዶናልድ ትራምፕ መመረጥ ያልተጠበቀ ከመሆኑም ባሻገር፣ የፕሬዚዳንቱ የውጭ ፖሊሲ ከዚህ በፊት ከነበሩት የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች ለየት ያለና አወዛጋቢ ነው፡፡ የትራምፕ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የሚያጠነጥነው ቅድሚያ ለአሜሪካ በሚለው ላይ ነው፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ከዓለም ዙሪያ ወደ አሜሪካ የሚደረገውን ስደትን መቆጣጠር፣ አሜሪካ ከሌሎች አገሮች ጋር የሚኖራትን የንግድ እንቅስቃሴ መቀየር፣ የዓለም አየር ንብረትን በተመለከተ የተለየ አቋም መያዝና ለታዳጊ አገሮች የሚደረጉ ሰብዓዊ ዕርዳታዎችን መቀነስ ወይም መከልከል የሚሉት በግንባር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ የሊብራል ሥርዓትን በመቃወም አምባገነናዊ መሪዎችን ለምሳሌም ለሩሲያ መሪ ለፑቲን በይፋ አድናቆቱን በመግለጽ ቀደም ሲል የአሜሪካ ወዳጅና አጋር ከሆኑት አገሮች ጋር ያለው ግንኙነት እንደሚለወጥ እየገለጸ ይገኛል፡፡

እንዲሁም ከሙስሊሙ ዓለም ጋር ያለው ግንኙነትና አክራሪነትን ለመዋጋት የሚከተሉት ስትራቴጂ ግልጽነት ካለመኖሩም በተጨማሪ፣ ከታዳጊ አገሮች ለአብነትም ከአፍሪካ አገሮች ጋር የሚኖረው የአሜሪካ ወዳጅነትና ሰብዓዊ ዕርዳታ ጋር ተያይዞ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ሲያነሱዋቸው የነበሩ ጉዳዮች ከዚህ በፊት ያልተለመዱ ከመሆናቸው የተነሳ በዓለም ማኅበረሰብ ዘንድ ጥያቄ ጭረዋል፡፡ በተለይም በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ዶናልድ ትራምፕ ለአፍሪካ አገሮች ምን ዓይነት ፖሊሲ እንደሚኖራቸው ሰፋ ባለ መልኩ ባይገልጹም፣ ስለአኅጉሩ ጥቂት ከተባሉት መካከል ዋነኛው የአፍሪካ መሪዎች ለሕዝቦቻቸው መልካም አስተዳደር ስለሌላቸው እንደገና 100 ዓመታት በቅኝ ግዛት መተዳደር አለባቸው በማለት በትዊተር ገጻቸው ላይ ያሰፈራት ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም የብዙዎቹ ጥያቄ በቅርቡ የተመረጡት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ያደረጉዋቸው ንግግሮችን ተግባራዊ ያደርጋሉ? ወይስ አያደርጉም? የሚለው ነው፡፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ሁለት አተያዮችን ማየት ያስፈልጋል፡፡ የመጀመሪያው የዶናልድ ትራምፕ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቀጣይነት ያለው፣ የቆየና በግለሰቡ እምነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የግለሰቡ ልምድ ማነስ፣ የአሜሪካን የውጭ ግንኙነቶች ውስብስበነት ጠንቅቆ ያለማወቅና የአገሪቱን ጥቅሞች ለይቶ ከማስከበር አኳያ ፕሬዚዳንቱ አሁን ያላቸው ግንዛቤ የተዛባ በመሆኑ፣ ወደፊት ከውጭ ጉዳይ ባለሙያዎች ጋር በመወያየት መሥራት እንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡

ስለሆነም አሁን መታየት ያለበት በቅስቀሳ ወቅት ፕሬዚዳንቱ ያደረጓቸው ንግግሮች ሳይሆኑ አሜሪካ ከሌሎች አገሮች ጋር በምታደርገው ግንኙነት ብሔራዊ ጥቅሞችን ማዕከል ማድረግ አለባቸው፡፡ ማለትም የፕሬዚዳንቱ አመለካከትና እምነቶች በአገሪቷ ውጭ ግንኙነቶች ላይ ያለው ተፅዕኖ የማይካድ ቢሆንም፣ የአገሪቱን ጥቅም በተሻለ ሁኔታ ተገንዝቦ ውሳኔ ይሰጣሉ በማለት የሚሾሙዋቸው የካቢኔው አባላትና አማካሪዎችም የላቀ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት አሜሪካ ከአፍሪካ ቀንድ ጋር የሚኖራት ግንኙነት የሚወሰነው ፕሬዚዳንቱ በምርጫ ወቅት ያደረጓቸው ቅስቀሳዎችን ብቻ ሳይሆን፣ የአሜሪካ መሠረታዊ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎችንና በቀጣናው አገሪቷ ያላት ጥቅሞችን ባማከለ መንገድ የፕሬዚዳንቱንና የሌሎች ሹማምንቶች አመለካከቶችንና እምነቶችን፣ እንዲሁም በዘርፉ ላይ የቆዩ ሙያተኞችንና አማካሪዎችን አስታውሰው ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት መቻል አለባቸው፡፡

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላምም ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ እ.ኤ.አ. የ2016 የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ማሸነፍ፣ አሜሪካ ከአፍሪካ ቀንድ ብሎም ከኢትዮጵያ ጋር የሚኖራትን የግንኙነት ሁኔታዎች በመዳሰስ ምን ዓይነት ለውጦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ለመገመት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ይህ ሪፖርት ሦስት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን፣ የመጀመሪያው አሜሪካ ከአፍሪካ ቀንድ ጋር ያላትን የቆዩ የግንኙነት ታሪኮችን መዳሰስና አገሪቷ ወደፊትም በቀጣናው የሚኖራት ብሔራዊ ጥቅሞችን መተንተን፣ በሁለተኛው ክፍል አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ግንኙነት ጥቅሞችንና ተግዳሮቶችን መዳሰስ፣ በሦስተኛ ክፍል ደግሞ ለአዲሱ ፕሬዚዳንትም ሆነ ለሌሎች ሹማምንት አፍሪካ ቀንድ ብሎም ኢትዮጵያ ለአሜሪካ ምን ዓይነት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ እንደሚኖራት በመተንተን የተለያዩ ትዕይንቶች (Scenarios) ማሳየት ነው፡፡

አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድ ያላት ፍላጎት

አፍሪካ ቀንድ ለአሜሪካ ስትራቴጂካዊ ቀጣና ነው፡፡ ምክንያቱ የቀጣናው ጂኦግራፊያዊ መገኛ በአንድ በኩል በነዳጅ ከበለፀገው የመካከለኛ ምሥራቅ አገሮች ባለው ቅርበት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ ሦስት አኅጉሮች ማለትም እስያ፣ አውሮፓና አፍሪካን የሚያገናኝ ቁልፍ ቦታ ነው፡፡ ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ ኃያላን አገሮች ቀጣናውን ለመቆጣጠር ፉክክር በማድረግ ቆይተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በአፍሪካ ቀንድ ፍላጎት ካላቸው አገሮች መካከል በዋናነት የባሕረ ሰላጤው ዓረብ አገሮች፣ ግብፅ፣ የአውሮፓ ኅብረት፣ ቻይናና ህንድ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ለአሜሪካ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ካላቸው አካባቢዎች አንዱ አፍሪካ ቀንድ ሲሆን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ለአገሪቷ የቀጣናው አስፈላጊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡ ለአሜሪካ የአፍሪካ ቀንድ አስፈላጊነት በአንድ በኩል ቀጣናው ከመካከለኛ ምሥራቅ ጋር ያለው ጂኦ-ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ትስስሮች ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ አሜሪካ ከሌሎች አፍሪካ አገሮች ጋር የጠበቀ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ለማድረግ አፍሪካ ቀንድን መቆጣጠር ይኖርባታል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1998 የአሜሪካ ኤምባሲዎች በምሥራቅ አፍሪካ ጥቃት ከደረሰባቸው በኋላ፣ እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ2001 ‹‹የ9/11›› ጥቃት ተከትሎ አሜሪካ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት ከምታደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ፣ ቀጣናው ሽብርተኝነትን ለመዋጋት ትኩረት ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል፡፡ አፍሪካ ቀንድ ለአሸባሪዎች መጠለያና ለእስልምና አክራሪነት ተጋላጭ ሥፍራ ነው፡፡ ለዚህም አመላካች የሚሆነው አብዛኛው የቀጣናው ማኅበረሰብ የእስልምና ተከታዮች መሆናቸውና ቀጣናው የእስልምና አክራሪነት ማፍለቂያ ከሆኑ ከመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ጋር ማኅበራዊ ትስስር ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌም አልቃይዳ በአካባቢው ሲያደርግ የነበረው እንቅስቃሴና በአሁኑ ወቅትም የአልሸባብ አሸባሪ ቡድን እንቅስቃሴ ቀጣናው ምን ያህል ለእስልምና አክራሪነትና ለሽብርተኝነት ተጋላጭ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ስለሆነም ያለፉት የአሜሪካ መሪዎች ክሊንተን፣ ቡሽና ተሰናባቹ ኦባማም አሜሪካ በቀጣናው ያላትን ፍላጎት ለማስከበር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ፖሊሲዎች ይከተሉ ነበር፡፡

በቀጣናው የአሜሪካ ዋና ተልዕኮ በጥቅሞቿና በወዳጆቿ ላይ ጥቃት እንዳይደርስ በማድረግ፣ በአካባቢው የሚገኙ ዓለም አቀፋዊ የሽብር ቡድኖችና የባህር ላይ ዘራፊዎችን እንቅስቃሴዎች መግታት፣ መደምሰስና የቡድኖቹን ትስስርና ግንኙነቶችን መበጣጠስ ላይ ያተኮረ ስትራቴጂካዊ እንቅስቃሴዎችን ታደርጋለች፡፡ ይህንን ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ አሜሪካ ከአፍሪካ ቀንድ ዋነኞቹ ወዳጆቹዋ ከሆኑት ከጂቡቲና ከኢትዮጵያ ጋር በአጋርነት ስትሠራ ቆይታለች፡፡ ለዚህም እ.ኤ.አ በ2002 ዓ.ም. በጂቡቲ ወታደራዊ የጦር ሠፈር ወይም ጣቢያ በማቋቋም ጠንካራ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከኢትዮጵያ ጋርም በአጋርነት የአካባቢው ደኅንነት ለመጠበቅ ይሠራሉ፡፡

አዲሱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንትም ቢሆኑ የአፍሪካ ቀንድ ጂኦ-ፖለቲካዊና ስትራቴጂካዊ ጥቅሞችን ያገናዘበ ፖሊሲ ይከተላሉ የሚል ግምት አለ፡፡ ምክንያቱም የቀጣናው ስትራቴጂካዊ ጥቅም ለአሜሪካ የላቀ በመሆኑ፣ ይህንን ጥቅም ለማስከበር ቀደም ሲል እንደነበረው የተለያዩ ስትራቴጂካዊ ዕርምጃዎችን መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ ዶናልድ ትራምፕ ምን ዓይነት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በአፍሪካ ቀንድ ሊኖራቸው እንደሚችል ከማየት በፊት፣ ቀደም ሲል የአሜሪካ መሪዎች በቀጣናው ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር ሲከተሉዋቸው የነበሩ ስትራቴጂዎችን ማየት ተገቢ ነው፡፡

ቀዝቃዛው ጦርነት ካከተመ በኋላ አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድ ያላትን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ሦስት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ስትከተል እንደነበረች ውድዋርድ የተባለው አጥኚ ገልጿል፡፡ የመጀመሪያው ሙሉ በሙሉ በወታደራዊ ጣልቃ ገብነት በቀጣናው ያላትን ጥቅም ማስጠበቅ ሲሆን፣ ይህንን ለማድረግ እንደ ሽፋን ሆኖ የሚያገለግል አስከፊ ሰብዓዊ ቀውስ ለመከላከል የሚል ነው፡፡ ለአብነትም እ.ኤ.አ 1992-93 በሶማሊያ ውስጥ የአሜሪካ ጣልቃ ገብነት የሚገለጸው በሰብዓዊ ቀውስ አማካይነት ነው፡፡ በዕርምጃው ምንም እንኳን የሰው ሕይወት ተርፏል ቢባልም፣ አፈጻጸሙ በተለያዩ ሥልቶችና ታክቲኮች ከተቀረው የዓለም ማኅበረሰብ ጋር በደንብ ያልታቀደና ያልተደራጀ ኦፕሬሽን ነበረ፡፡ ለአሜሪካ ፖሊሲም ሆነ መሬት ላይ ያለው እውነታ ለሶማሊያ ማኅበረሰብ ያልተጠበቀና ያልተፈለገ ውጤት አስከትሏል፡፡ እ.ኤ.አ. በ1998 በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ኤምባሲዎቿ በአልቃይዳ ጥቃት ከደረሰባቸው በኋላ በደኅንነት ምክንያት አሜሪካ በቀጣናው የኃይል ዕርምጃ ተጠቅማ የሰብዓዊ ቀውስ የመከላከል ፖሊሲዋን አቋርጣለች፡፡ በአጠቃላይ በ1990ዎቹ አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድ የነበራት የወታደራዊ ዕርምጃ ፖሊሲ እንደተጠበቀው ስኬታማ ሊሆን አልቻለም፡፡

አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድ ስትጠቀም የነበረው ሁለተኛው ስትራቴጂ ፀረ አሜሪካ የሆነን መንግሥት ማወክ (Destabilization) ሲሆን፣ ይህንን ሥልት ስትጠቀም በቀጣናው ባሉ ተቃዋሚ ኃይሎችና ጎረቤት አገሮች አማካይነት አንዱ በሌላው ላይ እንዲነሳ በማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌም በ1990ዎቹ አጋማሽ የሱዳን መንግሥት ለእስልምና አክራሪዎች የሚሰጠውን ሽፋን ለማስቆም የአሜሪካ መንግሥት እንደ ስትራቴጂ የተጠቀመው በቀጣናው ያሉ አጋር አገሮችን በመጠቀም ለሱዳን ተቃዋሚዎች ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ ይህንን ስትራቴጂ በመጠቀም በወቅቱም የአሜሪካ መንግሥት ለእስልምና አክራሪነት ሽፋን ሲሰጥ የነበረውን የሱዳን መንግሥት ከሥልጣን እንዲወገድ ቢያደርግም፣ እ.ኤ.አ ከ1998 እስከ 2000 በኢትዮጵያና በኤርትራ ድንበር የተቀሰቀሰው ግጭት የፀረ አሜሪካ መንግሥትን ማወክ ስትራቴጂ ውጤታማ እንዳይሆን ምክንያት ሆኗል፡፡

ሌላኛው ስትራቴጂ ማዕቀቦችን መጣል ነው፡፡ አሜሪካ የምትጥላቸው እነዚህ ማዕቀቦች ከአሁን ይልቅ በፊት ውጤታማ እንደነበሩ ይገለጻል፡፡ ደቡብ አፍሪካውያን በአፓርታይድ ሥርዓት ሥር በነበሩበት ጊዜ፣ በ1990ዎች የኢራቅን መንግሥት ለማዳከም፣ እንዲሁም በሊቢያ ላይ የተደረጉ ማዕቀቦች ውጤታማ ነበሩ፡፡ በመጀመሪያዎቹ 1990ዎች አሜሪካ ዓለም አቀፋዊ ማዕቀቦች በሱዳን ላይ እንዲጣሉ ብዙ ጉትጎታ ካደረጉት አገሮች የመሪነት ሚና ቢኖራትም፣ እሷ እንደፈለገችው የመላው ዓለም ሕዝብን ድጋፍ ማግኘት ባለመቻልዋ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም፡፡ በወቅቱ በሱዳን ላይ የሚጣሉ ማዕቀቦችን ካወገዙት አገሮች መካከል አንዷ ግብፅ ነበረች፡፡ ምክንያቱም ዕርምጃው በቀጥታ በራሷ ብሔራዊ ጥቅም ላይ አሉታዊ ጎን ስለነበረው ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ እ.ኤ.አ. በ2004 ዓ.ም. በዳርፉር ጉዳይ ላይ የተለያዩ ማዕቀቦችን በሱዳን ላይ እንዲጣል የአሜሪካ መንግሥት ቢፈልግም፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት አባል የሆኑት ሩሲያና ቻይና ማዕቀቦቹ እንዳይጣሉ በማድረግ ሊያጡ የሚችሉትን የራሳቸውን ጥቅም መከላከል ችለዋል፡፡ በወቅቱም በተመድ ውሳኔ ቅሬታ የነበራት አሜሪካ ራሷ በሱዳን ላይ ማዕቀቦችን የጣለች ሲሆን፣ የዳርፉር ቀውስ ከቀጠለ ወደፊትም በርካታ ማዕቀቦችን እንደምትጥል ገልጻ ነበር፡፡ አሜሪካ በሱዳን ላይ የጣለቻቸው ማዕቀቦች በዋናነት ዕርዳታና ኢንቨስትመንት ማቋረጥ፣ ትልልቆቹ ዓለም አቀፍ ተቋማት በአገሪቱ ውስጥ ያላቸውን ሚና መቀነስና የመሳሰሉት ነበሩ፡፡ አሜሪካ በሱዳን ላይ የጣለቻቸው ማዕቀቦች ሱዳንን ክፉኛ ሊጎዱዋት የሚችሉ ቢሆንም፣ የነዳጅ ሀብቷን ለማልማት ከእስያ አገሮች ድጋፍ ማግኘት በመቻልዋ በተወሰነ ደረጃ ማዕቀቦቹን መቋቋም ችላለች፡፡

አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ግንኙነት ፋይዳዎችና ተግዳሮቶች

ኢትዮጵያና አሜሪካ የቆየ የሁለትዮሽ ግንኙነት ያላቸው ናቸው ግንኙነታቸውም ቀስ በቀስ እያደገ ሲመጣ ሁለቱም አገሮች በአፍሪካ ቀንድ አካባቢያዊ ደኅንነትና ንግድ ላይ የተመሠረተ የትብብር ግንኙነታቸውን ይበልጥ አጠናክረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ሲታይ አገሪቷ በምሥራቅ አፍሪካ ከሚገኙት ባርካታ አገሮች ማለትም ከሱዳን፣ ከኤርትራ፣ ከሶማሊያ፣ ከጂቡቲና ከኬንያ ጋር የምትዋሰን ስለሆነች፣ እንዲሁም በአካባቢው የቆየ ታሪክ ስላላት ለአሜሪካ ልዩ የሆኑ ስትራቴጂካዊ ጠቃሜታዎች አሉዋት፡፡

ከ1970ዎቹ ጀምሮ የአሜሪካ ኢኮኖሚ መዳከሙንና የዋጋ ንረቱን እያባባሰ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ፣ በወቅቱ ሥልጣን ላይ የነበሩት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ኒክሰን ችግሮቹን ለመቅረፍ የኒክሰን ዶክትሪንና (ዴታንት) በሚል እንደገና አዲስ የውጭ ፖሊሲ ቀርፀዋል፡፡ የፖሊሲው ዋና ዓላማ የነበረው አሜሪካ በቀጥታ በሌሎች አገሮች የምታደርገውን ወታደራዊ ተሳትፎ መቀነስ እንዳለበት የሚያሳይ ቢሆንም፣ ለተመረጡ ወዳጅ አገሮች በቂ የመሣሪያና ሌሎች ድጋፎችን መስጠት እንዳለባት ይገልጻል፡፡ በወቅቱም የኢትዮጵያ መንግሥት የአሜሪካን ዓለም አቀፋዊ አጀንዳ ባይረዳውም ከአፍሪካ ቀንድ አገሮች ኢትዮጵያ በኒክሰን ዶክትሪን ውስጥ የተካተተች አገር ነበረች፡፡ በመሆኑም እ.ኤ.አ. በ1953 አሜሪካና ኢትዮጵያ 25 የመከላከያ ስምምነቶች ባደረጉት መሠረት፣ በስምምነቱ ኢትዮጵያ በቀጣናው ለአሜሪካ ወዳጅነት ቁልፍ አገር እንደሆነች ተገልጿል፡፡ ስምምነቱ አሜሪካ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ድጋፍና ወታደራዊ ሥልጠና ማድረግ እንዳለባት ሲገልጽ፣ ኢትዮጵያ ደግሞ በበኩሏ ለአሜሪካ ወታደራዊ ጣቢያ ለመስጠት በመስማማት ለመጀመሪያ ጊዜ ቃኘው የተባለው የአሜሪካ ወታደራዊ ጣቢያ እንዲመሠረት ምክንያት ሆኗል፡፡

አሜሪካ በፖሊሲዋ ኢትዮጵያ ስትራቴጂካዊ አጋርዋ መሆንዋ ብትገልጽም፣ ከጊዜ በኋላ ግን ኢትዮጵያ ለአሜሪካ የነበራትን አስፈላጊነት በተለያዩ ምክንያቶች ሊቀንስ ችሏል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያትነት ከተገለጹት መካከል የመጀመሪያው የሳተላይት ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ከመሻሻሉ ጋር ተያይዞ የቃኘው ወታደራዊ ጣቢያ አስፈላጊነት መቀነሱና አሜሪካ ከቃኘው የተሻለ የወታደራዊ ጣቢያ በህንድ ውቅያኖስ የዲያጎ ጋርሺያ ደሴት ላይ ማግኘቷ ነው፡፡ ሌላው ምክንያት አሜሪካ በወቅቱ ኢትዮጵያ ማስተካከል እንዳለበት የገለጸችው አገራዊ ጉዳዮችን ማለትም ዘመናዊ ሕግ ሥርዓት መዘርጋት፣ ለኤርትራ መብቶች መስጠት፣ ሥልጣን ወደታች ማውረድ ወይም የሥልጣን ክፍፍል ማድረግ አለመቻሏ እንደ ምክንያት ተጠቅሷል፡፡

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር የነበራት ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ባትለውጥም፣ ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የሁለቱም አገሮች ግንኙነት እየሻከረ መጥቷል፡፡ ይህ ወቅት ቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት እንደመሆኑ መጠን፣ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች ከመቼውም ጊዜ በላይ ስትራቴጂካዊ ሥፍራ ከመሆኑ የተነሳ ሩሲያና አሜሪካ ቀጣናውን ለመቆጣጠር ፉክክር ውስጥ የገቡበት ጊዜ ነበር፡፡ በወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ወደ ሥልጣን ሲመጡ አሜሪካ ከሌሎች አገሮች ጋር የሚኖራት ፖሊሲ ከሰብዓዊ መብት ማክበር ጋር በመያያዙ፣ እንዲሁም የግራ ዘመም ፖለቲካ አቀንቃኝ የነበረው የደርግ መንግሥት ከአሜሪካ ወታደራዊ ድጋፍ ማግኘት ባለመቻሉ ግንኙነቱን ወደ ሩሲያ ቀይሮታል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር የነበራትን ግንኙነት በማቋረጥ ከ1969 እስከ 1970 ዓ.ም. ድረስ በኦጋዴን ጦርነት ለሶማሊያ ወታደራዊ ድጋፍ አድርጋለች፡፡ ይሁን እንጂ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ግንኙነት በአዲስ መልክ ተጀምሯል፡፡

በዶናልድ ትራምፕ የሥልጣን ዘመን አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድ ሊኖራት የሚችል ፖሊሲ

ሀ. ዶናልድ ትራምፕ በምርጫ ቅስቀሳቸው ወቅት ቀዳሚ ትኩረት ብለው የለዩዋቸው ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ የአሜሪካ ጥቅሞች ሲገመገሙ

45ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ዶናልድ ትራምፕ በአፍሪካ ቀንድ ምን ዓይነት ፖሊሲ አቅጣጫ ሊከተሉ እንደሚችሉ ለማወቅ የመጀመሪያው ተግባር፣ አዲሱ ፕሬዚዳንት በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ያላቸውን በደንብ መመልከት ነው፡፡ ዶናልድ ትራምፕ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ምንም እንኳን የአፍሪካ ቀንድ ፖሊሲው ምን እንደሚመስል በግልጽ ባያስቀምጥም፣ አጠቃላይ የውጭ ፖሊሲውን በመመልከት ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚችል ግን መገመት ይቻላል፡፡ ፕሬዚዳንቱ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የተናገራቸው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ የሚያደርግ ከሆነ የአፍሪካ ቀንድ ፖሊሲው በዋናነት የአካባቢው ደኅንነት፣ ሽብርተኝነትን

ወደ ገጽ 22 ዞሯል

ጨረታ

ግዥ

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የቦሎሶ ሶሬ ወረዳ ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው: - የፋብሪካ ውጤቶችን። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 046-552-03-73 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው:- ጥሬ እንጨቶች። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:-011-558-52-29 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- በደቡብ መንገዶች ባለስልጣን የጉብሬ ዲስትሪክት ጽ/ቤት። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው:- ደንብ ልብስ። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 011-886-88-75 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- ኦሞ ኩራዝ ቁጥር 1 ስኳር ልማት ፕሮጀክት። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው:- የባህር ዛፍ እንጨት። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 011-551-4113 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- ስኳር ኮርፖሬሽን። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው:- የተለያዩ ዕቃዎችን። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 011551-37-06 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው: - የጽህፈትና የጽዳት እቃዎችን። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 0116621802 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ።
በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው:- የተሽከርካሪ ጎማዎችን። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:-0111057-03-33 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- በአራዳ ክ/ከተማ ራስ እምሩ ጤና ጣቢያ። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው:- የቢሮ ዕቃዎችን። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 0111-26-67-12 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- ሜጫ ወረዳ። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው:- አልሙኒየም። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 058-330-04-32 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የኦሮሚያ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ።በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው: - የህትመት ግዥ። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 011369-00-45 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የኪንዶ ኮይሻ ወረዳ ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው:- እንጨት፣ ብረታ ብረትና ሌሎች። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 046-450-02-84 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የኦሮሚያ እንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ቢሮ። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው:- የተለያዩ ዕቃዎችን። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 011-369-00-11 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት። በጨረታ አወዳድሮ መግዛት የሚፈልገው: - የተለያዩ እቃዎችን። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 0114-40-37-65 ይደውሉ።

ኮንስትራክሽን

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሀላባ ልዩ ወረዳ ማረሚያ ቤት። በጨረታ አወዳድሮ ማሠራት የሚፈልገው:- መጸዳጃ ቤትና ሌሎች። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 091091 66 28 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- በአረካ ከተማ አስተዳደር የአረካ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት። በጨረታ አወዳድሮ ማሠራት የሚፈልገው:- መጸዳጃ ቤት። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር: - 046-552-03-53 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ እንስሳትና ዓሣ ሀብት ቢሮ። በጨረታ አወዳድሮ ማሠራት የሚፈልገው:- የተለያዩ ግንባታ። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 046212-17-16 ይደውሉ።

ሽያጭ

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ። በጨረታ አወዳድሮ መሸጥ የሚፈልገው:- የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 0911-20-19-58 ይደውሉ።

ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት:- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ። በጨረታ አወዳድሮ መሸጥ የሚፈልገው:- ትራክተሮችና የእርሻ መሳሪያዎች። ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:-0114-43-05-92 ይደውሉ።

INVITATION TO BID FOR PRINTING SERVICE

Announcement No. 32/2016

Pathfinder International/Ethiopia (PI/E) is a non-for-profit organization dedicated to provide high quality sexual and reproductive health and family planning services that improve the lives of women and their families in Ethiopia.

For its Integrated Family Health Program jointly implemented with JSI Inc, Pathfinder International-Ethiopia intends to purchase printing service for **Family Health Card** as follows:

No.	Description	Specification	Number of Copies
1	Family Health Card (Amharic Version)	Paper size:- A4, Cover page:- 250gm. Glossy paper, Text:- 100 gm art paper, Color:- full color & pages 54 including cover	150,000
2	Family Health Card (Oromiffa Version)	Paper size:- A4, Cover page:- 250gm. Glossy paper, Text:- 100 gm art paper, Color:- full color & pages 54 including cover	50,000

All interested suppliers who fulfill the following minimum criteria are invited to submit formal detailed bids.

- Copy of Renewed Business license for the year 2008/2009 E.C.
- Copy of VAT & Taxpayer Registration Certificate (TIN)
- Deposit 2% **CPO,** not bank guarantee, of the bid amount in the name of Pathfinder International as bid security
- Validity date for the price offer should not be less than one month time after opening of the bid
- Pathfinder will not make any advance payment other than a final payment on complete delivery
- Supplier's offer should be as per the above given specification and proposed delivery date should be indicated in the offer.

The bid will be submitted to the following address:-

IFHP/Pathfinder International Ethiopia

Old Airport area, behind the South African Embassy, In front of Dashen Bank, in a G+6 grey building, 2nd floor- the Logistics & Procurement Office

Tel. 011-320-3501

Bids must be submitted on or before 2:00 pm in the afternoon, Monday December 19, 2016. Bid will be opened on same date, December 19, 2016 in the presence of bidders or their legal representatives at 3rd floor of Pathfinder's conference hall, room No. 304 at 2:30 PM in the afternoon.

Bidders are requested to fulfill all the necessary conditions clearly indicated in advertisement. Pathfinder reserves the right to reject any or all bids.

ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ

TSEHAY INSURANCE S.C

የጨረታ ማስታወቂያ

ኩባንያችን የካሣ ክፍያ ፈፅሞ የተረከባቸውን ተሽከርካሪዎችና የተለወጡ የተሽከርካሪ አካላትን እንዲሁም ሌሎች ንብረቶችን ባሉበት ሁኔታ በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል::

- ተሽከርካሪዎችንና የተሽከርካሪ አካላትን እንዲሁም ሌሎች ንብረቶችን መግዛት የሚፈልጉ ሁሉ ቃሊቲ ቶታል ነዳጅ ማደያ ፊት ለፊት በካፍደም ሲኒማ ወደ ዉስጥ የቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካን አለፍ ብሎ በሚገኘው የኩባንያዉ የተጎዱ ተሽከርካሪዎች ማቆያ ቦታ በመገኘትና በማየት የሚገዙበትን ዋጋ በሰም በታሸገ ኤንቬሎፕ እስከ ታህሳስ 07 ቀን 2009 ዓ.ም. ከቀኑ 11:00 ሰዓት ድረስ ሶማሌ ተራ ሁሉዓለም የንግድ ማዕከል 6ኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው ዋና መ/ቤት ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ገቢ በማድረግ መጫረት ይችላሉ::
- ጨረታው ታህሳስ 08 ቀን 2009 ዓ.ም ከጧቱ 4:00 ሰዓት በኩባንያው ዋና መ/ቤት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል::
- ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዕቃ የመነሻ ዋጋዉን 10% (አስር በመቶ) በባንክ ክፍያ ማዘዣ (CPO) ማስያዝ ይኖርባቸዋል:: ሆኖም የጨረታ ማስከበሪያው ለተሽከርካሪዎች ከብር 5,000.00 (አምስት ሺ) እንዲሁም የተሽከርካሪ አካላት ላይ ከብር 500.00(አምስት መቶ) ማነስ የለበትም::
- ሌሎች ተጫራቶች ባቀረቡት ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ መስጠት የተከለከለ ነው::
- በተሽከርካሪዎችና ሌሎች አካላት ላይ ከጨረታው በፊት ዕዳዎች ቢኖሩ በኩባንያው ይሸፈናል:: በጨረታው ለተካተቱ ንብረቶች ከጨረታው በኂላ ያሉትን ማናቸውም ወጪዎች ገዥው ሙሉ በሙሉ ይሸፍናል::
- የጨረታዉ አሸናፊዎች ያሸነፉበት ዋጋ ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) 15% (አስራ አምስት በመቶ) በተጨማሪነት ይከፍላሉ::
- አሸናፊዎች የጨረታው ውጤት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ እስከ ታህሳስ 20 ቀን 2009 ዓ.ም. ድረስ ክፍያ ፈፅመው ንብረቶቹን መረከብ ዕቃዎቹንም ሙሉ በሙሉ ማንሳት አለባቸዉ:: ይህ ካልሆነ ግን የጨረታው ውጤት የሚሰረዝ ሆኖ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ገንዘብ ለኩባንያው ገቢ ይደረጋል::
- ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 011 111 97 71/70 ወይም 011 126 28 23 በመደወል ወይም ከላይ በተጠቀሰዉ ዋና መ/ቤት በግንባር ቀርቦ መጠየቅ ይቻላል::
- ኩባንያው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ

ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

ሜዲካል አሶሲዬሽን ኦፍፊዚሺያንስ ኢንፕራይቬት ፕራክቲስ - ኢትዮጵያ(MAPPP-E) በሚከተለዉ የሙያ ዘርፍ ተወዳዳሪዎችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል።

የሥራ መደቡ መጠሪያ:.................................ሾፌር

ተፈሳጊ ችሎታ

10ኛ ክፍል አጠናቆ ስለ መኪና በቂ የቴክኒክ እውቀት ያለው (በቴክኒክ እና ሞያ ዲፕሎማ ቢኖር ይመረጣል)

- የአዉቶሞቢል እና ከዛ በላይ/ የአሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለዉ
- ዋስ ማቅረብ የሚችል

የሥራ ልምድ:

ሁለት ዓመት እና ከዛ በላይ በማሽከርከር ሞያ ልምድ ያለው :: የድርጅት ተሽከርካሪ የማሽከር ልምድ ኖሮት መንግስታዊ ባልሆኑ ልማታዊ ድርጅቶች የሰራ ቢሆን ይመረጣል::

ብዛት:...................................... 1

የሥራቦታ:-................................ አዲስ አበባ

ደመወዝ:- .... በስምምነት

ከላይ የተጠቀሰውን መሥፈርት የምታሟሉ ተወዳዳሪዎች አፍሪካ ጎዳና (ቦሌ መንገድ) ሳይ ኬክ ቤት ጀርባ ወይም ራማዳ ሆቴል ፊት ለፊት በሚገኘዉ የመንግስት ቤቶች አፓርታማ ላይ የማህበሩ ፅ/ቤት አንደኛ ፎቅ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰባት ተከታታይ የሥራ ቀናት ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 2:30 - 6:30 ከሰዓት 7:30-11:30 ቅዳሜ 2:30 - 6:30 ማመልከቻና ኮፒ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ በመያዝ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን::

ለተጨማሪ መረጃ:- ስ.ቁ0911-242-386

ዝክረ ፊደል...

ከገጽ 40 የዞረ

አትረሳቸውም፤›› ሲሉም በአጽንዖት ተናግረዋል::

በደም የተሳሰረው የኩባና የኢትዮጵያ ወዳጅነት ለዘላለም ይኖራል ያሉት ደግሞ በኢትዮጵያ የኩባ አምባሳደር ሁዋን ማኑኤል ሮድርጌዝ ባስካስም፣ ፊደል ለኩባውያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ፍትሕ የላቀ አስተዋጽኦ ያደረጉ ነበሩ ብለዋል::

ዓርብ ነሐሴ 7 ቀን 1918 ዓ.ም. ተወልደው፣ ዓርብ ኅዳር 16 ቀን 2009 ዓ.ም. በዘጠና ዓመታቸው ያረፉት አብዮታዊው መሪ ፊደል ካስትሮ ሥርዓተ ቀብር፣ በዕለተ ሰንበት የተፈጸመው የኩባ አብዮት በተወለደባት ሳንቲያጎ ዴኩባ ከተማ ነው:: ከመዲናይቱ ሃቫና ከአራት ቀናት ጉዞ በኋላ ለሥርዓተ ቀብር የበቃው አስክሬኑ ተቃጥሎ በአመድ መልክ ነው:: ፕሬዚዳንት ሙላቱ ተሾመን ጨምሮ የተለያዩ አገሮች መሪዎች በተገኙበት፣ ለ49 ዓመታት ኩባን የመሩት ፊደል ካስትሮ ግብአተ አመድ ሲፈጸም ለቀስተኞቹ ‹‹ፊደል ለዘለዓለም ይኑር!›› ‹‹እኔም ፊደል ነኝ!›› ሲሉ መሰማታቸው የዜና አውታሮች ዘግበዋል::

ተቀጽላ - የሳርትር ምስክርነት

ሳርትር ከምዕራባዊው ሥልጣኔ ታላቅ ፈላስፋዎች አንዱ በልቦለዶቹ፣ ባጫጭር ልብ ወለዶቹ፣ በትያትሮቹ ብቃት ደሞ ከፈረንሳይ ሥነ ጽሑፍ ቁንጮዎች አንዱ ነው:: የኖቤል ሽልማትን እምቢ አልቀበለውም፤ ኢምፔሪያሊዝም እኔን አይሸልመኝም ያለ ሰው ነው:: በሂትለር ወረራ ዘመን ህቡዕ (ድብቅ) አርበኛ ነበረ:: ሰውየው ይሁዲ ነው:: አጭር ነው፣ ጠንጋራ ነው፣ ወፍራም መነፅር ያረጋል:: ሴቶች በጣም ይወዱታል:: ከሳርትር ምስክርነት በትንሹ እነሆ በማለት:: ‹‹እነሆ ጀግና!›› ብሎ በጻፈው መጽሐፉ ያወሳው ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ነበር::

‹‹እነፊደል ካስትሮ የሥራ ሰዓት የዕረፍት ሰዓት ብለው አይለዩም:: ቢሮዋቸው ታጣፊ አልጋ አለ:: እንቅልፍ ሲመጣ እሱ ላይ ይተኛሉ:: ሲነቁ ወደ ሥራ ነው:: ካስትሮን ሕዝቡ ይወደዋል:: ሕዝቡና መሪው እኩል ሲዋደዱ ብዙ ጊዜ አያጋጥምም::

‹‹አንድ ቀን ካስትሮ እነ ሳርትርን ሲያስጎበኝ የነሱ መኪናዎች ተከትለውት የሱ መኪና ፊት ፊት እየሄደ ወደ አንድ ጫካ ገቡ መንገዱን ተከትለው:: ብዙም ሳይሄዱ አንድ በጣም ግዙፍ የሆነ ጥቁር ሰውዬ ድንገት ከጫካው ብቅ ብሎ መንገዳቸው ላይ ቆመ:: መትረየስ ይዟል:: ቁም! አለ፤ ቆሙ::

‹‹እኔ ፊደል ካስትሮ ነኝ››

‹‹አውቅሀለሁ:: በል አሁን አዙርና በመጣህበት ተመለስ››

‹‹ስማ:: እነዚህ የውጭ አገር እንግዳዎቻችን ናቸው››

‹‹ይሁኑ:: እነሱ ሊያልፉ ይችላሉ ከፈለጉ:: አንተ ግን ትመለሳለህ››

‹‹እንትንን (የቦታ ስም) ላስጎበኛቸው እኮ ነው››

‹‹በዛኛው መንገድ ውሰዳቸው››

‹‹ያ ሁሉ ዙሪያ ጥምጥም፣ ይህ አቋራጭ እያለ? ጊዜያችንን ለምን እናባክናለን?››

‹‹ይኼ ጫካ ስለሆነ:: ጠላት አደጋ ሊጥልብህ ስለሚችል:: አሁን እኔ ጠላት ልሆን እችል ነበር:: አንተስ ሞትክ ነው አለቀልህ፤ እኛ ግን ከዚያ በኋላ ምን እንሆናለን? አታስብልንም?››

እነ ካስትሮ እነ ሳርትር አዙረው በዙሪያ ጥምጥሙ መንገድ መሄድ ግድ ሆነባቸው:: ፊደል ካስትሮ የዚህ ሰውዬ ነገር ሳይከነክነው አልቀረም:: ለማንኛውም ተስፋዬ ገሰሰ አጋጥሞት አይቶ የነገረኝ እነሆ:: ለተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ወደ ኒውዮርክ ሲመጡ ከፕሬዚዳንቶቹ ሁሉ የማን አጀብና ጓዝ ይበዛል? የፊደል ካስትሮ:: ሀርለም ውስጥ (የጥቁሮች ሰፈር) ነበር ያረፈው ካስትሮ:: ሆቴሉን በሙሉ የያዙት እነካስትሮ ናቸው:: ምክንያቱም ካስትሮ ሲአይኤን አያምንም:: ዛሬ ተበልቶ የዛሬ ወር የሚገድል መርዝ ቢያበሉትስ? ለሞትም ሳይሆን ለበሽታ ቢዳርጉትስ? ያልጠረጠረ ተመነጠረ ነው፤ ወዳጄ:: ስለዚህ በግስ ዶሮስ ድንችንስ ምንስ - ካስትሮ የሚበላውና የሚጠጣው ከኩባ ይዞት የመጣውን ብቻ ነው::

‹‹ካስትሮ ለሕዝቡ በሬድዮና በቴሌቪዥን ሲናገር ለሰዓታት ነው:: አንድ ጊዜ ከአሥር ሰዓት በላይ ተናግሯል:: በሌላ ኮሚኒስት አገር ቢሆን ሕዝቡ ፈርቶና ተገዶ ነው የሚያዳምጠው:: ኩባውያን ታዲያ ካስትሮ ንግግር ያደርጋል ሲባል አብዛኛውን ሌላ የግል ፕሮግራማቸውን ሰርዘው ያዳምጡታል:: ብዙ ተማሪዎች እሱን ለማዳመጥ ሲሉ ከትምህርት ይቀራሉ (ይፎርፋሉ)::

ብዙ ኩባውያን እንዲህ ይላሉ ‹‹የሶሻሊዝም ጎዳና ባይመችም፣ ችግር ቢበዛበትም፣ ፊደል ካስትሮ መንገዳችን ነው ብሎ እስከመረጠው ድረስ ለእኛ መንገዳችን ነው:: እሱ እንሂድ እስካለ ድረስ እንሄዳለን::››

ባጭሩ ፊደል ካስትሮ ነፃ አውጪ ብቻ ሳይሆን የሕዝቡ ውድ መሪ ጭምር ነው::

ጋዜጠኛ መቼስ እፍረት አያውቅም:: አንዱ ፊደል ካስትሮን ‹‹ለምን ጢምዎን አይላጩትም?›› ብሎ ጠየቀው::

መልስ ‹‹እኔ የምላጨው አገሬ ምላጭ ስታመርት ነው››



ከ33 ዓመት በፊት የቆመው ትግላችን ሐውልት እግርጌው ከተሰጠፈ የፊደል ካስትሮ ምስል ጋር (ፎቶ በሔኖክ ያሬድ)

ማስታወቂያ

Premier Switch Solutions (PSS)

INVITATION TO BID

For "RFP for Appointment of QSA and ASV for PCI DSS Compliance"
Floating Date: As of December 8, 2016

Closing Date: January 9, 2017

Tender No.: PSS/Bids/002/2016

1. Premier Switch Solutions (PSS) invites all interested and eligible bidders by this National competitive Bid(NCB) for **"RFP for Appointment of QSA and ASV for PCI DSS Compliance"**. Tender No.: PSS/Bids/002/2016

The Tender remains floating from December 8, 2016 to January 9, 2017.

Bid Documents can be obtained from PSS's Head Office, the Insurance Tower of Awash Headquarters Building, 7th Floor, during Office hours, Monday to Friday 8:00 a.m. to 5 p.m. and on Saturday 8:00 a.m. to 12:00 p.m., upon payment of a non-refundable fee of Birr 500.00 (Birr Five Hundred only).

2. All interested bidders are expected to fulfill the Requirements stated herebelow.
   2.1. Availability of bid security;
   2.2. Availability of Letter of Authorization to sign the bid offers;
   2.3. Tax clearance certificate for the year
   2.4. Renewed trade license for the year 2009 EC
   2.5. Bidders should be VAT registered.
3. All Bids must be accompanied by a bid security in the amount of Birr 50,000.00 (BirrFifty Thousand only) or
   3.1. The bid bond shall be furnished in one of the following forms: -
      a. Certified Cheque /CPO issued by a recognized domestic bank or
      b. Unconditional bank guarantee
   3.2. Sealed bids marked as: "RFP for Appointment of QSA and ASV for **PCI DSS Compliance"** and be addressed to:

Premier Switch Solutions,

RasAbebeAregay Road,

Awash Towers

6th floor, Insurance Tower,

P. O. Box 45072, Addis Ababa, Ethiopia.

Bid proposal will be received at PSS's Head Office, on January 9, 2017until 5:00 P.M.. Bids received after the closing time will be automatically rejected and shall be returned unopened to the bidder.

4. Bids received in time and fulfilling the other formalities shall be opened in the presence ofinterested bidders or their legal representatives January 10, 2017 at 10:00 A.M at the Meeting Room of PSS.
5. PSS reserves the right to reject all or parts of this bid.
6. No one is allowed to duplicate or transfer the bidding document that she/he acquired to participate under this invitation.
7. Bidders are seriously advised to read and comply with the instructions provided in this bidding document.
8. Partial bid is not allowed

የኢትዮጵያ ባሌስትራ ፋብሪካ ኤም.ቢ. አክሲዮን ማህበር
Ethiopian Spring M.B. Share Company

የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ጥሪ

የኢትዮጵያ ባሌስትራ ፋብሪካ ኤም.ቢ. አክሲዮን ማህበር (Ethiopian Spring M.B. Share Company) የ 2009 በጀት ዓመት አፈፃፀም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ጥሪ በሚከተሉት አጀንዳዎች ላይ ለመነጋገር ታህሳስ 19 ቀን 2009 ዓ.ም (December 28,2016) በአክሲዮኑ ጽ/ቤት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በመገኘት ስብሰባ ለማድረግ ወስኗል፡፡

አጀንዳ፡-

1. እ.ኤ.አ. እስከ ጁን 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ለተከናወነው የሥራ ዓመት የኩባንያውን የዳይሬክተሮች ቦርድ የአፈፃፀም ሪፖርት መስማት፣
2. እ.ኤ.አ እስከ ጁን 30 ቀን 2016 ዓ.ም ለተከናወነው አፈፃፀም የሥራ ዓመት የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት መስማት፣
3. ከላይ በቀረቡት ሁለት ሪፖርቶች ላይ በመወያየት ማጽደቅና በተገኘው የዓመቱ ትርፍ ላይ መወሰን፣
4. የቀጣዩን 2017 በጀት ዓመት የውጭ ኦዲተር መሾምና ክፍያውን መወሰን፣
5. ሌሎች ከመደበኛ ጉባኤው ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ መነጋገር ናቸው፡፡

ሪዬስ ኢንጂነሪንግ አክሲዮን ማኅበር
Ries Engineering Share Company

EXTERNAL VACANCY ANNOUNCEMENT

Ries Engineering Share Company invites qualified applicants to apply for the following vacant position:

1.	Position	ELECTRICIAN I
2.	Educational Qualification	10+3/Diploma in Auto Electricity from recognized Technical School
3.	Experience	Minimum 4 years work experience on maintenance of Caterpillar earth moving machinery electrical system and power generators in workshop and field
4.	Other Requirement	Good command of written and spoken English Good knowledge of caterpillar Software (ET, SIS, etc.) 2nd Grade Driving License Computer Knowledge
5.	No. Required	1

Interested applicants are required to submit their applications with full CV and other supporting documents within 10 (ten) working days of the issuance of this announcement to:

Ries Engineering Share Company
Human Resource
P.O.Box 1116
Addis Ababa

ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ የግል ጤና ተቋማት አሰሪዎች ማህበር በሚከተለዉ የሙያ ዘርፍ ተወዳዳሪዎችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል፡፡

የሥራ መደቡ መጠሪያ፡..............................ሾፌር

ተፈላጊ ችሎታ፡-

10ኛ ክፍል አጠናቆ ስለ መኪና በቂ የቴክኒክ እውቀት ያለው(በቴክኒክ እና ሞያ ዲፕሎማ ቢኖር ይመረጣል)

- የአዉቶ ሞቢል እና ከዛ በላይ/ የአሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለዉ
- ዋስ ማቅረብ የሚችል

የሥራ ልምድ፡

ሁለት ዓመት እና ከዛ በላይ በማሽከርከር ሞያ ልምድ ያለው፡፡ የድርጅት ተሽከርካሪ የማሽከር ልምድ ኖሮት መንግስታዊ ባልሆኑ ልማታዊ ድርጅቶች የሰራ ቢሆን ይመረጣል፡፡

ብዛት፡......................................1

የሥራቦታ፡-................................አዲስ አበባ

ደመወዝ፡- ....በስምምነት

ከላይ የተጠቀሰውን መሥፈርት የምታሟሉ ተወዳዳሪዎች ሀይሌ ገ/ስላሴ መንገድ(22 አካባቢ) ካፒታል ሆቴል እና ስፓ አጠገብ በሚገኘዉ የማህበሩ ፅ/ቤት ገሊላ ሕንጻ ሁለተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 15 ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰባት ተከታታይ የሥራ ቀናት ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 2:30 - 6:30 ከሰዓት 7፡30-11:30 ቅዳሜ 2:30 - 6:30 ማመልከቻና ኮፒ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ በመያዝ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ስተጨማሪ መረጃ፡- ስ.ቁ 0911-745-875

ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

ድርጅታችን ደብሊው ኤ የዘይት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር አንድ ኤክስኪዩቲቭ ሴክሬታሪ ቀጥሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም አስፈላጊውን ፎርማሊቲ የምታሟሉ አመልካቾች ማስታወቂያው ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ቦሌ ቴሌ መድሀኒዓለም ሽገር ህንጻ አጠገብ ባለው አስፋልት ሶስት መቶ ሜትር ገባ ብሎ ጉርሻ ሬስቶራንት አጠገብ በሚገኘው በድርጅቱ ቢሮ ኦርጅናል የትምህርት ማስረጃ፣ የሥራ ልምድ ከፎቶ ኮፒ ጋር በማቅረብ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የሥራው ዓይነት፡.....................................ኤክስኪዩቲቭ

ብዛት፡....................................አንድ

ጾታ፡ ....ሴት

ተፈላጊ የትምህርት ችሎታ፡

በሴክሬታሪያል ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላት

የሥራ ልምድ፡ ....አምስት ዓመት እና ከዚያ በላይ

የቋንቋ ችሎታ፡

እንግሊዝኛ ቋንቋ በቂ ችሎታ ያላት፣ የኢንተርኔትና ኢ-ሜል አጠቃቀም ግንዛቤ እና ልምድ ያላት በተጨማሪ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ እና አረብኛ ለምትችል ቅድሚያ እንሰጣለን፡፡

ደመወዝ፡.................................በስምምነት

ስተጨማሪ ማስረጃ
ስልክ ቁጥር 0911647164/0911301345

World Vision Ethiopia

Invitation to Bid (Pre-qualification) for Office Furniture Provision, Ref. No. 054/16

WVE invitespotential suppliersto prequalify for the provision of different Office Furnitures.

Bid document/Terms of Reference shall be collected fromoffice #3by showing copy of renewed Trade License and paying birr 50, 11:00AM to 12:00PM or 3:00PM-4:00PM,Monday to Friday during December 06-18, 2016.WVE islocated at Gerjithe way to MebratHaylnext to Anbessa Garage, Addis Ababa. For further information, please call us via Tel. No.011 6291079.

Each bidders shall submit its sealed and stamped technicalproposal (including copies of renewed Trade License, Business Registration License,Tax Payer's Registration&VAT Certificates) duly marking the envelope as 'Original'.The proposal shall be delivered to office #3 in the bid box from *11:00AM to 12:30PM ONLY* on December 19, 2016. Bid proposals will be opened at 03:00PM on the same dateby the Procurement Committee.Following the completion of technicalevaluation, the best bidders will be contacted.

Note: The best bidders shall be required to present evidence of criminal check from authorized body and will receive adequate orientation on our Child Protection Policy, must sign onto it and comply with the standards stated in the Policy.

World Vision Ethiopia reserves the right to accept or reject all or any parts of the bid at any time without assigning any reason whatsoever.

የኢትዮጵያ መድኃኒት ፋብሪካ አ.ማ ETHIOPIAN PHARMACEUTICALS MANUFACTURING Sh.Co.

ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

የሥራ መደቡ መጠሪያ፣.... የጥራት ማረጋገጫ ፋርማሲስት

ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና
የሥራ ልምድ፣......................... በፋርማሲ የመጀመሪያ ዲግሪ እና 2 ዓመት በመድኃኒት ማምረት የሠራ/ች፣ ጥሩ የመድኃኒት አመራረት ዘዴ እና የኮምፒዩተር ስልጠና ያለው/ያላት

ብዛት .... 2 /ሁለት/

ደመወዝ .... በድርጅቱ እስኬል መሰረት

የቅጥር ሁኔታ .... በቋሚነት

የሥራ ቦታ............................... አዲስ አበባ

ከላይ የተጠቀሰውን መስፈርት የምታሟሉ አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ ሰባት ተከታታይ የሥራ ቀኖች ውስጥ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃዎችን ዋናውን ከማይ መለስ ፎቶ ኮፒ ጋር በመያዝ በአክሲዮን ማህበሩ ፐርሶኔል ዋና ክፍል በመቅረብ ማመልከት የም ትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

አድራሻ

የኢትዮጵያ መድኃኒት ፋብሪካበሣር ቤት መስመር ከብሥራተ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ወረድ ብሎ በሚገኘው አደባባይ በስተ ቀኝ በኩል

ስልክ 0113 71 10 00/0113 71 55 12

External Vacancy Announcement

Oromia Insurance Company S.C &Oromia Coffee Farmers Cooperative Union Lt

Vacancy No: HQBCPO /02/16

Oromia Insurance Company S.C and Oromia Coffee Farmers Union Ltd are two different institutions operating in insurance and coffee farming industry, respectively. Both have joined hands to construct a mega structure of Head Quarters with 35 storeys.

In order to run the construction project properly, the institutions have planned to set up a project management office with necessary human resource and material facilities.

Therefore, Oromia Insurance Company S.C and Oromia Coffee Farmers Union Ltd invite qualified applicants for the following job positions:

1. Job Position : Manager, Finance and Administration

Education : At least BA Degree in Accounting or Accounting and Finance
Experience : Eight years financial or administrative experience out of which four years as Manager in finance project management.

2. Job Position : Senior Architect

Education : At least MSc/BSc degree in Architectural Engineering.
Experience : At least 8 years service in Architectural engineering
Work place : Head Quarter project Office/Finfinne/
Terms of employment : Contract /Definite period for one year with possibility of extension based on performance

3. Job Position : Secretary

Education : Diploma in Secretarial Science and Office Management or related fields.
Experience : A minimum of four years experience in Secretarial work and Office Management. An experience of Project Management Office is Advantageous.

Notes for all positions:

- Work place is Head Quarter Project Office (Finfinne);
- Terms of employment is for a definite period of one year with possible extension;
- Lucrative Salary and Benefits packages that is subject to negotiation;

Skills required:

Good Report writing, Good Communication and Proficiency in Amharic & English languages are required and knowledge of Afan Oromo is also advantageous.

Interested applicants fulfilling the above minimum requirements should send application letter with non-returnable CV and copies of credentials through our postal address given below up to December 16, 2016 and note that only shortlisted applicants will be contacted.

OROMIA INSURANCE COMPANY S.C.
Human Resource and Facility Management Dep't
P.O.BOX 10090Addis Ababa, Ethiopia
Address: Africa Avenue (Bole Road) around Olympia
Oromia International Bank Building, 6th Floor

የተመራጩ ፕሬዚዳንት አዳማ ባሮው ደጋፊዎች በዋና ከተማዋ ባንጁል ደስታቸውን ሲገልጹ

የጋምቢያውያንን ሥጋት ያረገቡት ተሰናባች ፕሬዚዳንት

የዛሬ አምስት ዓመት ነው፡፡ በወቅቱ ሥልጣን ከያዙ 17 ዓመታትን ያስቆጠሩት የጋምቢያው ፕሬዚዳንት ያህያ ጃሜ ጋምቢያን ለአንድ ቢሊዮን ዓመታት እንደሚገዙ ከቢቢሲ ጋር በነበራቸው ቃለ ምልልስ ተናገሩ፡፡ ይህን ንግግራቸውን የሰሙ ጋምቢያውያን በተለይም የፕሬዚዳንቱ ተቃዋሚዎች ጃሜ በሰላም ሥልጣን ላይለቁ እንደሚችሉ ቢገምቱም፣ በምርጫ ከመሳተፍ አልተቆጠቡም፡፡ ባለፈው ሳምንት ማጠናቀቂያ በተካሄደው ምርጫ የተሳተፈው የሰባት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥምረት መሪ አዳማ ባሮው በምርጫው አሸናፊ ሆኑ፡፡

ለአንድ ቢሊዮን ዓመት በሥልጣን እንደሚቆዩ ተናግረው የነበሩት ያህያ ጃሜ፣ በምርጫው ከተሸነፉ በኃላ ያሳዩት አቋም ከሕዝቡ ሥጋት፣ ከፖለቲካ ተንታኞች ትችት የተለየ ነበር፡፡

በምርጫው ውጤት ሳቢያ በአገሪቱ ብጥብጥ ሊነሳ ይችላል ተብሎ የተሠጋ ቢሆንም፣ ተሰናባቹ ፕሬዚዳንት ለዚህ ዕድል አልሰጡም፡፡ መንግሥታቸው በምርጫው ዕለት መራጩ ሕዝብ በስልክም ሆነ በማኅበራዊ ድረ ገጾች ተጠቅሞ ለብጥብጥ የሚያነሳሱ መልዕክቶችን እንዳያስተላልፍ በመላ አገሪቱ ዓለም አቀፍ የስልክ ጥሪዎችም ሆኑ የኢንተርኔት አገልግሎቶች እንዲቋረጡ አድርጎ ነበር፡፡ ‹‹የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነቶችን ያቋረጥኩት በአገሪቱ በምርጫ ሰበብ ብጥብጥ እንዳይነሳ ለማረጋገጥ ነው፤›› ሲል የጋምቢያ መንግሥት አስታውቋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ በምርጫ ላሸነፏቸው ባሮው በሞባይል ስልክ በመደወል ደስታቸውን መግለጻቸውንና በውጤቱ ላይም ተቃውሞ እንደሌላቸው መናገራቸውም ተገልጿል፡፡

ቢቢሲ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥምረትን ጠቅሶ እንዳሰፈረው ለ22 ዓመታት አገሪቱን የመሩት ጃሜ በባለሀብቱ ባሮው ተሸንፈዋል፡፡ የአገሪቱ ምርጫ ኮሚሽንም ባሮው 45 በመቶ ድምፅ ሲያገኙ፣ ጃሜ ደግሞ 36 በመቶ አግኝተዋል ሲል ፕሬዚዳንቱ ሥልጣናቸውን እንደሚያስረክቡ አሳውቋል፡፡

‹‹ፈጣሪ የእኔ ጊዜ እንዳበቃ ነግሮኛል፡፡ ሥልጣኔን ለጋምቢያውያንና ለአንተ ክብር ስል በደስታ አስረክባለሁ፤›› በማለት በስልክ ለባሮው እንደነገሯቸው ተገልጿል፡፡

በ22 ዓመታት የሥልጣን ዘመናቸው ተቃዋሚዎቻቸውን በማሰቃየትና ዝም በማሰኘት የሚታወቁት ጃሜ በምርጫ መሸነፋቸው እንደተሰማ አንዳንድ ዜጎች የእሳቸው ምሥል ያለበትን ፖስተር መቅደዳቸውን፣ የመንግሥታቸው ወታደሮችም ምንም እንዳላሉ፣ አንዳንዶችም መኪና ላይ ሆነው ‹‹ነፃነት! ነፃነት!›› ሲሉ እንደነበሩ ዘገባዎች አመልክተዋል፡፡

እኚህ መሪ በማንኛውም ሥፍራ ሲዘዋወሩ በማይለያቸው መቁጠሪያ (በክርስትናና በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ፀሎት በሚደረግበት ጊዜ በእጅ የሚያዝ፣ ፀሎት ባይኖርም እጅ ወይም አንገት ላይ የሚጠለቅ) እና በትር የሚታወቁ ሲሆን፣ ለየት ያሉና የሚፈልጉትን ለማግኘት ማንኛውንም ዕርምጃ የሚወስዱ ናቸው፡፡

የተወለዱት እ.ኤ.አ በ1965 ሲሆን ሥልጣን የያዙት ደግሞ በ1994 ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ1984 የጋምቢያን መከላከያ ኃይል በመቀላቀል በ1989 ምክትል የመቶ አለቃ ማዕረግ ያገኙ ሲሆን፣ በ1992 የወታደራዊ ፖሊስ አባል ሆነው አገልግለዋል፡፡ በጋምቢያ ጎረቤት በሴኔጋል እንዲሁም በአላባማ ከፍተኛ ወታደራዊ ሥልጠና ወስደዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ1994 መንግሥት በሙስና ተዘፍቋል በማለት ከጋምቢያ ወጣት የመከላከያ አባላት ጋር በመሆን፣ የወቅቱ የአገሪቱን ፕሬዚዳንት ዳውድ ጃዋራ በመፈንቅለ መንግሥት አስወግደዋል፡፡

መፈንቅለ መንግሥቱ ያለምንም ደም መፋሰስ የተከናወነ ሲሆን፣ ከፕሬዚዳንቱ ወገንም እዚህ ግባ የሚባል ምላሽ አልገጠማቸውም ነበር፡፡ ራሱን ‹‹አርምድ ፎርስስ ፕሮቪዥናል ሩሊንግ ካውንስል (ኤኤፍፒአርሲ) እያለ የሚጠራው የመፈንቅለ መንግሥት አድራጊ ቡድኑ መሪም ነበሩ፡፡

ፕሬዚዳንት ጃሜ ‹‹አሊያንስ ፎር ፓትሪዮቲክ ሪኦሪንቴሽን ኤንድ ኮንስትራክሽን›› የተባለ ፓርቲ በመመሥረት እ.ኤ.አ በ1996 ምርጫ አካሂደዋል፡፡ በወቅቱ የውጭ ምርጫ ታዛቢዎች ምርጫው ነፃና ፍትሐዊ አይደለም ቢሉም፣ እ.ኤ.አ በ2001 በተደረገው ምርጫ መንግሥት በመራጮች ላይ ጣልቃ ከመግባቱ በቀር በተሻለ ሁኔታ ነፃና ፍትሐዊ እንደነበር አስታውቀዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ2006 የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ባደረጉባቸው ላይ የዕድሜ ልክ እስራት አስፈርደዋል፡፡ በአገር ክህደት ወንጀልም ሞት የተፈረደባቸው አሉ፡፡

ራሳቸውን ለእስልምና እምነት ማስገዛታቸውንና ብዙ ተዓምራት እንደሚያደርጉ፣ እ.ኤ.አ በ2007 ኤድስን ከዕፅ በሚቀመም በድኃኒት መፈወስ እችላለሁ በማለት የዘርፉ ተመራማሪዎችን እንዳነጋገሩና አስከትለውም የሴቶችን የመውለድ ችግር እንደሚፈቱ መናገራቸው ይታወሳል፡፡

ግብረ ሰዶማዊነትን አጥብቀው የሚያወግዙ ሲሆኑ፣ እ.ኤ.አ በ2014 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጉባዔ ላይ ባደረጉት ንግግርም ግብረ ሰዶማዊነት ትውልድን የሚያጠፋ ድርጊት መሆኑን በመጥቀስ፣ ምዕራባውያን ግብረ ሰዶማዊነት እንደ መብት እንዲከበር የሚያደርጉትን ጥረት አውግዘዋል፡፡ በአገራቸው ግብረ ሰዶማዊ ከተገኘም አንገቱ/ቷ እንደሚቀላ አስጠንቅቀው ነበር፡፡

የፕሬስና የሲቪል ማኅበረሰቡን የሐሳብ ነፃነት በመገደብና ነፃነትን በማፈን ከሚወቀሱት ጃሜ ሥልጣን የሚረከቡት የ51 ዓመቱ አዳማ ባሮው፣ ንብረቶችን በማስተዳደርና ሪል ስቴት በማልማት የሚታወቁ ባለሀብት ናቸው፡፡ በሕይወት ዘመናቸው በመንግሥት ቢሮ ያልሠሩ ሲሆን፣ በእንግሊዝ በትምህርት ላይ በነበሩበት በ2000ዎቹ መጀመሪያ፣ በለንደን በሚገኘው አርጎስ ካታሎግ ስቶር የደኅንነት ባለሙያ ሆነው አገልግለዋል፡፡

ጋምቢያ ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነፃ በወጣችበት እ.ኤ.አ በ1956 የተወለዱ ሲሆን፣ በምርጫ ቅስቀሳቸው ወቅት ነፃና ገለልተኛ የፍትሕ ሥርዓት፣ የመገናኛ ብዙሃንና ሲቪል ማኅበረሰብ እንዲኖርና የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ እንደሚሠሩ ተናግረዋል፡፡

በጃሜ የሥልጣን ዘመን በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ ጋምቢያውያን ለሥራ ፍለጋ ተሰደዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከዚህ ቀደም በሕይወት ዘመናቸው ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር አይተውና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ሠርተው ለማያውቁት ተመራጩ ፕሬዚዳንት የቤት ሥራ ነው፡፡ ቢቢሲ እንደሚለው የአገሪቱን ዜጎች ከስደት ለመታደግ የተቀናጀ የሥራ ፈጠራ፣ እንዲሁም የሥራ ዕድል የሚፈጥር ሥርዓት መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ባሮው በምረጡኝ ቅስቀሳቸው ወቅት የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከብሔርና ከሃይማኖት ጋር የተደበላለቀ መሆኑን በመናገር፣ ችግሩን የሚፈታ የኢኮኖሚ ፖሊሲና የፍትሕ ሥርዓት እንደሚዘረጉ አስታውቀው ነበር፡፡ በጋምቢያ ላለፉት 22 ዓመታት የተንሰራፋውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ የሃይማኖትና የብሔር ጽንፈኝነትና በአድልኦ የተሸበበ የፍትሕ ሥርዓት አቃንተው የጋምቢያውያንን በነፃነት የመኖር ፍላጎት ያረኩ ይሆን? የሚለው ጥያቄ የብዙዎች ነው፡፡w

ተመራጩ ፕሬዚዳንት አዳማ ባሮው በምርጫው ማሸነፋቸው ከተገለጸ በኋላ

ከሃያ ዓመታት በላይ ጋምቢያን የመሩት ያህያ ጃሜ ሽንፈታቸውን በፀጋ መቀበላቸውን የአገሪቱ የምርጫ ኮሚሽን አረጋግጧል

የተሸናፊው ፕሬዚዳንት ያህያ ጃሜ ደጋፊዎች

ጋምቢያውያን ድምፃቸውን ለመስጠት ወረፋ ይዘው ሲጠባበቁ

በዘጠና ዓመታቸው ላረፉት የኩባ አብዮታዊ መሪ ፊደል ካስትሮ መታሰቢያ፣ ኅዳር 25 ቀን 2009 ዓ.ም. በትግላችን ሐውልት ስር ሲከናወን፣ በኩባ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ከልጆቻቸው ጋር

ፎቶ በሪፖርተር/ በሔኖክ ያሬድ

ሕይወት እንደ ታክሲ

መነሻ መድረሻ አበጅቶ
ርቀት ተመን ሰጥቶ
ቦታ አቅጣጫን ለክቶ
የጉዞ መስመሩን አጣርቶ
የተሳፋሪውን መድረሻ እየጠራ
እንደየ ጉዞው በየስፍራ
ከተሳፋሪው ላይ እንደየርቀቱ
በታሪፍ በዋጋ ተቀብሎ በጥቂቱ
መንገዱን ሾፌሩ ሒሳቡን ረዳቱ
ያደርሳሉ ካሰቡበት ቦታ
ከመድረሻው ከፌርማታ
ልክ እንደ ታክሲ የለም ተራ
ሾፌሩ አንተውነህ ሕይወት ምትመራ
ጠርቶ እሚወስድህ ካሰብክበት ስፍራ
አላማህ ነው አቅጣጫህን የሚመራ
ተስፋ ነው ረዳትህ ነዋይ እሚያፈራ
ስኬት ነው መድረሻህ ቦታ
በህልፈት ነው ጉዞው እሚገታ
የሕይወትህ ጅረት መቋጫ ፌርማታ፡፡

በታሪኩ ከበደ፣ ምክረ ሰይጣን፣ (2008)

የሰዎች የግል መረጃን መለጠፍ መቀነስ ፌስቡክን አሳስቧል

በፊት በፊት ሰዎች የግል መረጃቸውን ማለትም የግል ሕይወታቸውን የሚመለከቱና ምናልባትም በፌስቡክ አደባባይ መለጠፍ የሌለባቸውን መረጃዎች ይለጥፉ ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን ፌስቡክ ሰዎች እንደዚህ ያሉ መረጃዎችን ይበልጥ እንዲለጥፉ በሚያበረታታ መልኩ ገጹን ምቹ ቢያደርግም ሰዎች እነዚህን መረጃዎች መለጠፍ እየቀነሱ መሆኑ ፌስቡክን እንዳሳሰበ ዘ ኢንዲፔንደንት ዘግቧል፡፡ የተሠራ ጥናት እንደሚያሳየው፣ ሰዎች ብዙ ጉዳዮችን በፌስቡክ ገጻቸው እየለጠፉ ያሉበት ጊዜ ቢሆንም፣ የሚለጠፉት ነገሮች ብዙዎቹ ስለሰዎች የግል ሕይወት ሳይሆን ስለ ዓለም ሁኔታ ናቸው፡፡ ይህ ምናልባትም ሰዎች ከመቼውም የበለጠ ግንኙነት ስላላቸው የግል መረጃቸው ለዚህ ሁሉ እንዲደርስ ካለመፈለግ ሊሆን ይችላል፡፡

ቤተሰቦች በራሳቸው የሚተማመኑ ልጆችን ለማፍራት ማድረግ ያለባቸውን የሥነ ልቦና ባለሙያዎች ጠቆሙ

በራስ መተማመን ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያስተምሩት፤ የሚያበረክቱት ስጦታ ነው፡፡ በልጅ አስተዳደግ ላይ 16 መጽሐፎችን የጻፉት የሥነ ልቦና ባለሙያው ካርል ፒክሀርት፣ በራስ መተማመን የሌላቸው ሕፃናት አዲስና፣ ፈታኝ ነገሮችን ብሞክር እወድቃለሁ፣ ሌሎችም ተስፋ ይቆርጡብኛል ብለው የሚፈሩ ናቸው ይላሉ፡፡ ይህ ደግሞ በወደፊት ሕይወታቸው የተለያዩ ነገሮችን ሞክረው ስኬታማ እንዳይሆኑ እንቅፋት ይሆንባቸዋል፡፡ ‹‹በራስ የመተማመን ጠላት መሳነፍና ፍርኃት ናቸው፡፡ ስለዚህም ልጆቻችሁ አዲስና ትንሽ የሚፈትናቸውን ነገር እንዲያደርጉ አበረታቷቸው›› ይላሉ፡፡

የሥነ ልቦና ባለሙያው ጠቃሚ ከሚሏቸው ነገሮች መካከል ልጆች አሸነፉ ተሸነፉም ጥረታቸውን ማድነቅ፣ ብቃታቸውን የሚያዳብሩበትን መንገድ ማበረታታት፣ ያስቸገራቸውን ነገር በራሳቸው እንዲፈቱ መተውና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

ልጇን በማደንዘዝ ታስተኛ የነበረችው እናት ተከሰሰች

ሚቼላ ፓይክ የተባለች የ37 ዓመት እናት ከፍቅረኛዋ ጋር በመተባበር ሕፃን ልጇ ፖፒን የእንቅልፍ መድሃኒት፣ ሔሮይንና ሌሎችንም በመደባለቅ እየሰጠች ለስድስት ወራት ያህል ለማስተኛት በመሞከሯ፣ የአራት ዓመቷ ፖፒም በዚህ ምክንያት ሕይወቷ በማለፉ ክስ ተመሥርቶባት ፍርድ ቤት መቅረቧን ዘ ኢንዲፔንደንት ዘግቧል፡፡ ዘገባው እንደሚያመለክተው፣ እናትየው ይህን ታደርግ የነበረው ከፍቅረኛዋ ጋር ጥሩ ጊዜ ለማሳለፍ በማሰብ ነበር፡፡ ሕፃኗ በወሰደቻቸው የመድሃኒትና የአደንዛዥ እፅ ድብልቆች በልብ ሕመም የሞተችው እ.ኤ.አ. 2013 ላይ ነው፡፡ የእናትየውን አፓርትመንት የፈተሸው ዶክተር አንድ ሺሕ የመድሃኒት እንክብሎችን ማግኘቱም ታውቋል፡፡

ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

የኦሮሚያ የግል ጤና ተቋማት ማህበር በሚከተለዉ የሙያ ዘርፍ ተወዳዳሪዎችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል።

የሥራ መደቡ መጠሪያ:.................................ሾፌር

ተፈላጊ ችሎታ:-

10ኛ ክፍል አጠናቆ ስለ መኪና በቂ የቴክኒክ እውቀት ያለው (በቴክኒክ እና ሞያ ዲፕሎማ ቢኖር ይመረጣል)

- የአዉቶሞቢል እና ከዛ በላይ/ የአሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለዉ
- ዋስ ማቅረብ የሚችል

የሥራ ልምድ:

ሁለት ዓመት እና ከዛ በላይ በማሽከርከር ሞያ ልምድ ያለው ። የድርጅት ተሽከርካሪ የማሽከር ልምድ ኖሮት መንግስታዊ ባልሆኑ ልማታዊ ድርጅቶች የሰራ ቢሆን ይመረጣል።

ብዛት:.................................1

የሥራ ቦታ:.........................አዳማ

ደመወዝ:-..........................በስምምነት

ከላይ የተጠቀሰውን መሥፈርት የምታሟሉ ተወዳዳሪዎች አዳማ ከደራርቱ አደባባይ ወደ መብራት ሃይል በሚወስደ ዉ መንገድ ላይ በሚገኘዉ አዳማ አዲ ሃዉስ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 212 ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰባት ተከታታይ የሥራ ቀናት ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 2:30 - 6:30 ከሰዓት 7:30-11:30 ቅዳሜ 2:30 - 6:30 ማመልከቻና ኮፒ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ በመያዝ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን።

ለተጨማሪ መረጃ:- ስ.ቁ0911-388-652

መስፍን ሰለሞን ኮንስትራክሽን

የጨረታ ማስታወቂያ

የመስፍን ሰለሞን ኮንስትራክሽን ሲገለገልባቸው የነበሩትን ተሽከርካሪዎች ከባለአክሲዮኖቹ መካከል ተወክለው በመጡት እና በቦርድ ስራ አመራር አማካኝነት በተደረገው አስቸኳይ ስብሰባ ተሽከርካሪዎቹ እንዲሸጡ የተወሰነ ስለሆነ ተሽከርካሪዎቹ ባሉበት ሁኔታ በጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል።

ለጨረታ የቀረቡ ተሽከርካሪ ዓይነቶች

1. ኤሮትራከር ሞዴል 2004 ብዛት 1
2. ፍራንኮን ሞዴል 2013 ብዛት 1

በመሆኑም በጨረታው ላይ መወዳደር የምትፈልጉ ተጫራቾች:-

1. ተሽከርካሪዎቹ በሚገኙበት ስፍራ ተገኝታችሁ መመልከት ትችላላችሁ፤
2. ተጫራቾች ስለጨረታው ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ከዚህ በታች የተገለጹትን ስልኮች መጠቀም ትችላላችሁ 0911665518፣ 0911480111፣ 0911691418፣ 0929028251
3. ተጫራቾች በጨረታው ሰነድ ላይ መወዳደር የፈለጋችሁትን ተሽከርካሪ በግልፅ ማመልከት ይኖርባችኋል
4. ሌሎች ተጫራቾች ባቀረቡት ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይቻልም፤
5. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው
6. የጨረታው ጊዜ ይህ ማስታወቂያ ለህዝብ ከተገለጠ በኋላ ባሉት 7 (ሰባት) ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ ይሆናል፤
7. ተሽከርካሪዎቹ የሚገኙበት ስፍራ ውንጌት አደባባይ ባለው የመኪና ማቆሚያ ቦታ፤
8. የጨረታ ሰነዱን የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት በሚገኝበት ቂርቆስ ክ/ከተማ ከደንበል ሲቲ ሴንተር ወረድ ብሎ ወደ መስቀል ፍላወር በሚወስደው መንገድ 200 ሜትር ገባ ብሎ በሚገኘው የሲኒመር ትሬዲንግ አ.ማ. ገበያ ማዕከል ውስጥ ነው ስልክ ፣ 0911480111፣ 0911691418፣ 0948300957 0911665518፣ 0118290751

ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ በአዋጅ ቁጥር 97/90 (እንደተሻሻለው) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በዋስትና የያዘውን ንብረት በሐራጅ ይሸጣል።

ተ.ቁ	የተበዳሪው ስም	የንብረት አስያዥ ስም	ለጨረታ የቀረበው መያዣ ንብረት	አበዳሪው ቅርንጫፍ	ንብረቱ የሚገኝበት አድራሻና የቦታ ስፋት					የጨረታ መነሻ/ዋጋ በብር	የጨረታዉ ቀንና ሰዓት		ጨረታው የወጣ
					ከተማ	ወረዳ	ቀበሌ	የካርታ ቁጥር	የቦታ ስፋት በካ.ሜ		ቀን	ሰዓት	
1.	ኮምቦልቻ አግሮ ኢንዳስትሪ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር	ተበዳሪው	መጋዘን	አፍሪካ ጎዳና	ኮምቦልቻ			5023/ኮ/ቴ/ኮገ/406.97	4087	1,745,883.40	27/04/09	3:00-5:00	ለሁለተኛ ጊዜ
2.	አቶ ታምሩ ፀጋዬ	ተበዳሪው	መኖሪያ ቤት	መርካቶ	ቡራዩ		ገፈርሳ ቡራዩ	Bur/8163/2001	105	610,071.15	03/05/09	4:00-6:00	ለመጀመሪያ ጊዜ
3.	አቶ ሙስጠፋ ዳዋኖ	ተበዳሪው	መኖሪያ ቤት	ኡታ ዋዩ	ሻሻመኔ		አዋሾ 01	LHC NO 7186	200	168,358.15	02/05/09	3:00-5:00	ለመጀመሪያ ጊዜ

- ተጫራቾች ከጨረታው ቀን በፊት ንብረቶቹ በሚገኙበት አድራሻ ቀርበው ማየት ይችላሉ፡
- ተጫራቾች የጨረታውን መነሻ ዋጋ 25% የጨረታ ማስከበሪያ ቦንድ በባንክ ክፍያ ማዘዣ ሲ.ፒ.ኦ አሰርተው ከጨረታው ቀን በፊት ማስያዝ ወይም ጨረታው በሚካሄድበት ዕለት ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ይዘው መቅረብ ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
- ጨረታው በሰንጠረዡ ላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ባለዕዳዎቹ ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው፣ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸውና ታዛቢዎች በተገኙበት ተ.ቁ 1 በኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ (ኮምቦልቻ ከተማ) ፤ተ.ቁ 2 በኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ ቡራዩ ቅርንጫፍ ፤ ተ ቁ. 3 በኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ ኡታ ዋዩ ቅርንጫፍ (ሻሻማኔ ከተማ) ውስጥ ይካሄዳል ።
- ጨረታውን ያሸነፈው ተጫራች ያሸነፈበትን ዋጋ በ15 ቀን ውስጥ ለባንኩ ገቢ ማድረግ ይኖርበታል።
- ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ገቢ የማያደርግ ተጫራች ጨረታው ተሰርዞ ያስያዘው ገንዘብም አይመለስለትም።
- በባንኩ ብድር ፖሊሲ መሰረት የሚፈለገውን ማስረጃ አሟልቶ የቀረበ የጨረታ አሸናፊ ብድርን በተመለከተ ቀርቦ የባንኩን የብድር መምሪያ ማነጋገር ይችላል።
- ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 011 557 2106/07 ዋናው መ/ቤት ወይም ለተ.ቁ 1. በ0115586382 አፍሪካ ጎዳና ቅርንጫፍ፤ ለተ.ቁ. 2 በ0112758648/43/42 መርካቶ ቅርንጫፍ ለተ.ቁ 3 በ046 2110062/73 ኡታ ዋዩ ቅርንጫፍ ደውሎ መጠየቅ ይቻላል።
- ባንኩ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ወይም ብድሩ ከተከፈለ ጨረታውን የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
- ጨረታውን ያሸነፈ ተጫራች ለመንግስት የሚከፈለውን አስፈላጊ ግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፍላል።
- የጨረታው አሸናፊ በቀሪ የሊዝ ዘመን የሚከፍለውን ክፍያ ለመክፈል ንብረቱ በሚገኝበት የከተማ አስተዳደር በመቅረብ የሊዝ ውል ይዋዋላል።

ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

አዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

ADDIS INTERNATIONAL BANK S.C.

የውጭ አገር ዜግነት ሳላችሁ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የአዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ ባለአክሲዮኖች

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቁጥር FIS/01/2016 ባወጣው መመሪያ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጪ አገር ዜጎች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ውስጥ የአክሲዮን ባለቤት ለመሆን እንደማይችሉ በወጣው የሀገሪቱ ሕግ መሠረት ባለአክሲዮን ሆነው ለመቀጠል የማይችሉ በመሆኑ በባንኮች ውስጥ ያላቸውን አክሲዮን በመተው አክሲዮኑን በአክሲዮኑ ላይ በተፃፈበት ዋጋ /Par Value/ መሰረት ባለአክሲዮን ለሆኑበት ባንክ መመለስ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም በትውልድ ኢትዮጵያውያን ሆናችሁ የውጭ አገር ዜግነት ያላችሁ የአዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ ባለአክሲዮኖች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ከ ህዳር 18 ቀን 2009 ዓ.ም (እ.ኤ.አ ከ November 27 2016) ጀምሮ ባሉት 60 ተከታታይ ቀናት ውስጥ፡-

1. የአክሲዮን ባለቤትነት ደረጋገጫ ምስክር ወረቀታችሁን ለባንኩ በመመለስ በባንኩ ውስጥ ያላችሁን የአክስዮን ድርሻ ለአክሲዮን ግዥ የከፈላችሁትን ገንዘብ በአክሲዮኑ ላይ በተፃፈበት ዋጋ /Par Value/ መሠረት ባምቢስ አካባቢ ዝቋላ ህንፃ ላይ በሚገኘው የባንኩ ዋና መ/ቤት ከአካል በመቅረብ ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻችሁ አማካኝነት እንድትወስዱ ፡፡
2. እስከ ሰኔ 23 ቀን 2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ እስከ ጁን 30 ቀን 2016) ድረስ ያላችሁን የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት በአካል በመቅረብ ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻችሁ አማካይነት እንድትወስዱ፡፡
3. የባንኩን አክሲዮን ገዝታችሁ ይህ ማስታወቂያ እስከወጣበት ቀን ድረስ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ያለባችሁን ክፍያ ባለመክፈላችሁ ወይም በሌላ ምክንያት የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያልወሰዳችሁ ባለአክሲዮኖች የምስክር ወረቀት አለመውሰዳችሁ ከባንኩ ባህር መዝገብ ላይ ተመሳክሮ ከተረጋገጠ በኋላ ገንዘባችሁን ባንኩ የሚመልስላችሁ መሆኑን፡፡
4. ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይህንን ግዴታቸውን መወጣት ያልቻሉ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ባለአክሲዮኖች በባንኩ ውስጥ ያላቸውን የባለአክሲዮንነት መብት ሙሉ በሙሉ በመሰረዝ የአክሲዮን ድርሻቸው ለባንኩ ተመላሽ የሚደረግ ሲሆን አክሲዮን የገዙበት ገንዘብ አክሲዮኑ ላይ በተፃፈበት ዋጋ / Par Value / መሠረት ታስቦ በተከፋይ ሒሳብ ተይዞ የሚቀመጥ መሆኑን፡፡
5. ከሰኔ 23 ቀን 2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ ከጁን 30 ቀን 2016) በኋላ በአክሲዮኑ መጠን መሰረት የሚሰላ የትርፍ ድርሻ የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን የማይከፈል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ተጨማሪ መረጃ በ 011 557 05 06/011 557 05 12 በመደወል ማግኘት ይችላሉ

አዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

CAFOD, SCIAF and Trócaire

VACANCY ANNOUNCEMENT

INTERNAL/EXTERNAL

CAFOD, SCIAF and Trócaire (CST) represent the official development agencies of the Catholic Church in England and Wales, Scotland and Ireland. In Ethiopia, the three agencies work jointly to address the poverty alleviation and humanitarian crisis through our local, international NGOs and the catholic church of Ethiopia. Trocaire (on behalf of CAFOD, SCIAF and Trocaire) is implementing a three year project **Enhancing resilience to Climate Change and increasing income of pastoralist, agro-pastoralist and drop-out pastoralist communities in three drought –prone districts of Borana zone, Southern Ethiopia.** The project will be implemented through our partners mainly Agency for cooperation and research in development (ACORD) and Community Initiative Facilitation and Assistance(CIFA).

Trocaire is currently looking for an Ethiopian citizen for the position of Program Officer based in Addis Ababa, Ethiopia. The Project officer will report toLivelihood Programme Coordinator.

Job Purpose

To contribute to CAFOD/SCIAF/Trocaire's involvement in Ethiopia in line with the agreed strategy, by taking the lead on the day-to-day management of a UKAM5-funded project that is mentioned above.

The scope of the post falls into the following broad functions ;

- **Programme management and development in line with the direction set by the Country/Sub-regional Strategy:** in co-operation with partners, developing and managing CST- supported long-term development project;
- **Managing effective relationships with partners:** developing and nurturing partnerships and providing or facilitating capacity development support, where appropriate;
- **Internal and external representation:** of the Joint **CAFOD/SCIAF/Trocaire** programme, in co-ordination with the Livelihood Programme Coordinator, Communication Officer and Programme Manager , as appropriate;
- **Financial management and monitoring of programmes and projects:** developing and managing budgets, and monitoring expenditure in line with agreed parameters;
- **Systems and compliance:** ensuring the effective use of CST's systems to share programme knowledge and inform decision making. This includes ensuring compliance with agreements, regulations and requirements attached to our work;

Job Specific Requirements;

- Understanding and first-hand experience of institutional funding work/projects, priorities, trends and donor conditions including EU and DFID;
- Experience using programme cycle management tools effectively to deliver work within an agreed project framework;
- Able and committed to working with and developing the capacity of local partners organisations/ National NGOs and Capacity to bring expertise and experiences of all organizations to the project.
- Experience in networking and the establishment of a working partnership with Oromia government offices at regional, zonal and district levels.
- Financial management understanding and experience;
- Ability and willingness to travel and spend 50% of his/her time at project site, sometimes at short notice and to areas of potential risk
- Languages: Fluent written and spoken English, Amharic and desirably Oromifa'.

Closing date: completed application form should be submitted by e-mail only to reception@cst-together.org by COB December 21, 2016.

Interested applicants can get Application form and Job Description from CAFOD website http://cafod.org.uk/Work-with-us/International-Jobs/Prog-Officer-Ethiopia

Sending Curriculum Vitae is not acceptable.

CST is an equal opportunities employer. Recruitment and selection procedures reflect our commitment to child protection.

ኪ ን ና ባ ህ ል

ዝክረ ፊደል ካስትሮ

በ‹‹ትግላችን ሐውልት››

በሔኖክ ያሬድ

ኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ አራተኛውን የአብዮት በዓሏን መስከረም 2 ቀን 1971 ዓ.ም. ለማክበር የመዲናይቱ ነዋሪዎች ከመሪዋ ጋር በአዲስ አበባ ከተማ አብዮት አደባባይ ከትመዋል:: ርእሰ ብሔሩ ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የዕለቱን የክብር እንግዳቸው፣ ቁርጠኛ ወዳጃቸው የወቅቱ የኩባ ፕሬዚዳንት ፊደል ካስትሮ ሩዝን ሊቀበሉ በዳግማዊ ምኒልክ ጎዳና በታላቅ አጀብ ቦሌ ኢንተርናሽናል ኤርፖርት ደርሰው ይጠብቁ ነበር:: ፊደል ካስትሮን የያዘው አደሮፕላን ግን ድምፁ አልተሰማም::

ፕሬዚዳንቱ በመዘግየታቸው ሊቀመንበሩ ወደ አብዮት አደባባይ ተመለሱ በአደባባዩም የሦስቱን ዓመታት ‹‹ትግልና ድል›› የሚዘክር መሰናዶ እያዩ አዲስ በታነፀው ሰገነት ላይ ሆነው ይከታተሉ ጀመር::

አብዮታዊ ዲስኩራቸውን እያሰሙ ባሉበት ሰገነት ላይ አንዱ ተጠግቷቸው ፊደል ካስትሮ አዲስ አበባ መድረሳቸውን ነገራቸውና ንግግራቸው አቋርጠው ሊቀበሏቸው ቦሌ ዘለቁ:: አቀባበልም ተደረገላቸው:: ከቦሌ እስከ አብዮት አደባባይ ግራና ቀኝ የተሰለፉት በተለይ የከፍተኛ 18 እና ከፍተኛ 19 ነዋሪዎች አጀቡን አደመቁት:: ‹‹ቪቫ መንግሥቱ ቪቫ ካስትሮ›› እየተባሉ በቅብብሎሽ ከአደባባዩ ደረሱ:: ዘውዳዊ ምልክቱ በመደሻና ማጭድ በተተካው በቀይና ግልጽ ማርቸዲስ አውቶሞቢል ቢሆንም አደባባዩን ዞሩ:: ይህ ከሆነ ድፍን 38 ዓመት ሆነው::

የኢትዮጵያ ቁርጠኛ ወዳጅ፣ ከ40 ዓመት በፊት ወረራ የፈጸመችባትን ሶማሊያ ለመግታት ከ15 ሺሕ በላይ ወታደሮቿን አሰልፋ ከደም ጠብታ እስከ መስዋዕትነት የተሰለፈችው ኩባ መሪዋ ፊደል ካስትሮ ከ40 ዓመት በፊትም በ‹‹ቀውጢው ዘመን›› አዲስ አበባ ጎራ ብለው ነበር:: መጋቢት 5 ቀን 1969 ዓ.ም. በወቅቱ አጠራር በኢምፔሪያሊስቶችና በአድኅሮት ያረብ አገሮች አጋፋሪነት ምሥራቅ ኢትዮጵያን ወርራ የያዘችውን የዚያድ ባሬ ሶማሊያን ሃይ ለማለት መትጋታቸው አልቀረም:: የሁለቱ አገሮች ጦርነት የቀዝቃዛው ጦርነት አካል የሶቭየት ኅብረትና የአሜሪካ፣ የሶሻሊስቱና የካፒታሊስቱ ዓለም ጎራ ዐውደ ውጊያ ሆኖ የታየበት ነበር::

እስከ አፍንጫዋ ታጥቃ የነበረችው የምዕራቡና የዓረቡ ዓለም ድጋፍ የነበራት ሶማሊያ፣ ከአሜሪካ ጦር መሣሪያ በገንዘቧ ገዝታ ‹‹ዓይንሽን ላፈር›› የተባለችውን ኢትዮጵያን እስከ 700 ኪሎ ሜትር ድረስ ድንበር ጥሳ ወሰን አፍርሳ ሕዝብ አፈናቀለች::

የፊደል ካስትሮና የኢትዮጵያ ሌላኛዋ ወዳጅ የደቡብ የመን (የመን ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ) ሶሻሊስት ፓርቲ መሪው አብዱልፈታህ እስማኤል ጭምር የተደረገው የማደራደር ጥረት አልተሳካም::

ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ‹‹ትግላችን›› ባሉት የመጀመሪያው መጽሐፋቸው እንደጻፉት፣ የፕሬዚዳንት ፊደል ካስትሮና የፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ እስማኤል የኤደን ሽምግልና ሳይሳካ ቀረ::

‹‹ጓድ ፊደል ሲቀበሉን ጦርነቱን ገጥመን፣ የተሸነፍን ይመስል በማዘንና በመጨነቅ ሊያፅናኑን ሞከሩ:: ሶማሊያዎች ውጊያውን ሊያሸንፉ ይችላሉ:: በጦርነቱ አሸናፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው በማለት እኛ መልሰን አፅናናናቸው::››

ሊቀመንበር መንግሥቱ የካስትሮ ምላሽንም በመጽሐፋቸው አስፍረውታል:: ‹‹ልክ ናችሁ በጦርነት አሸናፊው አብዮት ነው:: እኛ የጠላነው፣ ለአጭር ጊዜም ቢሆን መሸነፋችንን በመገመት ነው::››

ጦርነቱ የኢትዮጵያና የሶማሊያ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ጎን በአጋርነት የተሰለፉት የኩባና የደቡብ የመን ጭምር መሆኑ ነው:: አለፍ ሲልም የምዕራቡና የምሥራቁ ዓለም የአንድ ክንፍ ፍልሚያ::

‹‹ተነሥ ታጠቅ ዝመት አብዮታዊት እናት አገርህ ተደፍራለች›› በሚለው ‹‹ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት›› ዘመቻ፣ የኩባም የየመንም ወታደሮች ታከሉበት:: በፍልሚያው ጎራ በምሥራቅና በደቡባዊ ምሥራቅ የዘመቱት እርመኛ ወታደሮች ለአገር ነፃነት ተሰዉ::

የነዚያ ጀግና ወታደሮች ልጆችም የፊደል ካስትሮዋ ኩባ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ዕድል ሰጠች:: በወሳኙ የጦር ግንባር ‹‹ቆሬ›› እና በ‹‹መንግሥቱ ኃይለ ማርያም›› ስም ትምህርት ቤቶችንም መሠረተች::

‹‹ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ

እንደ ሆቼሚኒ እንደ ቼጉቬራ›› እያለ ያቀነቀነው ያ ትውልድ ፊደል ካስትሮም ታካዩ ነው:: የኢትዮጵያ አብዮት በተቀጣጠለበት የሶሻሊስት ርዕዮት የሚያንፀባርቁ መጻሕፍት በየፈርጁ በተተረጐመበት ጊዜ አንዱ የኩባ አብዮት ታሪክ ነበር:: የአዲስ አበባን ገበያንም ይዞት ነበር::

አራተኛው አብዮት በዓል በሶማሊያ ላይ ከተገኘው ድል በኋላ የተከበረ በመሆኑ ልዩ ስፍራ ነበረው:: ከ1968 እስከ 1970፣ እንዲሁም ከ1972 እስከ 1983 የአብዮት በዓል መስከረም 2 ብቻ ነበር:: ፊደል ካስትሮ የተገኙበት የ1971 ዓ.ም. የአብዮት በዓል ግን በመስከረም 2 ብቻ አልተገደበም:: በማግስቱ መስከረም 3 ቀን በወታደራዊ ሰልፍ መከበሩ ይታወሳል:: ‹‹ትግል ድል›› የተሰኘው

ፎቶ በሪፖርተር/ሔኖክ ያሬድ

ትግላችን ሐውልት አጥር የተሰቀለው የፊደል ካስትሮ ምስል

ታላቅ ዐውደ ርዕይም በሸገር ሜዳ አሜሪካ ኤምባሲ ፊት ለፊት የአሁኑ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ ተቋም ቅጥር ግቢ ሲታይ ፊደል አካሉ ነበሩ::

ኩባ ለኢትዮጵያ ከ40 ዓመት ወዲህ የደረሰች እንግዳ አልነበረችም:: በታሪክ እንደሚወሳው ከ80 ዓመት በፊት ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስትወር ኩባዊው አልሲንዳሮ ለነፃነት ተዋግቷል:: ‹‹ቀይ አንበሳ›› የተሰኘ መጽሐፉንም የዘመነ ፋሺስት ወረራን አስመልክቶ መጻፉና ወደ አማርኛም መተርጐሙ ይታወሳል::

የአዲስ አበባው መታሰቢያ

እሑድ ኅዳር 25 ቀን 2009 ዓ.ም. ጠቅላይ ፖስታ ቤት ፊት ለፊት፣ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ጀርባ በሚገኘው ‹‹ትግላችን›› ሐውልት አደባባይ የኢትዮጵያና የኩባ ሰንደቅ ዓላማዎች እየተውለበለቡ ይታያሉ:: በእጅ የሚያዙትም ጭምር:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ‹‹የኢትዮ ኩባ ወዳጅነት ፓርክ›› የሚል ስያሜ በታከለበት ትግላችን ሐውልት ዋናው መግቢያ ላይ በስፓኒሽ፣ በእንግሊዝኛና በአማርኛ መግለጫ ‹‹ፊደል ለዘላለም ይኖራል!!›› የሚል በግርጌ የሰፈረበት የፊደል ካስትሮ ምስል ይታያል::

‹‹ለኢትዮጵያ አንድነት ለሕዝቡና አብዮቱ ሲታገሉ ጥለው ለወደቁ የሕዝብ ልጆች የቆመው መታሰቢያ›› ላይ የኩባን አብዮት ከጫካ እስከ ከተማ ከነቼጉቬራ ጋር መርተው ለድል ያበቁት ፊደል የትግል ዘመናቸው ፎቶ ተሰቅሎበታል:: ‹‹ለእኛነታችን መሠረት ነህ! እናመሰግንሃለን›› የሚል ጽሑፍና የፊደል ፎቶ ያለበት ጥቁር ካኔቴራ ያጠለቁ በኩባ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ከነልጆቻቸው ፎቶ እየተነሱ ነበር::

‹‹ታማኝ›› የሚል ትርጉም ያለውን ‹‹ፊደል›› ከፊደል ካስትሮ ወስደው ለልጆቻቸው መጠርያ የሰየሙም አሉ::

በተጣለው ዳስ ውስጥ የኩባ ሙዚቃ ሞገድ አሳብሮ ይደመጣል:: ተወዳጁ የዚያን ዘመን አዲስ አበቤዎች የማይረሷት ‹‹ሁዋንታ ላሜራ›› የብዙዎችን ስሜት ቀስቅሳለች:: ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ‹‹እነሆ ጀግና›› ብሎ ባሳተመው የአገር ቤትና የውጭ አገር ጀግኖች መካከል የተወሳው ያልተረሳው ፊደል ካስትሮ ነበር::

‹‹ ‘ሁዋንታ ላሜራ’ የምትባለውን መዝሙራቸውን የሰማ ሊገምት እንደሚችለው የኩባ ሕዝብ ሙዚቃና ዳንስ በጣሙን ይወዳል:: በጣሙን ይችልበታል:: ይታያችሁ እንግዲህ ያ ሕዝብ በዚያ ቀን [በአብዮቱ የድል ቀን] መንገዶቹን ሞልቷቸው እየዘፈነ፣ እየደነሰ፣ እየተሳሳመ:: አንድ ሕዝብ አንድ ባህል አንድ ቀን:: ከእንግዲህ ደሞ አንድ ፓርቲ፣ አንድ መሪ ፊደል ካስትሮ::››

በመታሰቢያ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የተገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ኩባውያን፣ ዲፕሎማቶች በሐዘን መግለጫ መዝገብ ላይ ሲፈርሙ፣ ከዋናው ሐውልት (ትግላችን) በተጨማሪ በግራና በቀኝ (በደቡብና በሰሜን) የተተከሉ ለኢትዮጵያ ደማቸውን ካፈሰሱ ኩባውያን ወታደሮች መካከል የ162ቱ ወታደሮች ፎቶና ስም ያለበትን ቅጥር ይጎበኙ ነበር::

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ የቀድሞው ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ በዕለቱ ባስተላለፉት መልዕክት፣ የኢትዮጵያና ኩባ ወዳጅነት በደም የተሳሰረና ለዘላለም እንደሚቀይ ገልጸዋል::

‹‹ፊደል ካስትሮ ኢትዮጵያ በአስቸጋሪ ወቅት በነበረችበት ጊዜ ከእኛ ጋር በመሆናቸው አገራችን መቼም

ወደ ገጽ 33 ዞሯል

በኢትዮ ኩባ ወዳጅነት ፓርክ፣ በትግላችን ሐውልት ግራ እና ቀኝ ለኢትዮጵያ መስዕዋት ለሆኑት የኩባ ወታደሮች ከቆሙት የመታሰቢያ ሐውልቶች አንዱ

ምን እየሠሩ ነው?

‹‹ያለው አሠራር ዕድል አይሰጥም››

አቶ ፍቅሬ ዘውዴ፣

የዲጂታል ኦፖርቹኒቲ ትረስት በኢትዮጵያ ዳይሬክተር

አቶ ፍቅሬ ዘውዴ ይባላሉ፡፡ የዲጂታል ኦፖርቹኒቲ ትረስት በኢትዮጵያ ዳይሬክተር ናቸው፡፡ ድርጅቱ የተቋቋመው በ1994 ዓ.ም. ካናዳ ውስጥ ነው፡፡ በወጣቶች የሊደርሺፕ ክህሎትና በሥራ ፈጠራ ዙሪያ ኢትዮጵያን ጨምሮ በሌሎች አምስት የአፍሪካ አገሮች ይሠራል፡፡ የተቋቋመው የወጣቶችን ሥራ አጥነት ለመቀነስ እንዲሁም ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ ወጣቶችን ለሥራ ብቁ የሚያደርጉ የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ተፈላጊውን የሰው ኃይል ለማብቃት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ከተቋቋመ ሰባት ዓመታትን ቢያስቆጥርም በደንብ መስራት የጀመረው ከ 3 አመታት ወዲህ ነው፡፡ ድርጅቱ ባለፈው ሣምንት በራስ አምባ ሆቴል በሥራ ፈጠራ ሥኬት ያስመዘገቡ ሰዎች ለወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ልምዳቸውን የሚያጋሩበት መድረክ አዘጋጅቶ ነበር፡፡ በዕለቱ ከተገኙ ወጣቶች በቀላሉ ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉ የቢዝነስ ሐሳቦችን የማፍለቅ ውድድርም ተካሂዶ ነበር፡፡ የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሻሂዳ ሁሴን ዳይሬክተሩ አቶ ፍቅሬ ዘውዴን አነጋግራቸዋለች፡፡

ሪፖርተር፡- ድርጅቱ የሚያተኩረው በምን በምን ጉዳዮች ላይ ነው?

አቶ ፍቅሬ፡- ወጣቶች ተቀጥሮ ለመሥራት የሚያስችላቸውን የተለያዩ ሥልጠናዎች እንሰጣለን፡፡ ቢዝነስ የመፍጠር፣ ቢዝነስን የማሳደግ፣ ቢዝነስን ከደንበኞች ጋር የተዋሃደ እንዲሆን የሚያስችሉ የተለያዩ ሥልጠናዎች እንሰጣለን፡፡ በቀላል አገላለፅ ቢቻል ተቀጥረው አለዚያ የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው ለመሥራት የሚያስችላቸውን ክህሎት በሥልጠና እንዲያዳብሩት እናደርጋለን፡፡ በተለይ የተማሩ ወጣቶች ላይ ስንሠራ አይሲቲን ለቢዝነሳቸው እንዲጠቀሙ ተጨማሪ የአይሲቲ ሥልጠና እንሰጣቸዋለን፡፡

ሪፖርተር፡- በሴቶች ላይ በተለየ የምትሠሯቸው ፕሮግራሞች አሉ? እስቲ በሴቶች ዙሪያ ስለምትሠሯቸው ሥራዎች ይንገሩን?

አቶ ፍቅሬ፡- የምንሰጣቸውን ሥልጠናዎችና የቢዝነስ ዴቨሎፕመንት አገልግሎቶች በተቻለ መጠን ሴቶች ባሉበት ሆነው እንዲደርሳቸው የምናደርግበት አሠራር አለን፡፡ የሥልጠናዎችን ተደራሽነት በተመለከተ ሴቶች በመደበኛ የሥልጠና ፕሮግራም ላይ ለመገኘት በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይመቻቸው ይችላል፡፡ ስለዚህም እነሱ ባሉበት አካባቢ፣ በሚመቻቸው ሰዓት ሥልጠናውን በግሩፕ የሚያገኙበትን ሁኔታ እናመቻችላቸዋለን፡፡ በተጨማሪም ምን ዓይነት ሥልጠና ብንሰጣቸው የተሻለ እንደሚሆን ከእነሱ መረጃ በመሰብሰብ ሥልጠና የሚሰጥበትን መንገድ በመቀየስ የበለጠ የተመቸ እንዲሆን እናደርጋለን፡፡ ሴቶች እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ፣ ሥኬታማ ከሆኑ ሴቶች ጋር የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ የምናደርግበትንና ጠቃሚ ሆነው ያገኘናቸው አሠራሮችም አሉን፡፡ የተለያዩ ፕሮግራሞቻችንን የምናደርሰው ኢንተርኖቻችንን በመጠቀም ነው፡፡ የሴቶች ሴቶችን መርዳትን ታሳቢ በማድረግም ቢያንስ 50 በመቶ የሚሆኑ ኢንተርኖቻችን ሴቶች እንዲሆኑ የምናደርግበት ሁኔታም አለ፡፡

ሪፖርተር፡- ኢንተርን ሆነው በድርጅታችሁ አገልግሎት የሚሰጡ ወጣቶችን እንዴት ነው የምትመለምሉት?

አቶ ፍቅሬ፡- ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው የወጡ ወጣቶችን ነው የምንወስደው፡፡ የዩኒቨርሲቲ ምሩቆች ነገር ግን ወደ ሥራው ዓለም ያልገቡ ናቸው፡፡ ካለን ውስን አቅም አንፃር በየዓመቱ የምንቀበለው 122 እስከ 130 ወጣቶችን ነው፡፡ ለአንድ ወር ያህል ተከታታይ የአሠልጣኞች ሥልጠና እንሰጣለን፡፡ ከዚያም ለአንድ ዓመት ያህል ከእኛ ጋር እንዲሠሩ እናደርጋለን፡፡ ከእኛ ጋር በሚቆዩበት የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥም ከሥር ከሥር በአመራርና በአይሲቲ ላይ ያላቸውን ዕውቀት እንገነባለን፡፡ የአንድ ዓመት ጊዜያቸውን በሚያጠናቀቁበት ወቅት በተለያዩ ሥራዎች ለመሠማራት ብቁ ይሆናሉ፡፡ ከእኛ ጋር ተመርቀው በመውጣት ገበያውን ይቀላቀላሉ፡፡ ተፈላጊው ክህሎት ስላላቸውም በቀላሉ ሥኬታማ ይሆናሉ፡፡ አንዳንዶቹ ኢንተርኖቻችን ገና ሳይመረቁ በተለያዩ ተቋማት ይቀጠራሉም፡፡ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን እንዲማሩ የሚነሳሱበትና የድኅረ ምረቃ ትምህርታቸውን የሚቀጥሉም አሉ፡፡

ሪፖርተር፡- ከአዲስ አበባ ውጭ በተለያዩ የክልል ከተሞች ትሠራላችሁ? የምትሠሩ ከሆነ አካባቢዎቹን የምትመርጡበት መሥፈርቶች ምን ምን ናቸው?

አቶ ፍቅሬ፡- ምንሠራው የወጣት ሥራ አጦች፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት በሚበዙባቸው በአዲስ አበባ፣ በመቀሌ፣ በባህር ዳር፣ በአዋሳና በአርባምንጭ ከተሞች ነው፡፡ ድርጅቱ በኢትዮጵያ ከተቋቋመና መሥራት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከ25,000 የሚበልጡ ወጣት ሴቶችና ወንዶችን መድረስ ችለናል፡፡ሥልጠናውን ለማዳረስ የምንሞክርበት ሁኔታ ፒር ቲቺንግ (የአቻ ለአቻ ሥልጠና) በመሆኑ ግን ውጤታማ ነው፡፡ ከአንድ አካባቢ ወስደን የምናሰለጥነው አንድ ኢንተርንም በአካባቢው ላይ ትልቅ ተፅዕኖ የሚፈጥርበት ዕድል መኖሩም የተሻለ ውጤታማ ያደርገናል፡፡

ሪፖርተር፡- በሥራ ፈጠራ ዙሪያ ያሉ ችግሮች ምንድን ናቸው?

አቶ ፍቅሬ፡- በጣም ብዙ ችግሮች አሉ፡፡ ዋናው ሥራ የሚሠራበት ቦታ አለማግኘት ነው፡፡ ጥሩ የቢዝነስ ሐሳብ ኖሯቸው ወደ ተግባር ለመለወጥ መሥሪያ ቦታ በማጣት ብዙ የሚቸገሩ አሉ፡፡ ቦታ ቢያገኙም በአገሪቱ ባለው አመቺ ያልሆነ የአከራይ ተከራይ ግንኙነት ለመሥራት የሚቸገሩ ብዙ ናቸው፡፡ የኪራይ ዋጋ እስከ 40 በመቶ በአንዴ የሚጨምሩ አሉ፡፡ ይኼ የገበያ ሁኔታውን ለመገመት አዳጋች ከማድረጉ ባለፈ የትርፍ ህዳጋቸው በጣም እንዲቀንስ ያደርገዋል፡፡ ቢሮክራሲም ሌላው ችግር ነው፡፡ አንድ ጉዳይ ለማስፈጸም ከምዝገባ ጀምሮ ብዙ ውጣ ውረዶች አሉ፡፡ የሚጠየቁ ሰነዶችም ብዙ ናቸው ገደብ የላቸውም፡፡ አንድ ሰው አንድ የቢዝነስ ሐሳብ ይዞ ሲነሳ ሐሳቡን እስካልተገበረው ድረስ ምን ያህል ውጤታማ እንደሚሆን ለማወቅ አይችልም፡፡ ለዚህም አንድ ዓመት ወይም ስድስት ወር የመሞከሪያ ጊዜ ያስፈልገዋል፡፡ ነገር ግን ያለው አሠራር ዕድል አይሰጥም፡፡ ገና ከመጀመርያው ሕንፃ ይኑርህ፣ ቤት ይኑርህ፣ ይህን ክፍል የሚባል ነገር አለ፡፡ እነዚህ በጣም ተስፋ የሚያስቆርጡ ናቸው፡፡ ፋይናንስም ሌላው መሠረታዊ ችግር ነው፡፡ የኛ ዒላማ ወጣቱ ነው፡፡ ወጣቱ ደግሞ ገንዘብ ሲበደር የሚያስይዘው ኮላትራል (ማስያዣ ንብረት) የለውም፡፡ ለዚህም መነሻ ገንዘብ በማጣት ስራውን ከጅምሩ ይተዉታል፡፡ እንዲህ ያሉ ችግሮችን ይፈታሉ ተብለው የተቋቋሙ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት እንኳን ያለ ኮላተራል ብድር አይሰጡም፡፡ እንዲያውም ባንኮች ከሚጠይቁት ማስያዣ የበለጠ የሚጠይቁበት አጋጣሚ አለ፡፡ ወጣቶች የሚያመጡትን አዲስ የቢዝነስ ሐሳብ ወደ ተግባር ለመለወጥ ድጋፍ የማድረግ ነገርም ዝቅተኛ ነው፡፡ ለዚህም በማኅበረሰቡ ሌላ ትልቅ ለውጥ መፍጠር የሚችለውን ሐሳብ ወደ ጎን ብሎ ተቀጣሪ ሆኖ የመሥራት ነገር አለ፡፡ እነዚህ ትልቅ ነገሮች ናቸው፡፡

ሪፖርተር፡- ድርጅቱ የቴክኒክ ድጋፎችን ከማድረግ ባለፈ ወጣቶቹን በገንዘብ የሚደግፍበት አሠራር አለ?

አቶ ፍቅሬ፡- እኛ በመሠረቱ የገንዘብ ድጋፍ አንሰጥም፡፡ ነገር ግን ይህን አገልግሎት ከሚሠጡ ከተለያዩ ተቋማት ጋር አብረን በመሥራት የሚሰጡት የፋይናንስ ድጋፍ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ሥልጠናና ክትትል እናደርጋለን፡፡

ሪፖርተር፡- በአገሪቱ የሚሰጡ የኢንተርፕሩነርሺፕ ሠልጣኞች በወኔ ተሞልተው አንድን ሥራ እንዲጀምሩ የሚያነሳሳ እንጂ በሥራው ላይ ሲያጋጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችም እንዳሉና እንዴት መወጣት እንዳለባቸው ጭምር የሚያሠለጥኑ አይደሉም የሚሉ አሉ። በዚህ ላይ የእርስዎ አስተያየት ምን ይመስላል?

አቶ ፍቅሬ፡- እንዲህ ዓይነት ነገር የሚፈጠረው የሚሰጡ ሥልጠናዎች የፅንሰ ሐሳብ ብቻ ሲሆኑ ነው፡፡ እኛ ግን ዝም ብለን ሌክቸር አንሰጥም፡፡ እኔ ኢንተርፕሩነር መሆን እችላለሁ ወይ ብሎ ራስን እንዲጠይቅ የሚያስችል ሥልጠና እንሰጣለን፡፡ በሥልጠናዎች ላይ ሥኬታማ የሆኑ ሥራ ፈጣሪዎች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ እናደርጋለን፡፡ ይህ ምን ምን ዓይነት ችግሮች መኖራቸውን እንዲገነዘቡ እንዴትስ ማለፍ እንዳለባቸው እንዲያውቁ ያስችላል፡፡

ሪፖርተር፡- ለምን ያህል ጊዜ ነው ሥልጠና የምትሰጡት?

አቶ ፍቅሬ፡- ሥልጠናዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ለመጀመርያ ጊዜ ሠልጣኞች ከሦስት እስከ አራት ሳምንት እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡ ከዚያ በኋላ ለአንድ ወር ያህል ክትትል እናደርግላቸዋለን፡፡ ሌሎቹ ግን ከአንድ እስከ ሁለት ሳምንት የሚሰጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ብቻ በቂ ባለመሆናቸው በሚፈልጉት መጠን ድጋፍ የሚያገኙበት አሠራርም አለን፡፡ እነሱ ፍላጎት ኖሯቸው እስከመጡ ከሶስት ወር እስከ ስድስት ወራት ድረስ አስፈላጊውን አገልግሎት እንሰጣቸዋለን፡፡

ሪፖርተር፡- ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ ምሩቆችን ለስራ ብቁ ለማድረግ የምትሰሩትስ ካለ?

አቶ ፍቅሬ፡- ብዙ ጊዜ ከኮሌጆች፣ ከዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀው የሚወጡ ወጣቶች ለሥራ ብቁ የሚያደርጋቸውን ዕውቀት ጨብጠው አይወጡም፡፡ በተለይም የኮሙኒኬሽን፣ የኔት ዎርኪንግ፣ ደንበኛ አያያዝ የመሳሰሉት ክህሎቶች ላይ ደካማ ናቸው፡፡ ቀጣሪዎቹ የሚፈልጉት ያህል ዕውቀት የላቸውም፡፡ ቀጣሪዎች የሚፈልጉት ሌላ፣ የትምህርት ተቋማት የሚያዘጋጁት የሰው ኃይል ሌላ ነው፡፡ ይኼንን እንደ አንድ ክፍተት ተመልክተን እየሠራንበት ነው፡፡

ሪፖርተር፡- አለ ለሚሉት ችግር ማለትም የትምህርት ተቋማት የሰው ኃይል ከማፍራት አኳያ ያለባቸው ክፍተት እንዴት ተፈጠረ? ቀጣሪዎችስ ሠራኞች ምን ዓይነት ክህሎት እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ?

አቶ ፍቅሬ፡- የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የተለያየ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ይፈልጋሉ፡፡ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ጨርቃጨርቅ ላይ ቴክኒካል ክህሎት ያለው ሰው ይፈልጋል፡፡ ሌሎችም እንደዚሁ፡፡ ሁሉም ኢንዱስትሪዎች ደግሞ ከሠራተኞች የሚፈልጉት አንድ ዓይነት መስፈርት አለ፡፡ ከእነዚህም መካከል አንዱ የኮሙኒኬሽን ክህሎት ነው፡፡ ሠራተኛው እንዴት ነው ደንበኞችን የሚያስተናግደው? እንዴት ነው ራሱን የሚገልጸው? የሚለው ጉዳይ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ በተለይም ደግሞ ለወጣቶች የሕይወት ክህሎት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የተለያዩ ችግሮች ሲገጥማቸው እንዴት መወጣት ይችላሉ? እነዚህ እነዚህ ሁሉ አብረው የሚሄዱ ዕውቀቶች ናቸው፡፡ እኛም በዚህ ረገድ የሚኖረውን ክፍተት ለወጣቶች ሥልጠና በመስጠት ለመሙላት እንጥራለን፡፡ ከዚህም ሌላ ቴክኒካል የሆኑ የኢንተርፕሩነር ሥልጠናዎችን እንሰጣለን፡፡ የትምህርት ሥርዓቱ ላይ ችግር አለ፡፡ በሁሉም ቦታዎች ላይ ያለው የትምህርት ጥራቱ ደካማ እንደሆነ ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡ እያደገ ከሚሄደው የኢንዱስትሪዎች ፍላጎት ጋር የተጣጣመ የትምህርት አሰጣጥም የለም፡፡ ተማሪዎች የሚማሩበት መንገድም የተግባር ትምህርትን ያላካተተ የፅንሰ ሐሳብ ትምህርት ብቻ መሆኑም ትልቅ ችግር ነው፡፡ የፅንሰ ሐሳብ ትምህርቶች ከተግባር ጋር አያይዘው ስለማይማሩ ወደ ሥራው ዓለም በሚገቡበት ወቅት በትምህርት ያገኙትን ዕውቀት ወደ ተግባር ለመለወጥ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል፡፡

ሪፖርተር፡- የትምህርት ጥራቱ ጉዳይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዴት ነው?

አቶ ፍቅሬ፡- እኛ ካጤንነው ጊዜ ጀምሮ የትምህርት ጥራቱ እየደከመ እየደከመ ነው የመጣው፡፡ በተለይም ደግሞ ብዛት ላይ ትኩረት ተደርጎ መሠራት ከተጀመረ በኋላ የትምህርት ጥራቱ በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል፡፡ ብዛት ላይ ማተኮሩ የመምህራን ቁጥርና የተማሪዎች ቁጥር እንዳይጣጣምም አድርጓል፡፡

ሪፖርተር፡- በአገሪቱ ያለውን የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

አቶ ፍቅሬ፡- የተለያዩ ስትራቴጂዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ዋናው የትምህርት ሥርዓቱን ከጥራት፣ ከይዘትና ከተደራሽነት አኳያ መለወጥ ያስፈልጋል፡፡ አሁን በብዛት እየተሠራ ያለው ተደራሽነት ላይ ነው፡፡ ተደራሽነትን ደግሞ ከሌሎች ነገሮች ጋር ሚዛናዊ አድርጎ ማስኬድ ካልተቻለ አደገኛ ነው፡፡ የዚህ ጥቅሙና ጉዳቱ የሚታየው ከዓመታት በኋላ ነው፡፡ ከዓመታት በኋላ አደገኛ ነገር ከማየት አሁኑኑ ነገሮችን በጥሞና አስቦ መሥራት ግድ ነው፡፡ መምህር ሳይኖር 30 ዩኒቨርሲቲ ቢከፈት ምንድነው ጥቅሙ? በአሁኑ ወቅት በደንብ ያልሠለጠኑ መምህራን እንዲያስተምሩ ሲደረግም ይታያል፡፡ ያለው የተጠያቂነት ሥሜትም በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ክፍል ገብቶ ሳያስተምር ሁለትና ሦስት ወር ሌላ ቦታ ቆይቶ ቅዳሜና እሑድ ገብቶ የአንድ ሴሚስተር ኮርስ ጨርሶ መሄድም ተለምዷል፡፡

ሪፖርተር፡- ለመፍጠር ያሰባችሁትን ያህል ለውጥ መፍጠር ችለናል ይላሉ?

አቶ ፍቅሬ፡- እኛ የምንፈልገው ፈጣንና በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ከራሳቸው አልፎ ለሌሎች ሥራ መፍጠር የሚችሉ ወጣቶችን ማፍራት ነው፡፡ ይኼንን ማሳካት የአንድ ድርጅት ሥራ ብቻ ሊሆን አይችልም፡፡

የትግራይ ክልል በርከት ...

ከገጽ 7 የዞረ

ሙሉጌታ ሀዱሽ (የቴክኒክና ሙያ ቢሮ ኃላፊ) ናቸው::

በተጨማሪም ዶ/ር ፋና ሐጎስና አቶ አማኑኤል አሰፋ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆን ተሹመዋል:: እንዲሁም ዶ/ር ረዳኢ በርኼ ደግሞ የክልሉ የዋና ኦዲተር ኮሚሽነር ሆነው ተሹመዋል::

የቢሮ ለውጥ ያደረጉ አመራሮችን በተመለከተ አቶ ገብረ መስቀል ታረቀ የፀጥታና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ ጎይቶም ይብራህ የወጣቶች ጉዳይና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ በመሆን ሲሾሙ፣ ዶ/ር ገብረ ሕይወት ገብረ እግዚአብሔር ደግሞ የደቡባዊ ምሥራቅ ዞን አስተዳዳሪ ሆነዋል::

በጥቅምት ወር 2009 ዓ.ም. የሕወሓት ከፍተኛ አመራሮች ቀደም ብሎ በድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ባደረገው ጉባዔ ላይ ያሳለፉቸውን ውሳኔዎች መሠረት በማድረግ ለስምንት ቀናት ስብሰባ አካሂደው ነበር:: በወቅቱ የ15 ዓመታት ግምገማ በማካሄድ የፓርቲውን የወደፊት አቅጣጫ በተመለከተ ባለ አሥር ነጥብ የአቋም መግለጫ አውጥቶ ነበር::

በመግለጫውም፣ ‹‹የያዝነው ሥልጣን በዋናነት ለሕዝብ አገልግሎት አላዋልነውም፤›› የሚለው ይገኝበታል:: ‹‹ወጣቶች በነፃነት እንዳይንቀሳቀሱና በራሳቸው አመለካከት እንዳይራመዱ መደረጋቸውንና ለዚህም ሁሉ መነሻው ፀረ ዲሞክራሲያዊ የሆነ አካሄድ በመስፈኑ ነው፤›› ተብሎ ነበር:: ‹‹በእነዚህና መሰል ምክንያቶች በድርጅቱና በሕዝቡ መካከል ለዘመናት የቆየው አንድነትና መተማመን በተለያዩ ደረጃዎች ተሸርሽሯል፤›› ሲልም ጉባዔው በመግለጫው ገልጿል::

በተመሳሳይ ቀደም ብሎ የኦሮሚያና የአማራ ክልል መንግሥታት ካቢኔ ማዋቀራቸው ይታወሳል::

የክልሎቹ አዲሱ የካቢኔ መዋቅር በፌደራል መንግሥት ደረጃ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ካደረጉት አዲስ የካቢኔ ሹምሽርና ሽግሽግ ጋር መመሳሰል ይታይበታል::

ነገር ግን በክልል ደረጃ ከኦሮሚያ ክልል በስተቀር የዋና አመራሮች ለውጥ አለመደረጉ ይታወቃል:: የኦሮሚያ መንግሥት ዋናና ምክትል ርዕሰ መስተዳደሮችን በአዲስ ሲለውጥ፣ ቀደም ብሎም የክልሉን መንግሥት የሚያስተዳድረው ኦሕዴድም ሊቀመንበሩንና ምክትል ሊቀመንበሩን እንዲሁ መለወጡ አይዘነጋም::

የስምጥ ሸለቆዋ ከተማ

በታደሰ ገብረማርያም

ከአዲስ አበባ 97 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች:: አመሠራረቷም ከኢትዮ ጂቡቲ የባቡር መስመር ጋር የተያያዘ ነው:: ከተማዋ 100ኛ ዓመቷን አክብራለች:: በቀደምትነት ኦሮሞዎች የመሠረቷት ሲሆን በኋላ ላይ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ ሆናለች:: ይህም የሥራ፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የመቻቻልና የዕድገት ከተማ አስብሏታል::

የከተማዋም መሠረተ ልማት በመንገድ፣ በንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ በኤሌክትሪክ ኃይልና በትምህርት ቤቶች አሸፋፈን ሲታይ ከሞላ ጎደል መልካም ነው:: በተለይም በትምህርት ዘርፍ ከአፀደ ሕፃናት (ቅድመ መደበኛ ትምህርት) ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ እንዲሁም በጤና ዘርፍ የግሉን ዘርፍ ጨምሮ ከጤና ጣቢያ እስከ ሪፈራል ሆስፒታል አላት::

በኢንዱስትሪውም፣ የውጭ ባለሀብቶችንም ያሳተፉ ኢንዱስትሪዎች ባለቤት ናት:: ከጥቃቅንና አነስተኛ ተነስተው ትልቅ ደረጃ የደረሱ ማፍራት የተቻለባት ከተማ ስትሆን፣ በተለይ ለአዲስ አበባ ቅርብና የኢትዮ ጂቡቲ የባቡር መሥመር መተላለፊያ መሆኗ፣ አንድ የንግድ ማዕከል ሆና እንድታገለግል አድርጓታል::

ለኦሮሚያ ክልልም ሆነ በአጠቃላይ ለአገሪቱ በከፍተኛ ደረጃ የኮንፍረንስ ማዕከል ሆና እያገለገለችም ትገኛለች:: ይሁን እንጂ ገልማ አባገዳ አዳራሽን ጨምሮ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች፣ የሶደሬ ሪዞርት፣ ባኮ የእንፋሎት ጠበል የመሳሰሉ መስህብ ቢኖራትም፣ በቱሪዝም ዘርፍ ብዙ ተሠርቷል ለማለት አያስደፍርም:: የሚጎበኙ ቦታዎችን ከማዘጋጀትና ከአደረጃጀት አኳያ መከናወን የሚገባቸው ሰፊ ሥራዎችም አልተነኩም::

በታላቁ የስምጥ ሸለቆ ውስጥ የምትገኘው ይህች ከተማ ሞቃታማ የአየር ፀባይ ቢኖራትም፣ ለነዋሪዎቿ ምቹና ውብ፣ ዋል አደር ብሎ ለሚመለስ ወይም በአጠቃላይ ለጎብኚዎቿ ጥሩና ተስማሚ ናት:: ብዙ የተዘመረለትና እየዘመነች ያለችው ይህች ከተማ አዳማ ትባላለች:: በነዋሪዎቿም ዘንድ የስምጥ ሸለቆዋ እንቁ ከተማ የሚል ቅጽል ሥም አትርፋለች::

ሰማዕታት ሐውልት

የተቆረቆረችበት ስፍራ፣ ‹‹አሮጌ አዳማ›› ወይም ‹‹መልካ አዳማ ቀበሌ›› ይባላል:: ቦታው ከ100 ዓመት በፊት የኢትዮ ጂቡቲ አሮጌው የባቡር ሐዲድ የተዘረጋበትና ዙሪያውም በአፋን ኦሮሞ ‹‹አዳሜ›› በአማርኛ ደግሞ ‹‹ቁልቋል›› የሚባል ተክል የበዛበት ነበር:: ከተማዋም ስያሜዋን ያገኘችው ከዚሁ ቁልቋል ወይም አዳሜ እንደሆነ በጥናት ተረጋግጧል::

በአሮጌዋ አዳማ ውስጥ በርካታ አባወራዎች ይገኛሉ:: ሁሉም የሚተዳደሩት በግብርና ነው:: ምንም እንኳን አንድ ምዕተ ዓመት የሞላት ብትሆንም፣ እስካሁን ድረስ ክሊኒክን ጨምሮ የውሃና የኤሌክትሪክ አገልግሎት የላትም:: ውሃ ለማግኘት ቢያንስ እስከ ስድስት ኪሎ ሜትር ድረስ በእግር መጓዝ ግድ ይላል:: ከነዋሪዎቿ መካከል ጥቂቶቹ የሶላር ብዙዎቹ ደግሞ የኩራዝ ተጠቃሚዎች ናቸው::

የአዳማ ከተማ ከተቆረቆረችበት ከፍታ ቦታ ላይ አሁን ወደምትገኝበት ዝቅተኛ ቦታ ላይ እንዴት ልትስፋፋ ቻለች የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው:: አቶ አለማየሁ ቱሉ የአዳማ ከተማ 100ኛ ዓመት አከባበር ጽህፈት ቤት አስተባባሪ ይህንኑ አስመልክተው እንደገለጹት፣ የዛሬ 100 ዓመት ከፍታ ቦታ ላይ ከሚገኘው አሮጌው አዳማ ውስጥ በተዘረጋው ሃዲድ በመጓዝ ላይ የነበረ የባቡር ፉርጎ ተበጥሶ ቁልቁለቱን ይወርድና ለገሃር ይቆማል:: ከዚህ በኋላ ለምን ከተማዋን በዚሁ ዝቅተኛ ሥፍራ ላይ አናደርጋትም ተብሎ አሁን በምትገኝበት ቦታ ልትስፋፋ ቻለች::

በአሮጌዋ አዳማ ወይም በመልካ አዳማ ቀበሌ ነባሩ ሃዲድ ከተዘረጋ ጊዜ ጀምሮ የነበሩ ቤቶች አሁንም እንዳሉ ሲሆን፣ ይህም የቱሪስት መስህብ ሆኖ ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግም እየተሠራ መሆኑን አቶ አለማየሁ ይናገራሉ::

የከተማዋን 100ኛ ዓመት አስመልክቶ ካለፈው ዓመት ሚያዝያ እስከ ዘንድሮው ዓመት የመጀመርያ ወር ድረስ ከተካሄዱት ልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች እስከ አምስት ሚሊዮን ብር መገኘቱን አቶ አለማየሁ ገልጸዋል::

ከዚህም ሌላ በአንድ ጊዜ 80 ሺህ ሰዎችን የማስተናገድ አቅም ያለው ዘመናዊ ስታዲየም ለመገንባትና የከተማ መናፈሻ (ሲቲ ፓርክ) ለማቋቋም ታቅዷል:: ለዕቅዱም እውን መሆን የስታድየሙና የመናፈሻ ዲዛይኖች ተሰርቷል:: ለስታድየሙ ግንባታ የሚውል 33 ሄክታር መሬትም ተዘጋጅቷል::

ማስታወቂያ

ፍሮምሲስ የትምህርት እና ስልጠና አ.ማ 7ኛ መደበኛ እና 3ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ

የአክሲዮን ማህበሩን ወቅታዊ እና ቀጣይ ሁኔታዎች ለመምከርና ስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን በማመላከት ተገቢ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ እንዲቻል የአክሲዮን ማህበሩን አባላት መደበኛ እና የ3ተኛ ድንገተኛ ጉባዔ ለማድረግ የኩባንያዉ ባለአክሲዮኖች በአካል ወይም በህጋዊ ወኪሎቻቸዉ አማካኝነት ታህሳስ 16 ቀን 2009 ዓ.ም ከጧቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ በቀበና አካዳሚ (ሳንፎርድ ት/ቤት ፊት ለፊት) በሚካሄደዉ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ኩባንያዉ ጥሪዉን ያቀርባል::

የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

1. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ ማፅደቅ፣
2. የዳይሬክተሮች ቦርድን ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ፣
3. የቁጥጥር ኮሚቴን ሪፖርት ማዳመጥ፣
4. የ2008 ዓ.ም ኦዲት ሪፖርት ማድመጥ፣
5. የተጓደሉ የቦርድ አባላት መምረጥ
6. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረተት አባላት 2/3ኛ ድምፅ በማግኘት የሚቀርቡ አጀንዳዎች ላይ መወያየት፣
7. የዕለቱን ዉሳኔዎች ማፅደቅ::

የ3ኛ ድንገተኛ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. የዕለቱን የ3ኛ ድንገተኛ ስብሰባ አጀንዳ ማፅደቅ፣
2. የማህበሩን ካፒታል ማሳደግ፣
3. መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል፣
4. የ3ኛ ድንገተኛ ጉባዔ ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ::

ETHIOPIAN AGRICULTURAL COMMODITIES WAREHOUSING SERVICE ENTERPRISE

Invitation to Bid (ITB)

ITB.NO. LAB.EQUIPMENT. *EACWSE NCB /O-10 /2016 for Procurement of*Labartaory Equipmenand Others

Ethiopian Agricultural Commodities Warehousing Service Enterprise (EACWSE) is established through the Council of Ministers regulation No. 331/2014 to handle mainly warehousing and quality services of agricultural commodities.Therefore, EACWSE would like to invite National Competitive Bidding (NCB) for capable and reliable suppliers for the following

No.	Descriptions	UOM	QTY
1	Round hole sieves with pan (from 1/64"____20/64"	Pcs	2
2	Moisture tester	Pcs	10
3	Compact scale 300g +- 0.01gm	Pcs	10
4	Coffee Grinding machine	Pcs	5
5	Roasting machine	Pcs	5

1. A bid security shall be made 2% of bid amount in Ethiopia Birr in the form of CPO or unconditional guarantee letter or any payable order, all from a reputable financial institution.
2. Interested bidders can purchase tender document upon a payment of non-refundable Birr 150.00 (one hundred fifty) and can inspect the bidding document at the address below.
3. All bids must be deposited in the tender box at Ethiopia Agricultural Commodities Warehousing ServiceEnterprise (EACWSE) Head office (CheleleqAlsam Tower 1st floor) on/before bid closing time**on January 28, 2016at 11: am** and the opening of the bids will be conducted **onJanuary 28, 2016, at 11:30 am**, in the presence of bidders or their representative atCheleleq AL-Sam Tower 2, 1stfloor.
4. The Enterprise reserves the right to accept or reject any or all bids at any time.
5. For further information, please use the following contact address during working hours.

Ethiopia Agricultural Commodity Warehouse Enterprise (EACWASE) Contact Person: +251-115530991Alsam Tower, Addis Ababa, Ethiopia

ኢትዮጵያ የተዘረፉባት ታሪካዊ ቅርሶቿ እንዲመለሱላት ጠየቀች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት በባዕዳን ወራሪዎች ተዘርፈው የተወሰዱባት ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች እንዲመለሱላት ግፊት እንዲደረግ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ጠየቁ፡፡

ባለፈው ቅዳሜ ኅዳር 24 ቀን 2009 ዓ.ም. በዩናይትድ ዐረብ ኢምሬትስ መዲና አቡዳቢ በተካሄደውና ከአርባ አገሮች በላይ ፕሬዚዳንቶች፣ ርዕሳነ ብሔራትና እንደራሴዎች በተገኙበት በአደጋ ላይ ባሉ ባህላዊ ቅርሶች ኢንተርናሽናል ጉባኤ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም፣ የኢትዮጵያ ቅርሶች እንዲመለሱ የዓለሙ ማኅበረሰብ ግፊት እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ለሁለት ቀናት በኢሜሬትስ ቤተመንግሥት በተካሄደው ጉባኤ ከሺሕ ዓመታት በላይ ያስቆጠሩ የጥንት ሥልጣኔ አመልካቾች ባህላዊ ቅርሶች፣ በጦርነትና በዘረፋ ውድመት እየደረሰባቸው መሆኑን ተመልክቷል፡፡ በተለይ ዳኢሽ (አይኤስ) በሶርያና በኢራቅ፣ ቦኮ ሃራም በማሊ፣ ታሊባን በአፍጋኒስታን ያደረሷቸው ጥፋቶች ተወስተዋል፡፡ ኢዜአ እንደዘገበው፣ በአቡዳቢ ዓለም አቀፍ የታሪካዊ ቅርስ ጉባኤ የተካፈሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም እንዳሉት የተዘረፉ ቅርሶችን የማስመለስ ሒደቱ የዘገየ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የበርካታ ታሪካዊ ቅርሶች ባለቤት እንደመሆኗ መጠን በውጭ ወረራ ዘመን አሁን ደግሞ በሕገ ወጥ የቅርስ አዘዋዋሪዎች ምክንያት የዘረፋው ሰለባ ሆናለች ብለዋል፡፡

በዚህም የበዙና ውድ የሆኑ ጥንታዊ ድርሳናትና ሃይማኖታዊ ቅርሶች እንዲሁም በቁፋሮ የተገኙ ቅሪቶች አገሪቷ ማጣቷን ገልጸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያምን ጨምሮ የተለያዩ አገር መሪዎች በአቡዳቢው የባህላዊ ቅርስ ጉባኤ ተገኝተዋል

በሕገ ወጥ መንገድ ከአገሪቱ ከተወሰዱት ጥንታዊ ድርሳናት መካከል ሃይማኖታዊ መጻሕፍት፣ የመድኃኒት፣ የሥነ ክዋክብት፣ የቀን መቁጠሪያ፣ የፍልስፍና፣ የሕግና የአስተዳደር መጻሕፍት በማሳያነት አንስተዋል፡፡

በዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ዘመን በ1860 ዓ.ም. እንግሊዛውያን ተጓዦችና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ከ1928 - 1933 በነበረው የጣሊያን ወረራ ደግሞ የኢትዮጵያ ቅርሶች በብዛት የተዘረፉባቸው ዘመናት ናቸው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ከ3,500 በላይ ታሪካዊ ድርሳናት በአውሮፓ አገሮችና በአሜሪካ እንደሚገኙ ይታመናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቅርስ ዘረፋና ሕገ ወጥ ዝውውር እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ አገሮች ችግር መሆኑንም ሳይጠቅሱ አላለፉም፡፡

ከዚህ በላይ የከፋ አደጋ የሚሆነው ግን ባህልን የማጥፋት አካል የሆነው ቅርሶችን ሆን ተብሎ የማውደም የአሸባሪዎች ተግባር እንደሆነ የዓለምን ባህል ለማጥፋት ሆን ተብሎ የሚፈጸመው ድርጊትም ኢትዮጵያን እንደሚያሳስባት ጭምር ተናግረዋል፡፡

የሁለት ቀናት ጉባኤው ሲጠናቀቅም ዩኔስኮ (የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት) በወታደራዊ ግጭቶች ወቅት ቅርሶችን ከጥቃት እንዲከላከል የሚደግፍ የአቡዳቢ ውሳኔ መተላለፉ ታውቋል፡፡

ፍሬ ከናፍር

‹‹ቀነኒሳ በቀለ በሪዮ ኦሊምፒክ በማራቶን አለመወዳደሩ ታላቅ ስህተት ነው!››

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ የዓለም ኮከብ አትሌቶች ምርጫ በተካሄደባት ሞናኮ ከተማ ለኤኤፍፒ የዜና ምንጭ የተናገረው፡፡ ጫማውን የሰቀለው ገናናው ሯጭ ኃይሌ ኅዳር 22 ቀን 2009 ዓ.ም. በሰጠው መግለጫ በቅርቡ በተካሄደው የበርሊን ማራቶን የዓለም ክብረ ወሰንን ለመስበር ስድስት ሰከንድ አምልጦት ያሸነፈው ቀነኒሳ በቀለ፣ ዘንድሮ ክብረ ወሰኑን እንደሚሰብር እምነቱ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ የኦሊምፒክ 5,000 ሜትርና 10,000 ሜትር ሻምፒዮኑ ቀነኒሳ በቀለ በዘንድሮ የበርሊን ማራቶን ያስመዘገበው 2 ሰዓት 03 ደቂቃ 03 ሰከንድ ሃቻምና ዴኒስ ከሚቶ በጀርመን መዲና ካስመዘገበው 2፡02፡57 የተቃረበ ነበር፡፡ ‹‹ምንም ይሁን ምንም ለንደን (የዓለም ሻምፒዮና የሚካሄድባት) እየመጣች ነው›› ያለው ኃይሌ፣ ‹‹ታያላችሁ ወይ ዱባይ አሊያም በሌሎች ማራቶኖች ዕድል ከቀነኒሳ ጋር እንደምትቆም›› በማለትም ተናግሯል፡፡

ናሽናል ኮሌጅ

ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

ናሽናል ኮሌጅ ከታች በተዘረዘሩት የሥራ መደቦች ሰራተኞችን በቋሚነት አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል

ተ.ቁ	የሥራ መደቡ መጠሪያ	ተፈላጊ የትምህር ደረጃ	ብዛት	የሥራ ልምድ
1	ቴክኒክና ሙያ (TVET) አስተባባሪ (ኮኦርድኔተር)	በመጀመሪያ ዲግሪ በአካውንቲንግ ወይም በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ	1	1 አመት የሥራ ልምድ
2	በማኔጅመንት እና ተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ	የመጀመሪያ ዲግሪ	1	ዜሮ አመት

ማሳሰቢያ

- የሥራ ቦታው ሜክሲኮ/ላንቻ ካምፓስ
- ጾታ አይለይም
- ደሞዝ በስምምነት
- ለተመረጡ ተወዳዳሪዎች የፈተና ጊዜ ማስታወቂያ በስልክ ይገለፃል
- መስፈርቱን የምታሟሉ አመልካቾች ይህ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 7 ተከታታይ የስራ ቀናት ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ከማመልከቻ ጋር በመያዝ ሜክሲኮ ዋናው ካምፓስ አስተዳደር ቢሮ ማመልከት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

ለተጨማሪ መረጃ 0911405622 ወይም0115572130 መደወል ትችላላችሁ

ሲቲ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አ.ማህበር

የስብሰባ ጥሪ

የሲቲ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አክሲዮን ማህበር የባለክሲዮኖች አስራ ስድስተኛ /16ኛ/ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከዚህ በታች በተመለከቱት አጀንዳዎች መሠረት አርብ ታህሳስ 7 ቀን 2009 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ ሺ-ሰማኒያ በሚገኘው በማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ስለሚካሄድ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች በሙሉ በተባለው ቀንና ቦታ ተገኝተው በጉባዔው ላይ እንዲሳተፉ የዲሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

በስብሰባው ላይ ለመገኘት የማይችል ባለአክሲዮን ከጉባዔው እለት ቢያንስ 3 ቀናት አስቀድሞ በማህበሩ ጽ/ቤት በመገኘት የውክልና ቅጽ በመሙላት ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን በስብሰባው ዕለት ራሱ መገኘት የማይችል ባለአክሲዮን ህጋዊ የውክልና ሰነድ የያዘ ወኪል በሰዓቱ /በስብሰባው ዕለት/ መላክ የሚችል መሆኑን እንገፃለን፡፡

የ16ኛው መደበኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ፡-

1.1 ረቂቅ አጀንዳውን ማፅደቅ፤
1.2 የዲሬክተሮች ቦርድ ሪፖርትን መስማት፤
1.3 የኦዲተሮችን ሪፖርት መስማት፤
1.4 በሁለቱ ሪፖቶች ላይ ውይይት እና ውሳኔ ማድረግና፤
1.5 ኦዱተሮችን መሾምና የስራ ዋጋቸውን መወሰን፤

የዲሬክተሮች ቦርድ
ሲቲ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አ.ማህበር

አድራሻ፡- ንግስት ኤልዛቤት መንገድ፤ከአራት ኪሎ ወደ መገናኛ በሚወስደው መንገድ ራስ አምባ ሆቴል አጠገብ ፤

ስልክ ቁጥር፡- +251111-233212 / +251910-447063

ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.
BUNNA INTERNATIONAL BANK S.C.

BUNNA INTERNATIONAL BANK SHARE COMPANY
BALANCE SHEET
AS AT 30 JUNE 2016

	Notes	Birr	2015
Assets			
Cash and bank deposits	3	1,252,902,247	819,487,008
Other assets	4	204,500,476	137,327,489
Loans and advances (net)	2 d),6	3,631,844,755	2,417,941,350
Investment in shares	2 e),5.1	31,370,000	16,370,000
Investment in debt securities	2 e),5.2	1,587,511,000	1,020,562,000
Property and equipment (net)	2 f),7	112,830,990	88,007,940
Total assets		**6,820,959,469**	**4,499,695,787**
Liabilities			
Customers' deposits	8	5,384,603,762	3,501,041,459
Margin held in letter of credit and CAD		149,900,663	102,131,070
Other liabilities	9	262,515,426	171,415,767
Provision for profit tax	11	63,391,996	47,388,646
Total liabilities		5,860,411,847	3,821,976,942
Equity			
Share capital	10	686,422,293	508,373,455
Share premium		6,873,848	3,198,648
Legal reserve	12	127,560,367	80,798,641
Special reserve	13	605,935	605,935
Retained earnings		139,085,178	84,742,166
Total equity		960,547,622	677,718,845
Total liabilities and equity		**6,820,959,469**	**4,499,695,787**

Eng. Tibebu Eshete
Chairman of the Board of Directors

Eshetu Fantaye
CEO/President

BUNNA INTERNATIONAL BANK SHARE COMPANY
INCOME STATEMENT
FOR THE YEAR ENDED 30 JUNE 2016

	Notes	Birr	2015
Income			
Interest Income	14	491,082,086	308,278,238
Commission Income	17	112,335,170	71,950,127
Service Charges	16	67,557,149	52,776,106
Gain (Loss) on Foreign Currency		48,636,875	38,299,153
Other Income	18	15,268,751	10,788,660
		734,880,031	**482,092,284**
Expenses			
General Expenses	20	144,384,177	111,677,281
Interest Expense	15	174,240,574	89,922,564
Salaries & Benefits	19	130,035,979	86,534,625
Provision for Loans & Advances	2(d)	35,365,150	11,640,150
Audit Fee		119,250	138,000
Directors Allowance	21	296,000	288,000
Total Expenses		**484,441,129**	**300,200,620**
Profit before Tax		**250,438,902**	**181,891,664**
Provision for Profit Tax	11	63,391,996	47,388,646
Profit after Tax		187,046,906	134,503,018
Transfer to Legal Reserve		(46,761,726)	(33,625,755)
Net Profit after Tax & Legal Reserve		**140,285,179**	**100,877,264**
Allocation for promoters & founders	22	-	(15,535,099)
Directors' remuneration	21	(1,200,000)	(600,000)
Retained Earning for the Year		**139,085,178**	**84,742,165**
Earning per share of Birr 1,000	23	343.23	286.63

Felema Construction P.L.C.
ፈለማ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ.ማ.

Re vacancy Announcement

Closing Date: Wednesday, ***14 Dec, 2016 (Tahisas 5, 2009 E.C)***

Felema Construction P.L.C. is one of the class 1 contractors that seeks energetic professional to fill the following position based at Addis Ababa.

S/N	Position	Qty	Qualification	Experience	Duty station
1	***Site Engineer***	***2***	BSc Degree in Civil Engineering or Construction Technology & Management or Advanced Diploma.	a minimum of 3/7 year's total experience out of which 4 yr in similar position	Addis Ababa 40/60 Saving House Project Site (Ayat)
2	***Office Engineer***	1	BSc Degree in Civil Engineering or Construction Technology & Management or Advanced Diploma.	a minimum of 3/6 years experience in similar position.	Addis Ababa 40/60 Saving House Project Site (Ayat)
3	***General Forman***	3	TVET/College Diploma in Building Technology.	a minimum of 8 year proven work experience.	Addis Ababa 40/60 Saving House Project Site (Ayat)

Salary and Benefit Packages: Negotiable but attractive
Interested applicants can send their CV, application letter and non-returnable copies of their documents ***deliver in person*** to the company's head office, which is located on the Jackros – Sahlite Mehret Road, behind St. Joseph Catholic Church or bordering the Mission School before Wednesday, 14 Dec, 2016 (Tahisas 5, 2009 E.C)

Contact Address: Phone No..: 0116-67-72-30, 0118-68-61-40

ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከዚህ በታች በተመለከተው የስራ መደብ ላይ መመዘኛውን የሚያሟላ አመልካች አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል

ተ.ቁ	የስራ መደብ መጠሪያ	የመደብ መታወቂያ ቁጥር	የስራ ደረጃ	መነሻ ደመወዝ	ብዛት	ተፈላጊችሎታ
1	የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር	17/አአ-357	ፕሳ-9	5781.00	1	በሂውማን ሪሶርስ ማኔጅመንት፣ በማኔጅመነት፣በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን እና በፐብሊክ አድሚኒስሬሽን የመጀመሪያ ዲግሪ እና 10 አመት፣ የማስተርስ ዲግሪ እና 8 አመት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ

የቅጥር ሁኔታ፡- በቋሚነት
ሴት አመልካቾች ይበረታታሉ
በተፈላጊው ችሎታ ከተገለጸው የትምህርትና የስራ ልምድ በላይ ማስረጃ ያላቸው አመልካቾች መወዳደር ይችላሉ፡፡አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ጠዋት ከ 2፡30-6፡30 ሰዓት ከሰአት በኂላ ከ7፡30-11፡30 ሰዓት የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃዎቻችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ የመጀመሪያ ህንጻ ሰው ሀብት ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቀርባችሁ ማመልከት ትችላላችሁ የሚቀርበው የስራ ልምድ ማስረጃ ያልተደለዘ ፣የስራው አይነት፣ የደመወዝ ልክ፣ ከመቼ እስከ መቼ እንደሰራ ጊዜውን ለይቶ የሚገልጽ የአሰሪውን ሙሉስም ፊርማና የስራ ደረጃ ያካተተ መሆን ይኖርበታል ከግል ድርጅትየሚቀርበው ማስረጃ ከፍብሎ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ገቢው የስራ ግብር ስለመከፈሉ የሚገልጽ መሆን አለበት የክልል አመልካቾች በግንባር በወኪል ፣በፖስታ ፣በፋክስ በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የስራ መጠየቂያ ቅጽ ከሌለ ግን የማስረጃዎቻቸውን ፎቶ ኮፒ ከግል ሁኔትታ መግለጫ / CV /በማያያዝ በፖስታ ሳጥን ቁጥር 1234 መላክ ይቻላል፡፡

አድራሻችን በልደታ ክፍለከተማ ቀበሌ 07/14 የኢትዮጵያ ጎማ ቁጠባ አጠገብ ስልክ ቁጥር 0115-51 54 25

አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.)
Lion Insurance Company (S.C.)

የውጭ ሀገር ዜግነት ላላቸው ባለአክሲዮኖች በሙሉ የቀረበ ጥሪ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅርቡ ባወጣው መመሪያ ቁጥር FIS/01/2016 የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን የኢንሹራንሱ ባለአክሲዮኖች ያላቸውን የአክሲዮን ሰርተፊኬት በመመለስ የተከፈለውን የአክሲዮን ዋጋው (Par Value) እና እ.ኤ.አ እስከ ጁን 30 ቀን 2016 ያልተከፈለ ትርፍ ድርሻ ክፍያ በጥሬ ገንዘብ እንዲከፈላቸው ያሳስባል::

ስለዚህ የውጭ አገር ዜግነት ያላችሁ የአንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ) ባለአክሲዮኖች በሙሉ እ.ኤ.አ ከሕዳር 23 ቀን 2016 (ከሕዳር 14 ቀን 2009 ዓ.ም.) ጀምሮ ባሉት 60 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የአክሲዮን ሰርተፊኬታችሁን ለኩባንያው በመመለስ ያላችሁን የአክሲዮን ዋጋ እና እ.ኤ.አ እስከ ጁን 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ያልተከፈለ የትርፍ ድርሻ ክፍያ ከኩባንያው የፋይናንስ እና ኢንቨስትመንት መምሪያ በአካል ወይም በህጋዊ ወኪል አማካይነት በመቅረብ እንድትወስዱ እናሳስባለን::

በመመሪያው መሰረት የውጭ አገር ዜግነት እያላቸው በተባለው ጊዜ ውስጥ በመቅረብ አክሲዮን ሰርተፊኬቶችን የማይመልሱ እና ክፍያ የማይቀበሉ ከሆነ ኩባንያው በመመሪያው በተገለጸው ኃላፊነት መሰረት የአክሲዮኑ ዋጋና እ.ኤ.አ እስከ ጁን 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ያለውን ያልተከፈለ የትርፍ ድርሻ ከአክሲዮን ሂሳብ በመቀነስ በተከፋይ ሂሳብ የሚቀመጥ መሆኑን ያሳስባል::

ሆኖም ግን ከላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የአክሲዮን ሰርተፊኬቱን ያልመለሱ እና የውጭ አገር ዜግነት እያላቸው ለኩባንያው ሳያሳውቁ በባለአክሲዮንነት ለሚቀጥሉ ባለአክሲዮኖች ይህ ሁኔታ እንደታወቀ ከአክሲዮን ባለቤትነት የሚሰረዙ እና በስማቸው ያለው የአክሲዮን ዋጋ እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚገኝ የትርፍ ድርሻ ሙሉ በሙሉ ለመንግስት ገቢ የሚደረግ መሆኑን በጥብቅ እናሳስባለን::

ለበለጠ መረጃ በሚከተለው አድራሻ ማብራሪያ መጠየቅ ይቻላል::

አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.)
ፋይናንስና ኢንቨስትመንት መምሪያ
አንበሳ ኢንሹራንስ ህንፃ 2ኛ ፎቅ
ስልክ ቁጥር +251 116188383
አዲስ አበባ

Terms of Reference for Consultancy Service to conduct an in-depth Analysis of Gambella Refugees Camps and the Host Communities for Livelihood Support programme

ETH/BID/004/2016

DanChurchAid (DCA) is a Danish international NGO providing humanitarian and development assistance to poor and marginalized people across the world. DCA started its operations in Ethiopia in the mid-1970s and has been supporting food insecure communities with relief and development assistance by working through its local partners. After receiving its official legal status to operate in the country in July 2004, DCA intensified its operation in three core program areas namely Food Security (PT3), HIV/AIDS (PT4), and Gender and Capacity Building (PT1) with major geographic focus on the rural food insecure areas in Eastern Amhara and Southern Oromia. DCA also supports humanitarian emergencies on project basis in different part of the country based on the need and availability of funding.DCA has been working in Gambella since early 2014 with non-food-items and WASH emergency response to humanitarian crisis of South Sudanese refugees. Since mid-2015 DCA has expanded its operation Gambella and included a fresh food e-voucher system set up in Tierkidi and Kule camps and it also in the process to start the e-voucher in Jewi camp targeting households with vulnerable groups such as pregnant and lactating mothers

Furthermore, together with its implementing partner, Norwegian Church Aid (NCA), DCA has been working in Jewi camp as a WASH implementing partner to construct emergency sanitation facilities in the camp.In particular, emergency communal latrines and showers in the first phase of the relocation to Jewi and it is constructing household latrines in the second phase in collaboration with the target communities, ARRA and UNHCR. As the situation in South Sudan is deteriorating, Ethiopia and in particular Gambella regional state is experiencing huge refugee influx of South Sudanese refuges with more than 36,692 new refugees since 1st of September 2016.The situation has forced UNHCR and ARRA to expand the existing camps even more than their holding capacity and have opened up new camp. The situation is creating considerable pressure on implementing agencies to seek for additional funding to respond to these heightened humanitarian needs, while it has the potential to change the dynamics between the refugees and the host communities. Given this growing demand, DCA is exploring opportunities to scale up its current operation in support of both refugees and their host communities and has decided to conduct an in-depth contextual analysis of the current livelihood status, market dynamics, socio economic needs of the refugees and their host communities and the available opportunities to improve the food security status and wellbeing of the refugees and host communities. The analysis will be conducted by an experienced consultant.

The overall objective of the task is to provide a well-documented **context analysis** of the livelihood situation in Gambella (focused on Jewi, Kule Tierkidi and Nguenyyiel refugee camps and surrounding host communities), clearlyoutliningexisting local economic dynamics, and local structures and provide **recommendations** for future programming in the refugee camps and host communities.

Minimum requirements of the consultancy firm to carry out the Livelihood Context analysis

The perspective consultant (s)should have the necessaryprofessional mix:-

The consultant should have a significant experience in conducting needs assessment, and be knowledgeable in both humanitarian and development setting particularly in relation to livelihood, food security and business development in refugee or rural setup. More specifically, the consultant(s) is expected to have the following expertise:

- Post graduate degree in marketing, business management , economics, development studies
- Proven experience of effectively undertaking similar needs assessments including market analysis
- Clear knowledge of refugee assistance programming and legal framework(s) in Ethiopia
- Knowledge of the socioeconomic dynamics of Gambella region
- The consultancy firm must ensure that the required professional mix is in place and it is able to deploy the proposed team members during the entire activities including the field visits.

Interested consultants can collect the Terms of References (ToR) for the context analysisfrom DCA Ethiopia Country Office at Welosefer, Ethio-China avenue, Kirkos Sub-City, House No. 174, Addis Ababa; Telephone 0115-514047, during the working hours starting from 7thDecember, 2016.

Interested applicants should submit their technical and financial proposalin two separate envelopes,in hardcopy with a sealed and stamped&signed envelopeson or before16th December 2016 before close of business (5:00 PM) to DCA Ethiopia officehand delivered or via biddings.ethiopia@dca.dk.

The consultant/firm should also submitacopy of sample previous work,certificate of registration; valid business license should be related to the thematic area (example license in the areas of Professional Scientific and technical services). Licenses related to financial Intermediation, insurance, Real Estateand Business services shall not be considered as valid licenses. Licenses should be renewed for the Ethiopian FY 2008 or 2009 and firms should be VAT registered. DCA shall deduct all appropriate taxes and pay to the relevant government authority.DCA Ethiopia reserves the right to cancel part or the entire bid.

IIRR
International Institute of Rural Reconstruction

የጨረታ ማስታወቂያ

አለም አቀፍ የገጠር ልማት ተቋም (International Institute for Rural Reconstruction) በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ቁጥር 0783 መሰረት በህጋዊነት ተመዝግቦ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግስታዊ ያልሆነ የልማት ተቋም ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ድርጅቱ በ ኦሮሚያና ሰገን ክልሎች በመተግበር ላይ ላለው "Pastoralist Education Project" የተሰኘ ፕሮጀክት፤ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መጽሐፍቶች ለፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

የተፈላጊ መጽሐፍቶች ዓይነት/ዝርዝር፡-

ተ.ቁ	የመጽሐፍቱ ዓይነት	የአንዱ ዋጋ	መለኪያ
1	Galaxy Chemistry Grade 7 & 8		
2	Galaxy Biology Grade 7 & 8		
3	Top Civics for Grade 7 & 8		
4	Extreme Maths Grade 7 & 8		
5	Precise Social Study Grade 7 & 8		
6	Royal Social Study Grade 7 & 8		
7	Junior Examination Based English for Grade 7 & 8		
8	Fundamental of Mathematics for Grade 7 & 8		
9	Simplified English Grammar for Grade 7 & 8		
10	Macmillan School Dictionary		
11	Alpha Problem Solving Series Chemistry Grade 7 & 8		
12	Excellent Physics and Chemistry for Grade 7 & 8		
13	Vital Dictionary of Chemistry for Grade 7& 8		
14	SMART Real Social Study Grade 7 & 8		
15	Mega: Book of Modern English Grammar with Practical Exercise		
16	Key The New Exam Book Grade 7 & 8		
17	Best English -Amharic Dictionary		
18	The New Guide to Physics for Grade 7 & 8		
19	Merit English -Amharic Dictionary		
20	Galaaksii Fiiziksii Kutaa 7 fi 8ffaa		
21	Galaaksii Keemistirii Kutaa 7 fi 8ffaa		
22	Galaaksii Herrega Kutaa 7 fi 8ffaa		
23	Galaaksii Baa'uloojii Kutaa 7 fi 8ffaa		
24	SMART English for Grade 5th & 6th		
25	Royal Barnoota Keemistirii Kutaa 7 fi 8ffaa		
26	Excellent English for Results Grade 5-8		
27	Issenshaal Fiiziksi kutaa 7 fi 8ffaa		
28	Oxford Advanced Dictionary International Student's latest Edition		
29	Elellee English-Oromo-Amharic Dictionary; 93,000 words		
30	Dungoo: Galmee Jechootaa Afaan Oromoo, Amharic and English		
31	መርቲ የአማርኛ ፈሊጣዊ አነጋገሮች		
32	ምርጥ የምሳሌያዊ አነጋገሮች		
33	አዲሱ የአማርኛ ቅኔ ከነመፈቻቸው		
34	Harreee Taphatu		
35	Marqaa		
36	Fudura Faalmaa		
37	Dubertii cimtuu		
38	Gorsa Abbaa		
39	Horaa		
40	Naachaa Fillleettii		
41	Quonnaan Bulaa fi samatota sadan		
42	Bishaan		
43	Geejjiiboota		
44	Idoowwan Bashannanaa		
45	Three in one / Afan Oromo inclusive		
46	The three hungry Goats		
47	English Alphabet/Laminated chart		
48	The cat and mouse; Red level Book 3		
49	Lame Bora; Blue Level Book 5		
50	Little two eyes; Green level book 5		
51	Domestic Animals /English/Chart		
52	Body part/English / Chart		
53	Shapes/English/Chart		

በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘረውን መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች በጨረታው ላይ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለ

1. በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላችሁ፤
2. የሚፈለግባችሁን የዘመኑን ግብር የከፈላችሁ ለመሆናችሁ ማስረጃ ማቅረብ የምትችሉ፤
3. የVATምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የምትችሉ እንዲሁም
4. የTIN ምስክር ወረቀት ማቅረብ የምትችሉ፡፡

የዋናውን ሰነድ ፎቶ ኮፒ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዛ ችሁ ማቅረብ አለባችሁ፡፡

ሀ. ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ያለምንም ክፍያ ይህ ማስታወቂያ ለመጀመሪያ ጊዜ በሪፖርተር ጋዜጣ በአማርኛው እትም ታትሞ ከወጣበት ህዳር 28 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ የስራ ቀናት ዘወትር በስራሰዓት መካኒሳ አካባቢ ወደ ቆሬ በሚወስደው መንገድ ከቀበሌ 02 ፊት ለፊት የቸሻየር ፋውንዴሽን ግቢ ውስጥ በሚገኘው በድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት መውሰድ ይችላሉ፡፡

ለ. አሸናፊ ተጫራቾች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ መጽሐፍቶችን የጨረታው ሰነድ ላይ በቀረበው ስፔሲፊኬሽን መሰረት የማጓጓዣ ወጭውን ሸፍነው እስከ ሃዋሳ ድረስ በማጓጓዝ በተጠቀሰው ጊዜ መጽሐፍቶቹን ማስረከብ ይኖርባቸዋል፡፡

ሐ. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን የመጽሐፍት ዓይነት ከጨረታ ሰነዱ ጋር በማያያዝ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

መ. ለአሸናፊ ተጫራቾች ክፍያ የሚፈፀመው ከድርጅቱ ጋር በገቡት ውል መሰረት ዕቃውን ሲያስረክቡ ይሆናል፡፡

ሰ. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ቢድቦንድ) የጠቅላላ ዋጋውን 1% በጥሬ ገንዘብ ወይም ሲፒኦ ማስያዝ አለባቸው፡፡

ረ. የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ቢያንስ ለ3 (ሦስት) ወር ማገልገል ይኖርበታል፡፡

ሠ. በቂና የተፈለገውን አይነት የጨረታ ማስከበሪያ ያላስያዙ ከውድድር ውጭ ይሆናሉ፡፡

ሸ. አሸናፊው በተሰጠው ግዜ ገደብ ውስጥ የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ውል እንዲፈርሙ ተጠይቀው ቀርበው ካልፈረሙ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ በሙሉ ይወረሳል፡፡

ቀ. ከዚህም ሌላ ለ2ተኛ አሸናፊ የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ውል እንዲፈርም ተጠይቆ ካልፈረመ ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ በሙሉ ይወረሳል፡፡

በ. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይህ ማስታወቂያ ለመጀመሪያ ጊዜ በሪፖርተር ጋዜጣ በአማርኛው እትም ታትሞ ከወጣበት ከህዳር 28 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ በ8ኛው ቀን (ዕሮብ ታህሳስ 5 ቀን 2009 ዓ.ም) በድርጅቱ የስብሰባ አዳራሽ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ይከፈታል፡፡

ተ. ድርጅቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

አድራሻ፡-መካኒሳ ወደ ቆሬ በሚወስደው መንገድ Save the Children አለፍ ብሎ ከወረዳ 02 ፊትለፊት Cheshier Foundation ግቢ ውስጥ፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0113-212994 ወይም 0113-212864 መደወል ይችላሉ፡፡

አለም አቀፍ የገጠር ልማት ተቋም (International Institute for Rural Reconstruction)

አምስተኛዋ ኢትዮጵያዊት የዓለም ኮከብ

የዓመቱ ኮከብ አትሌቶች አልማዝ አያናና ጃማይካዊው ዩዜን ቦልት

በደረጀ ጠገናው

በብራዚል አስተናጋጅነት ባለፈው ክረምት በተከናወነው 31ኛው ኦሊምፒያድ ለኢትዮጵያ ብቸኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ያስመዘገበችው አልማዝ አያና የዓለም ኮከብ አትሌት ሆና ተመርጣለች:: በወንዶች በአጭር ርቀት የዓለም ፈጣኑ አትሌት ጃማይካዊው ዩዜን ቦልት ክብሩን አግኝቷል::

የዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች ማኅበር (አይኤኤኤፍ) በሞናኮ ባለፈው ዓርብ እ.ኤ.አ. ለ2016 የውድድር ዓመት ለኮከብ አትሌት ምርጫ በሴቶች ካቀረባቸው መካከል አልማዝ አያና አሸናፊ ሆናለች:: አትሌቷ ለዚህ ክብር የበቃችው ከጃማይካዊቷ የአጭር ርቀት ተወዳዳሪ ኤሳኤ ቶምፕሰንና ከፖላንዳዊቷ የመዶሻ ወርዋሪዋ አኔታ ቮድርቼክ ልቃ በመገኘቷ መሆኑ የአይኤኤኤፍ ዘገባ አስመልክቷል:: አልማዝ በሪዮ ኦሊምፒክ የ10,000 ሜትር አዲስ የዓለም ክብረ ወሰን ከማስመዝገቧ በተጨማሪ በ5,000 የነሐስ ሜዳሊያ ባለቤት መሆኗ ይታወሳል::

ከአዲስ አበባ 657 ኪሎ ሜትር ርቃ ከምትገኘው ቤንሻንጉል ጉሙዝ የተገኘችው አልማዝ አያና፣ በአህጉራዊና ዓለም አቀፍ መድረኮች በውድድር ዓመቱ ሮም ላይ በተደረገው የዳይመንድ ሊግ ውድድር በ5,000 ሜትር የአሸናፊነቱን ድል ስትቀዳጅ፣ ርቀቱን ለማጠናቀቅ 14 ደቂቃ 12 59 ሰከንድ የወሰደባት ጊዜ የዓመቱ ምርጥ ሁለተኛ ሰዓት ነበር:: አትሌቷ በሞናኮ በተከናወነው ሥነ ሥርዓት የተቀዳጀችው ክብር ከኢትዮጵያውያቱ እንስቶች ሦስተኛዋ እንድትሆን አስችሏታል:: ከዚህ በፊት መሠረት ደፋርና ገንዘቤ ዲባባ የክብሩ ባለቤት መሆናቸው ይታወሳል::

እ.ኤ.አ. በ2010 በካናዳ በተዘጋጀው የዓለም ወጣቶች ሻምፒዮና የመጀመሪያዋን ዓለም አቀፍ የውድድር መድረክ አንድ ብላ እንደጀመረች የሚነገርላት አልማዝ በወቅቱ በ3,000 ሜትር ተወዳድራ ርቀቱን 9 ደቂቃ 08 08 ሰከንድ አጠናቃ አምስተኛ ደረጃ በመያዝ ማጠናቀቋ ግለ ታሪኳ ያስረዳል:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም በዚሁ ርቀት ስትወዳደር መቆየቷ ይነገራል::

በመካከለኛው ርቀት ብዙም መጓዝ ያልቻለችው አልማዝ እ.ኤ.አ. ከ2014 በሞሮኮ ማራካሽ በተከናወነው የአፍሪካ ሻምፒዮና በ5,000 ሜትር ተወዳድራ የርቀቱ አሸናፊም ለመሆን በቅታለች:: ከአንድ ዓመት በኋላ በቻይና ቤጂንግ በተዘጋጀው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ በ5,000 ሜትር አገሯን ወክላ የቀረበችው አልማዝ የአይበገሬነቷ ሚስጥር ጎልቶ መውጣት ጀመረ:: በጥሩነሽ ዲባባ ተይዞ የቆየው የርቀቱን ክብረወሰን በሁለት ደቂቃ በማሻሻል በእጇ ማስገባት የቻለችበትን ጊዜ ማስመዝገቧም የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው:: ባለፈው ክረምት በተከናወነው የሪዮ ኦሊምፒክ በ10,000 ሜትር ያስመዘገበችው አዲሱ የዓለም ክብረ ወሰንም ለ23 ዓመታት ተይዞ የቆየ መሆኑ አይዘነጋም::

አልማዝ አያና ይህንን ክብር ካገኙ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች አምስተኛዋ ስትሆን፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በመሆን በቅርቡ ወደ ኃላፊነት የመጣው ሻለቃ ኃይሌ ገብረ ሥላሴና ቀነኒሳ በቀለ መሸለማቸው ይታወሳል::

የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ውድድር በባህር ዳር ተካሄደ

በዳዊት ቶሎሳ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሊያከናውናቸው ካቀዳቸው ዓመታዊ የአገር ውስጥ ውድድሮች የግማሽ ማራቶን ውድድር እሑድ ኅዳር 25 ቀን 2009 ዓ.ም. በባህር ዳር ከተማ አካሂዷል::

በውድድሩ የተለያዩ ታዋቂና አዳዲስ አትሌቶች ተሳታፊ መሆን የቻሉ ሲሆን፣ አትሌቶቹም ኢትዮጵያን ወክለው በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ለመሳተፍ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ የአገር ውስጥ ውድድሮች ራሳቸውን የበለጠ ለመገምገም እንደሚያግዛቸውም ተናግረዋል::

በአሥረኛው የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ላይ በመሳተፍ አንደኛ ደረጃን በመያዝ ያጠናቀቀው ታምራት ቶላ፣ በአገር ውስጥ የሚዘጋጁ እንደነዚህ መሰል የተለያዩ ውድድሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚደረጉት ፉክክሮች የተሻለ እገዛ እንደሚያደርጉ ነው ያስረዳው::

እንደ አትሌቱ አስተያየት ከሆነ፣ አገሪቱ በዓለም መድረክ ላይ የነበራትን የአትሌቲክስ ታሪክ ከቀድሞ በተሻለ ለመሥራት የአገር ውስጥ ውድድሮችን ቁጥር በመጨመር፣ ቀደም ብሎ ማጠናቀቅ እንደሚያስፈልግም ተናግሯል::

በሪዮው 31ኛው የሪዮ ኦሊምፒያድ የአሥር ሺሕ ሜትር የነሐስ ሜዳሊያ ባለቤት የነበረው ታምራት በአገር ውስጥ የሚደረጉት ውድድሮች ውስንነትና የአትሌቶች በቡድን አለመሥራት ለአትሌቲክሱ ውጤት ማሽቆልቆል ምክንያት እንደሆነ ገልጿል::

በ2008 ዓ.ም. በሰበታ ከተማ በተካሄደው ዘጠነኛው የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ውድድር ሦስተኛ ደረጃን በመያዝ ያጠናቀቀው አትሌቱና በእንግሊዝ ካርዲፍ ሲቲ በተዘጋጀው ግማሽ ማራቶን መሳተፉ ይታወሳል:: በውድድሩ ርቀቱን በአንድ ሰዓት 00፡06 ሰከንድ በማጠናቀቅ አምስተኛ ደረጃ ይዞ መጨረሱ ይታወሳል:: በወቅቱም የኬንያውያን የቡድን ሥራ ጠንካራ መሆን የበላይነቱ ሊወሰድበት እንደቻለ ሁኔታውን በቁጭት ያስታውሳል:: በሪዮ ኦሊምፒክ በ10 ሺሕ ሜትር ላይ በቴክኒክ ጉዳይ በእንግሊዛዊ ሞ ፋራ ብልጫ የተወሰደበት እንዳስቆጨውም አልሸሸገም::

ኢትዮጵያ በረዥም ርቀት ያላትን ታሪክ በነበረበት ለማስቀጠልና ከተፎካካሪዋ ኬንያ ጋር በዓለም አቀፍ መድረክ የተሻለ ሆና ለመቅረብ ሁሉም አትሌቶች የውድድር ዕድል ተፈጥሮላቸው በአገር ውስጥ የቡድን ስሜቱን መፍጠር ዋነኛው የቤት ሥራ እንደሆነ አትሌቱ ይናገራል::

በረዥም ርቀት ጠንክሮ እንደሚሠራ የሚናገረው አትሌቱ በ10,000 እና ግማሽ ማራቶን በዓለም አቀፍ ውድድሮች ጠንካራ ሆኖ መቅረብ ዕቅዱ እንደሆነም አስተያየቱን ሰጥቷል::

በ10ኛው የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ኦሮሚያ ፖሊስን በመወከል 1 ሰዓት ከ01 ደቂቃ ከ53 ያጠናቀቀው ታምራት፣

የውድድሩ አሸናፊዎች ታምራት ቶላና ታደለች በቀለ

በሪዮ ኦሊምፒክ ላይ የተገኘውን የ10,000 ሜትር ውጤት ዘንድሮ በለንደን በሚደረገው የዓለም ሻምፒዮና ላይ አሸናፊ ለመሆን ከወዲህ ጠንክሮ እየሠራ እንደሚገኝ ጭምር አብራርቷል::

በ20ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የብሔራዊ ፌዴሬሽኑን የአመራር ኃላፊነት የተረከቡት የቀድሞ አንጋፋ አትሌቶች መመረጥ በተመለከተ፣ አትሌቲክሱ ወደ ተሻለ ደረጃ ማደግ ይችል ዘንድ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም አልሸሸገም::

‹‹ፌዴሬሽኑ በአትሌቶች መመራቱ አትሌቶች ምን ዓይነት ሥልጠና ማድረግ እንዳለባቸው፣ የሚያጋጥማቸውን ችግር እንዴት መፍታት እንደሚችሉና ውድድሮቻቸውን እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው በቅርበት ስለሚያውቁት ለመነጋገር ጭምር ይረዳል›› በማለት አትሌቱ አስተያየቱን ሰጥቷል::

ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ሻለቃ ኃይሌ ገብረ ሥላሴ በቅርበት መጥቶ ስላለው ወቅታዊ የአትሌቲክስ ጉዳይ እያማከረው እንደሆነም ሳይገልጽ አላለፈም::

አትሌቶች ስለሚያደርጉት ልምምድ ያብራራው አትሌቱ፣ ‹‹ውድድር ሳይሆን ልምምድ ማድረግ ከባድ ነው፣ በማለት ልዩነቱን የገለጸ ሲሆን፣ በአንፃሩ በልምምድ ወቅት የአትሌቶችን አቅምና ፅናት ለይቶ ለማወቅ የጎላ ድርሻ እንደሚኖረው ጭምር ተናግሯል:: ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ አትሌቶችን ከክልል በማምጣትና ፉክክርን በማስፋት በቀጣይ ለሚደረጉ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ጠንክሮ መሠራት ያስፈልጋልም ብሏል::

በአሥረኛው የኢትዮጵያ ግማሽ ማራቶን ከኢትዮጵያ ሶማሌ ክልልና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በስተቀር ስምንት ክልሎችና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ 13 ክለቦችና በግል የቀረቡ 79 ሴቶችና 154 ወንዶች በድምሩ 233 አትሌቶች ተሳትፈውበታል::

በሴቶች ታደለች በቀለ ከኦሮሚያ ማረሚያ ርቀቱን 1 ሰዓት፣ 10 ደቂቃ፣ 28 ሰከንድ በሆነ ጊዜ አጠናቃ አሸናፊ ሆናለች:: እሸቴ በከሪ ከኦሮሚያ ፖሊስ 1 ሰዓት፣ 11 ደቂቃ፣ 13 ሰከንድ ሁለተኛ፣ ጉሉሜ ቶሎሳ ከኦሮሚያ ፖሊስ ሦስተኛ ደረጃ በመያዝ አጠናቀዋል::

በወንዶች ታምራትን ተከትለው የገቡት ጌታነህ ጫላ መከላከያ 1 ሰዓት፣ 02 ደቂቃ፣ 28 ሰከንድ ሁለተኛና አረዶም ጥዑማይ ከመሰቦ ሲሚንቶ 1 ሰዓት፣ 02 ደቂቃ 40 ሰከንድ ሦስተኛ ደረጃን በመያዝ የውድድሩ አሸናፊ ሆነዋል::

በሻምፒዮናው አሸናፊ ለሆኑት በሁለቱም ጾታ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ለወጡ አትሌቶች የሜዳሊያ ሽልማት የተሰጠ ሲሆን፣ በተጨማሪም በግል ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ለወጡ አትሌቶች ከ20 ሺሕ እስከ ሦስት ሺሕ ብር ባስመዘገቡት ውጤት መሠረት ተሸልመዋል::

ፓርላማው ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ቋሚ የውይይት መድረክ አዘጋጀ

የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በፓርላማ

በዮሐንስ አንበርብር

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕግ አወጣጥና መንግሥትን በመቆጣጠር ተግባሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ሊያሳትፍ ነው፡፡

የሚሳተፉት ፓርቲዎች በአገር አቀፍ ደረጃ የተዋቀሩ እንደሚሆኑና የታደሰ የምርጫ ቦርድ ምዝገባ ሠርተፊኬት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተቀምጧል፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎችንና ሲቪክ ማኅበራትን በሕግ አወጣጥና በመንግሥት ላይ በሚያደርገው ቁጥጥር ለማሳተፍ የሚያስችለውን (ማኑዋል)በማዘጋጀት ላይ እንደሚገኝ፣ የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ አማኑኤል አብረሃ ተናግረዋል፡፡

በመተዳደርያ ደንባቸው መሠረት ጉባዔ ያላካሄዱ ፓርቲዎች በዚህ የፓርላማ ውይይት ላይ መሳተፍ እንደማይችሉ የገለጹት አቶ አማኑኤል፣ የሚሳተፉትም የታደሰ ሠርተፊኬት ሊያመጡ ይገባል ብለዋል፡፡

ይህም ማለት ምርጫ ቦርድ በሕጉ መሠረት ጉባዔ የማያካሂዱ ፓርቲዎችን ይሰርዛል ማለት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ፓርላማው ቢያንስ በዓመት ሦስት ጊዜ ከፓርቲዎቹ ጋር እንደሚወያይ፣ ነገር ግን ትልልቅ ጉዳዮች በሚኖሩበት ጊዜ ጥሪ እንደሚደረግላቸው አስረድተዋል፡፡ በዓመት ሦስት ጊዜ የሚደረገው ውይይትም ፓርላማው ዓመታዊ ሥራውን ሲጀምር፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የግማሽ ዓመት ሪፖርት ሲያቀርቡ፣ እንዲሁም በመጨረሻ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በሚያቀርበው በኦዲት ግኝትና በበጀት ላይ እንደሚሆን አቶ አማኑኤል አስረድተዋል፡፡

አባት ልጁን ሲቀጣ ስለሞተበት በገዛ እጁ ሕይወቱን አጠፋ

በታምሩ ጽጌ

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ልዩ ስሙ ቂሊንጦ በሚባለው አካባቢ አባት ልጁን ሲቀጣ ሕይወቱ ስላለፈበት በገዛ እጁ ሕይወቱን አጠፋ፡፡

ሲሳይ አዲሴ የተባለው አባት ኅዳር 23 ቀን 2009 ዓ.ም. ከቀኑ ሰባት ሰዓት አካባቢ አቤል ሲሳይ የሚባል ልጁን ‹‹ገንዘብ ወስደኃል›› በማለት ሲቀጣው፣ ጎረቤቶች ደርሰው እንዳስጣሉት ሪፖርተር ከአካባቢው ባገኘው መረጃ አረጋግጧል፡፡

አባት ለጊዜው ገላጋዮችን አክብሮ ልጁን መቅጣት ያቆመ ቢሆንም፣ ጎረቤቶቹ ወደየቤታቸው ሲመለሱ ግን ልጁ የወሰደውን ገንዘብ የት እንዳደረሰውና ምን ያህል ገንዘብ እንደወሰደ እንዲያምንለት ደግሞ ሳይቀጣው እንዳልቀረ ጎረቤቶቹ ጥርጣሬያቸውን ገልጸዋል፡፡

በንዴት ላይ የነበረው አባት ልጁን የሚመታበት ቦታ ባለመምረጡ ወይም ልጁ ሊቋቋመው ያልቻለውን ኃይል በማሳረፉ እንደሆነ ሳይታወቅ፣ ልጁ ተኝቶ ባደረበት ቦታ ጠዋት ሲያየው ሕይወቱ ማለፉን ያወቀው አባት ራሱን በራሱ በሽጉጥ መግደሉን የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡

የ13 ዓመት ዕድሜ ያለውን ታዳጊና የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ልጁን ከተገቢው በላይና ልጆች መቀጣት ባለባቸው ቦታ ላይ ባለመቅጣቱ ሕይወቱ ስላለፈበት፣ እሱም ሕይወቱን ሊያጣ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

ልጁ እንደተወለደ ከባለቤቱ ጋር በተፈጠረ አለመግባባት ሲለያዩ፣ ልጁን ይዞ ላለፉት 13 ዓመታት እናትና አባት ሆኖ በመንከባከብ ያሳደገው የ39 ዓመቱ አባት፣ በግብርና ሥራ የሚተዳደር መሆኑንና ልጁን አቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት እያስተማረው እንደነበር ታውቋል፡፡

የአቶ ሲሳይ የቀብር ሥነ ሥርዓት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በገላን ጉራና ቂሊንጦ መንበረ ፀሐይ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ኅዳር 25 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፈጸመ ሲሆን፣ የልጁ አቤል ሲሳይ ቀብር ደግሞ እናቱ በምትኖርበት ሰሜን ሸዋ ሸኖ አካባቢ መፈጸሙ ታውቋል፡፡

ማስታወቂያ